የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፬
አዲስ አበባ መስከረም ፯ ቀን ፪ሺ፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 64
ADDIS ABABA 17th September, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ ዓ.ም

የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ....... ገጽ ፬ሺ፱፻፸፮

CONTENTS

Proclamation No. 650/2009

Higher Education Proclamation …… Page 4976

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩
## የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ

በኢትዮጵያ ህዝቦች የዕድገት ፍላጎትና ዓለም አቀፋዊው ትስስር መሰረት ተቋማት አስተማማኝ የማስፈፀም ዓቅም ግንባታ ዓቅሞች እንዲሆኑ የሚያበቃ ተቋማዊ ለውጥን እንዲያረጋግጡ ለማስ ቻል ሕጋዊ ስርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ተቋማት አንገብጋቢ በሆኑ የትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት ጥያቄዎች ላይ በማተኮር የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሰላም፣ የዲሞክራሲ እና የልማት ፍላጐትን ለማሳካት አስተዋፅኦዋቸውን በብቃት እንዲያበረክቱ የሚያስችል ሕጋዊ ማዕቀፍን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት እየተስፋፋ ባለ- በት ሁኔታ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተቋም ነፃነትና ለመንግስትና ለህዝብ ጥቅም ባጠቃላይ ባለው ተጠያቂነት መካካል ተገቢው ሚዛን እንዲጠ- በቅ በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የተቋማት የአስተዳደር ስርአት በሕገ-መንግስቱ መሠረት፣ በአመክኖአዊነትና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መርህ ላይ በተመሰረተ መመራመር የሚመራ የአካዳሚክ ማሕበረሰብን ሕይወት የሚያራምድ እንዲሆን ሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ባጠቃላይ በደረሰበት የእድገት ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን ሕጋዊ አቅጣጫና አመራር በመሻቱ እና በተለይ በግል ተቋማት የሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት በትምህርት አግባብነትና ጥራት የሚጠበቅበትን አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችል አቅጣጫን የሚያስይዝ ስርዓት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 650/2009
## HIGHER EDUCATION PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to lay down a legal system to enable institutions to effect institutional transformation, and thus be able to serve as dynamic centers of capacity building consistent with the aspirations of the peoples of Ethiopia in the context of globalization;

**WHEREAS**, it has become necessary to create an appropriate legal framework to guide institutions focus on critical issues of relevance and quality of education and research to contribute with efficacy to the Ethiopian peoples' aspirations of peace, democracy and development;

**WHEREAS,** to ensure good governance in the context of an expanding higher education system, it is imperative to provide by law for an appropriate balance of an institution's autonomy and its accountability to Government and to public interests generally;

**WHEREAS**, it is necessary to provide by law that the system of governance of institutions shall promote, consistent with the Constitution, a life of a learning academic community governed by the principle of freedom of expression based on reason and rational discourse;

**WHEREAS**, the stage of development of the country's higher education in general requires legal direction and guidance to enable it become efficacious, it has also become particularly necessary to guide properly by law higher education in private institutions in order to ensure and promote its positive contributions through relevant and quality education;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "አካዳሚክ ማሕብረሰብ" ማለት በተቋም ውስጥ በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት በመማር፣ በማስተማር እና በምርምር ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችን ያቀፈ ነው፤

፪/ "አካዳሚክ መኮንን" ማለት የምርምርና ህትመት መኮንን፣ ሬጂስትራር እና የመሳሰሉትን መኮንኖች ማለት ነው፤

፫/ "የአካዳሚክ ሰራተኛ" ማለት በማስተማር እና/ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ የተቋም ሰራተኛ ሲሆን ሰኔት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛ ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ የተቋሙ ባለሙያንም ይጨምራል፤

፬/ "የትምህርት ክፍል" ማለት የአንድ ተቋም አካል የሆነ ኮሌጅ፣ ፋካልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢኒስቲትዩት፣ ማዕከል ወይም ዲፓርትመንት ነው፤

፭/ "የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር፣ የቢዝነስ አመራር፣ የፋይና-ንስና የሂሳብ ሥራ፣ የምግብ አገልግሎት ማቅረብ፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከና ውን የተቋም ሰራተኛ ነው፤

፮/ "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው፤

፯/ "ማዕከል" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የትምህርት ስትራ-ተጂ ማዕከል ነው፤

፰/ "ከፍተኛ ትምህርት" ማለት በስነጥበብ፣ ማሕበራዊ ሳይንስና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ ፕሮግራሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ሥር በተመለከቱት የትምህርት አግባቦች የሚሰጥ ትምህርት ነው፤

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Higher Education Proclamation No. 650/2009."

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "academic community" means all those persons studying, teaching and doing research as permanent or visiting members of an institution;

2) "academic officer" means research and publication officer, registrar and other similar officers;

3/ "academic staff" means members of an institution employed in the capacity of teaching and/or research, and any other professional of the institution who shall be recognized so by senate statutes;

4/ "academic unit" means a college, faculty, school, an institute, a department or a centre established as a constituent unit of an institution;

5/ "administrative support staff" means personnel of an institution employed to provide administrative, business management, accounting, catering, maintenance, safety, security and such other services;

6/ "Agency" means Education Relevance and Quality Agency to be established by regulation of the Council of Ministers;

7/ "Centre" means Education Strategy Centre to be established by regulation of the Council of Ministers;

8/ "higher education" means education in the arts and sciences offered to undergraduates and graduate students who attend degree programmes through any of the delivery modes stated under Article 19 of this Proclamation;

፱/ "ተቋም" ማለት የመንግሥት ወይም የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

፲/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፩/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ "የግል ተቋም" ማለት በአንድ ግለሰብ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥር ባላቸው ሰዎች ባለቤትነት ወይም ዓላማቸው ለትርፍ ባልሆነ ማሕበራት ወይም በሕብረት ስራ ማህበራት ወይም በንግድ ማሕበርነት የተመሠረተ ወይም በውጭ አገር የተመሠረተና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

፲፫/ "የመንግስት ተቋም" ማለት እንደ አግባብነቱ በጀቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

፲፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፭/ "የቴክኒክ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ያልሆነና የመማር ማስተማርንና የምርምር ሥራን ለማገዝ የተቀጠረ ሰራተኛ ሲሆን በማስተማርያ ሆስፒታሎች ውስጥ የተቀጠረ የአካዳሚክ ሰራተኛ ያልሆነን ባለሙያንም ይጨምራል፤

፲፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል::

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተቋም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሃይማኖት ተቋም ሥር ባለና ዓላማውና የትምህርት ሥርዓቱ ኃይማኖት ነክ በሆነ ተቋም ላይ እንዲሁም የዲፕሎማ እና የሰርተፊኬት ስልጠና ብቻ በሚሰጥ ተቋም ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

9/ "institution" means a public or private higher education institution;

10/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Education, respectively;

11/ "person" means a natural or juridical person;

12/ "private institution" means a non-public higher education institution established by one or more individual owners or by non-profit making associations, founded as co-operative society or commercial association, or higher education institution established abroad and operating in Ethiopia;

13/ "public institution" means an institution whose budget is allocated by the Federal or State Government, as the case may be;

14/ "state" means any state specified in Article 47 of the Constitution of the Federal Democractic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

15/ "technical staff" means non-administrative personnel employed to support the teaching-learning and research processes and non-academic professional medical personnel employed in a teaching hospital;

16/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply to any institution operating in Ethiopia.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, this Proclamation shall not apply to institutions under religious organizations and whose objectives and curricula are primarily religious and to those institutions that offer only diploma and certificate programmes.

## ፬. የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች

የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ አገሪቱ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድ ትሆን የሚያስችሏት በእውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የታነፁ ምሩቃንን በአገሪቱ ፍላ ጐት መሠረት በተገቢ የሙያ መስኮችና የትምህርት ዓይነቶች ማፍራት፤

፪/ በአገሪቱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ትኩረቱ በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የሆነ ምርምርን ማራመድና ማጎልበት፤

፫/ ትምህርትና ምርምር በአመክኖአዊነትና ተቀባ ይነት ባለው የሃሳብ ልውውጥ መርህ ላይ የተመሰረተ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ ነፃነትን የሚያጎለብት መሆኑንና ከማንኛውም አድሎ የፀዳ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፬/ በአገሪቱ የዕድገት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የማሕበረሰብና የማማከር አገልግሎትን ማበርከት፤

፭/ ተቋማዊ ነፃነትን ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥ፤

፮/ በተቋማት አስተዳደር የቁልፍ ባለ ድርሻዎች ተሳትፎን ማረጋገጥ፤

፯/ በተቋማት እንቅስቃሴ ፍትህን፣ ፍትሃዊነት- ንና የሕግ የበላይነትን ማራመድና መጠበቅ፤

፰/ ዴሞክራሲያዊ ባህልን ማሳደግና የማሕበረሰቡ የባህል ብዙህነትን መጠበቅ፤

፱/ የመንግስት ተቋማት ስርጭት ሚዛናዊ መሆ ኑን ማረጋገጥና የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎን የአገሪቱ ፍላጎትንና ፍትሃዊነትን መሠረት በማድረግ ማስፋፋት።

## ክፍል ሁለት
## ስለተቋማት፣ የተቋማት ሠራተኞች እና ተማሪዎች

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስለተቋማት

## ፭. መቋቋም

፩/ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይቋቋማል።

፪/ በክልል መንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም በክልሉ በሚወጣ ሕግ መሠረት ይቋቋማል። ሆኖም በክልል መንግስት የሚወጣው ሕግ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና ሌሎች የፌዴራል አነስተኛ የጥራት መመዘኛዎችን ሳይነካ መሆን ይኖርበታል።

## 4. Objectives of Higher Education

The objectives of higher education are to:

1/ prepare knowledgeable, skilled, and attitudinally mature graduates in numbers with demand-based proportional balance of fields and disciplines so that the country shall become internationally competitive;

2/ promote and enhance research focusing on knowledge and technology transfer consistent with the country's priority needs;

3/ ensure that education and research promote freedom of expression based on reason and rational discourse and are free from biases and prejudices;

4/ design and provide community and consultancy services that shall cater to the developmental needs of the country;

5/ ensure institutional autonomy with accountability;

6/ ensure the participation of key stakeholders in the governance of institutions;

7/ promote and uphold justice, fairness, and rule of law in institutional life;

8/ promote democratic culture and uphold multicultural community life;

9/ ensure fairness in the distribution of public institutions and expand access on the basis of need and equity.

## PART TWO
## INSTITUTIONS, STAFF AND STUDENTS OF INSTITUTIONS

## SECTION ONE
## INSTITUTIONS

## 5. Establishment

1/ A public institution financed by the federal government shall be established by regulation of the Council of Ministers.

2/ A public institution financed by a state government shall be established by law enacted by the state; provided however, that the state law shall comply with the requirements of this Proclamation and other federal minimum quality standards.

፫/ አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የግል ተቋም እንደ አግባብነቱ በማሕበራት፣ በንግድ ማሕበራት፣ በሕብረት ሥራ ማሕበራት ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ይቋቋማል::

፬/ ማንኛውም ተቋም የሚቋቋመው፣ የሚለወጠው ወይም ማሻሻያ የሚደረግበት የሚከተሉትን ባካተተ የኘሮጀክት እቅድ ላይ በመመሥረት ይሆናል፡-

ሀ) ማሕበራዊ ተቀባይነት ያላቸው የተቋም ዓላማዎችን ያስቀመጠ፤

ለ) የተቋሙ ደረጃና ዋና ዋና አካዳሚክ ክፍሎች ዝርዝር እና የትምህርት ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን ያካተተ መግለጫ፤

ሐ) የተቋሙን አካዳሚክ ሰራተኞች፣ የትምህርት መገልገያዎችና የገንዘብ ምንጭን የሚገልፅ መረጃ፤

መ) ትምህርትና ምርምርን በብቃት ለማካሄድ የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዓት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤

ሠ) የአገሪቱ አነስተኛ የጥራት መመዘኛዎችን የሚያከብር ስለመሆኑ የፅሑፍ ማረጋገጫ::

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሥር የተመለከቱትን በሚመለከት ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል::

፮/ የግል ተቋምን ለማቋቋም የሚቀርበው የፕሮጀክት ዕቅድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሥር ከተመለከቱት መረጃዎች በተጨማሪ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጉዳዮች ካካተተ የመመሥረቻ ፅሁፍ ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የተቋሙን ተግባራት ወሰን፤

ለ) ተቋሙ የሚገለገልባቸውን ንብረቶችና የወጪ መሸፈኛ ምንጭ፤

ሐ) የተቋሙን የአመራር አካላትና ወኪሎች::

፯/ ስለተቋም መቋቋም፣ መለወጥ ወይም መሻሻል የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ በውጭ አገር በተቋቋመ ተቋም ወይም የተቋሙ ቅርንጫፍ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## ፮. ሕጋዊ ሰውነት

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ ይችላል::

3/ Without prejudice to the provisions of this Proclamation, a private institution shall be established in accordance with the law governing associations, business organizations, cooperatives or any other relevant law.

4/ Any institution shall be established, changed or modified on the basis of a project which shall:

a) set socially acceptable aims for the proposed institution;

b) contain a description of the status and main academic units of the institution, and documentation on programmes and curricula;

c) provide data on the research and teaching staff, the facilities, and the funding schemes;

d) provide for a management system which shall guarantee effective delivery of education and research;

e) undertake to comply with minimum national standards and requirements.

5/ The Ministry shall issue directives on application of the provisions of sub-article (4) of this Article.

6/ The project for the establishment of a private institution shall, in addition to the requirements under sub-article (4) of this Article, be accompanied by a memorandum of establishment specifying the institution's:

a) scope of activities;

b) property and source of funding;

c) management bodies and agents.

7/ The requirements for the establishment, change or modification of an institution under this Article shall apply *mutatis mutandis* to the establishment of an institution or a branch of an institution that originates in a foreign country.

## 6. Legal Personality

An institution established in accordance with this Proclamation shall have legal personality and, as such, it shall be entitled to own property, to enter into contracts, and to sue and be sued in its own name.

## ፯. የተቋማት መሪ እሴቶች

ተቋማት ለተልእኳቸው መሳካት የሚያራምዱዋቸውና የሚጠብቋቸው መሪ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለፅ ነፃነት፤

፪/ በተልዕኮ ስኬት ላይ የተመሰረተ ታዋቂነት፤

፫/ አካዳሚያዊ ተወዳዳሪነትና በትብብር ላይ የተመሰረተ ዝምድና፤

፬/ የተቋም ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር፤

፭/ አሳታፊ አስተዳደርና የሕግ የበላይነት፤

፮/ ፍትህና ፍትሃዊነት፤

፯/ ሙስናን የመታገል ባህል፤

፰/ ጥራትንና ቀልጣፋነትን ያቀናጀ አገልግሎት መስጠት፤

፱/ ቆጣቢ የሃብት አጠቃቀምና ውጤታማ የንብረት ክብካቤ፤

፲/ ለምስጉን ሰው እውቅና መስጠት፤

፲፩/ ዴሞክራሲና የባህል ብዙህነት።

## ፰. የተቋም ሃላፊነት

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ተቋም የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩/ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና የተቋማት መሪ እሴቶችን የማክበር፣ የትምህርትና ምርምር ተቋም መሆኑን የማረጋገጥ፤

፪/ የትምህርት ፕሮግራሞችን የመቅረፅና የከፍተኛ ትምህርትን የመስጠት፤ በአገሪቱ ፍላጐት ላይ በመመሥረት በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የታነፁ ምሩቃንን የማፍራት እና በፕሮግራሞቹ መሠረት የተለያዩ የትምህርት ማስረጃዎችን የመስጠት፤

፫/ በሃገራዊ የትኩረት አቅጣጫ መሰረት አግባብነት ያላቸው የጥናት፣ ምርምር እና የማሕበረሰብ አገልግሎትን ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሃገራዊና ከባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የማካሄድና ግኝቶቹንም ተገቢ በሆነ አግባብ የማሰራጨት፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከአገር ውስጥና ከውጭ ተቋማት እና ከሌሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመተባበር አካዳሚያዊና የምርምር ፕሮጀክቶችን የማካሄድ፤

፬/ በዚህ አዋጅና ተፈፃሚነት ባላቸው የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች መሰረት ሰራተኞቹን የመቅጠርና የማስተዳደር፤ የተቋሙን ገንዘብና ንብረትም የማስተዳደር፤

## 7. Guiding Values of Institutions

The guiding values that institutions shall promote and uphold in pursuance of their mission are:

1/ pursuit of truth and freedom of expression of truth;

2/ institutional reputability based on successful execution of mission;

3/ competitiveness in scholarship and cooperation with other institutions;

4/ institutional autonomy with accountability;

5/ participatory governance and rule of law;

6/ justice and fairness;

7/ a culture of fighting corruption;

8/ quality and speedy service delivery;

9/ economical use of resources and effective maintenance of assets;

10/ recognition of merit;

11/ democracy and multiculturalism.

## 8. Responsibilities of Institutions

Without prejudice to other provisions of this Proclamation, every institution shall:

1/ uphold the objectives of higher education and the guiding values of the institution; and ensure that it is an institution of scholarship;

2/ develop programmes of study and provide higher education; prepare and supply qualified graduates in knowledge, skills, and attitudes on the basis of needs of the country; and award academic qualifications in accordance with its programmes;

3/ undertake and encourage relevant study, research, and community services in national and local priority areas and disseminate the findings as may be appropriate; undertake, as may be necessary, joint academic and research projects with national and foreign institutions or research centres;

4/ recruit and administer its personnel and manage its finance and property in accordance with this Proclamation and other applicable laws;

፭/ በዚህ አዋጅ መሰረት የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈፀም፤

፮/ የተቋሙን ዕቅድ፣ በጀትና አደረጃጀት የማዘጋጀትና የመተግበር፤ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት ያፈፃፀም ሪፖርቶችን የማቅረብ፤

፯/ በተልዕኮው ላይ በመመስረት ከኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነቶችን የመመስረት፤

፰/ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ወይም ለሕብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦች እውቅና ወይም ሽልማት ወይም የክብር ዲግሪዎችን የመስጠት፤

፱/ ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እገዛ ማድረግና እንደአስፈላጊነቱ ለመሰናዶና ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች እገዛ ማድረግና ከነሱ ጋር መተባበር፤

፲/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አመታዊና የቀደምት አመታት የትምህርት ግብአትና ውጤት እንዲሁም የፋይናንስ ገቢና ወጪ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሳተም፤

፲፩/ በዚህ አዋጅና በማቋቋሚያው ሕግ ወይም በመመስረቻው ሰነድ የተሰጠውን ሌሎች ሃላፊነቶችን የመወጣት::

## ፱. ስለተቋም ደረጃ

ማንኛውም ተቋም ቀጥሎ ከተመለከቱት በአንዱ መቋቋም ይችላል፡-

፩/ ዩኒቨርስቲ፤

፪/ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፤

፫/ ኮሌጅ፤

፬/ ኢንስቲትዩት::

## ፲. ስለትምህርት ደረጃ

በዚህ አዋጅ ስለተቋማት ደረጃ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በማንኛውም ተቋም የሚሰጥ ሥርዓተ ትምህርት፡-

፩/ በባችለር (ቢ.ኤ/ቢ.ኤስ.ሲ) ዲግሪ፤

፪/ የሕክምና ዶክተር (ኤም.ዲ.) ወይም የእንስሳት ሕክምና ዶክተር (ዲ.ቪ.ኤም) ዲግሪ፤

፫/ የማስትሬት ዲግሪ (ኤም.ኤ እና ኤም.ኤስ.ሲ) ወይም የሕክምና ወይም የሌላ ሙያ ስፔሻሊስት፤

5/ legislate and implement internal rules and guidelines in accordance with this Proclamation;

6/ prepare and implement institutional plans, budget and organizational structures, and submit performance reports in accordance with this Proclamation;

7/ establish cooperation relations with industries and other institutions in pursuit of its mission;

8/ give recognition or award prizes or honorary degrees to persons of outstanding achievements or contributions to society;

9/ provide support to primary and secondary education and provide support and cooperate with preparatory and technical and vocational schools as may be appropriate;

10/ publish annual and multi-year statistics on educational input-and-output and financial incomes and expenditures as stipulated in this Proclamation;

11/ discharge other responsibilities provided for in this Proclamation and in its instrument of establishment.

## 9. Status of Institutions

Any institution may be established as an entity having the status of:

1/ university;

2/ university college;

3/ college;

4/ institute.

## 10. Levels of Curriculum and Education

Without prejudice to the provisions of this Proclamation on status of institutions and subject to senate decisions, curricula to be developed by any institution shall have programmes, as may be appropriate, leading to the award of:

1/ Bachelor Degree (BA/BSc);

2/ Medical Doctor (MD) or Doctor of Veterinary Medicine (DVM) degree;

3/ Master's Degree (MA/MSc), or a Medical or other Professional Specialty;

፬/ የዶክትሬት (ፒ.ኤች.ዲ) ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ፣ ወይም

፭/ በሴኔት የተወሰነ ማንኛውም ሌላ ዲግሪ፣

የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## ፲፩. የዩኒቨርስቲ ደረጃ ስለመስጠት

፩/ ማንኛውም ተቋም "ዩኒቨርስቲ" የሚለው ስያሜና ደረጃ በሚኒስቴሩ የሚሰጠው የሚከተሉትን መመዘኛዎች ሲያሟላ ይሆናል፡-

ሀ) በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ ፪ሺ እና ከዚያ በላይ ተማሪዎችን ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ ፕሮግራሞች የማስተማር አቅም ሲኖረው ወይም በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ ፪ሺ እና ከዚያ በላይ ተማሪዎችን ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ አራት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ የማስተማር ዓቅም ሲኖረው፤

ለ) በዩኒቨርስቲ ኮሌጅነት ወይም በኮሌጅነት ወይም በኢኒስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለአራት ተከታታይ አመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ ሲሆን፤

ሐ) አግባብነት ባላቸው የተለያዩ መስኮች ምርምር የሚያደርግ፣ የምርምር ውጤቶቹን ያሳተመ እና የምርምር ግኝቶችን ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍባቸውን መንገዶች ያመቻቸ ሲሆን፤

መ) በሚኒስቴሩ የወጡ ሃገራዊ አነስተኛ የደረጃ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ደረጃውን የጠበቀ ስርዓተ ትምህርት፣ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ በዚህ አዋጅ የተደነገገውን ተቋማዊ የአስተዳደር አደረጃጀት፣ የማስተማሪያ ክፍሎች፣ ቤተመፃሕፍትና ቤተሙከራዎች ያለው እና ሌሎች ለየትምህርት መስኩ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ያሟላ ሲሆን፤ እና

ሠ) ሌሎች በሚኒስቴሩ የተቀመጡ አነስተኛ የደረጃ መመዘኛዎችን ሲያሟላ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ተቋም የዩኒቨርስቲ ስያሜና ደረጃ ይዞ እንዲቋቋም ታስቦ ከሆነና ያለው የሃብት አቅርቦትና ተቋማዊ እቅድና ራዕይ ሲታይ የታሰበው ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተቀመጡትን መመዘኛዎች ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያሟላ ይችላል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን ተቋሙ ዩኒቨርስቲ ሆኖ መቋቋም ይችላል፡፡

4/ Doctorate (PhD) Degree or its equivalent; or

5/ any other degree that may be determined by the academic senate.

## 11. Granting the Status of a University

1/ An institution shall be granted the name and status of a “university” by the Ministry where:

a) it has a minimum enrollment capacity of 2,000 students in regular undergraduate and graduate programmes in at least three academic units larger than departments, or it has a minimum enrollment capacity of 2,000 students in regular undergraduate programmes in at least four academic units larger than departments;

b) it has a record of at least four consecutive classes of graduates in a degree programme if it has been rendering services of higher education after being accredited as a university college, college or institute;

c) it undertakes research in different appropriate fields, has published its research products and has facilitated means of dissemination of the research findings to end-users;

d) it has a curriculum that match the national standards set by the Ministry, the necessary academic staff, institutional governing structures as provided for by this Proclamation, teaching materials, classrooms, libraries, laboratories, and other appropriate discipline-related facilities; and

e) it fulfills other minimum national standards set by the Ministry.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article and without prejudice to Article 5 of this Proclamation, an institution may be established with the name and the status of a university if it is conceived as such and its resource provisions as well as its institutional plans and vision are such that it can, in the judgment of the Ministry, fulfill the requirements set forth under sub-article (1) of this Article in an acceptable time.

፫/ በመደበኛና በርቀት ትምህርት ላይ ወይም በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ የተመሰረተ ተቋም የዩኒቨርስቲ ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ የራሱን ጥናት በማድረግ ወይም መልካም ዓለም አቀፍ ተሞክሮን በመጠቀም በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል።

## ፲፪. የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃን ስለመስጠት

፩/ ማንኛውም ተቋም ከሚኒስቴሩ "ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) ከተመለከቱት በተጨማሪ፡-

ሀ) በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ ቁጥራቸው ቢያንስ ፪ሺ የሆኑ ተማሪዎችን ከዲፓርትመ- ንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ የማስተማር አቅም ያለው፣ እና

ለ) በኮሌጅነት ወይም በኢንስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለሶስት ተከታታይ አመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ፣

መሆን አለበት::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተ ጠበቀ ሆኖ አንድ ተቋም ያለው የሃብት አቅርቦት፣ ተቋማዊ እቅድና ራዕይ ሲታይ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተቀመጡትን መመዘኛዎች ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያሟላ ይችላል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን ተቋሙ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሆኖ መቋቋም ይችላል::

፫/ በመደበኛና በርቀት ትምህርት ላይ ወይም በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ የተመሰረተ ተቋም የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ የራሱን ጥናት በማድረግ ወይም መልካም ዓለም አቀፍ ተሞክሮን በመጠቀም በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል።

## ፲፫. የኮሌጅ ደረጃን ስለመስጠት

አንድ ተቋም በሚኒስቴሩ "ኮሌጅ" የሚለውን ስያ ሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (መ) እና (ሠ) ከተመለከቱት መመዘኛዎች በተጨማሪ ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆነ አንድ የትምህርት ክፍል በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል::

3) The Ministry shall determine the university status of an institution that offers a combination of regular and distance or virtual education or only distance and/or virtual education on the basis of, as the case may be, its own study or in accordance with international good practice.

## 12. Granting the Status of a University College

1/ An institution that may be granted the name and status of a "university college" by the Ministry shall, in addition to the requirements stipulated under paragraphs (c), (d) and (e) of sub-article (1) of Article 11 of this Proclamation:

a) have a minimum enrollment capacity of 2,000 undergraduate students in its regular degree programmes in three academic units larger than departments; and

b) have a record of at least three consecutive classes of graduates in a degree programme if it has been rendering services of higher education after being accredited as a college or an institute.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article and without prejudice to Article 5 of this Proclamation, an institution may be established with the name and status of a university college if its resource provisions as well as institutional plans and vision are such that it can, in the judgment of the Ministry, fulfill the requirements set forth under sub-article (1) of this Article in an acceptable time.

3) The Ministry shall determine the university college status of an institution that offers a combination of regular and distance or virtual education or only distance and/or virtual education on the basis of, as the case may be, its own study or in accordance with international good practice.

## 13. Granting the Status of a College

An institution that may be granted the name and status of a "college" by the Ministry shall, in addition to the requirements stipulated under paragraphs (d) and (e) of sub-article (1) of Article 11 of this Proclamation, offer higher education in degree programmes at least in one academic unit larger than departments.

## ፲፬. የኢኒስቲትዩት ደረጃን ስለመስጠት

አንድ ተቋም ከሚኒስቴሩ "ኢኒስቲትዩት" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (መ) እና (ሠ) ከተቀመጡት በተጨማሪ፡-

፩/ ቢያንስ በአንድ የትምህርት መስክ ወይም አይነት ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችል፣ እና

፪/ በሚሰጠው የትምህርት አይነት በዲግሪ ደረጃ ትምህርት የመስጠት አቅም ያለው፣

መሆን ይኖርበታል፡፡

## ፲፭. አዲስ መንግሥታዊ ተቋም ስለማቋቋም

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ እና ፲፪ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እን ደተጠበቁ ሆነው አዲስ መንግስታዊ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በዩኒቨርስቲ ወይም በዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃ ሊቋቋም ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ አዲሱ መንግስታዊ ተቋም ከደረጃው የሚጠበቁ መመዘኛዎችን በሙሉ ማሟ ላቱን ያረጋግጣል፡፡

## ፲፮. ስለአካዳሚያዊ ነፃነት

፩/ ማንኛውም ተቋም በተቋሙ ተልዕኮና በአለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት አካዳሚያዊ ነፃነት ይኖረዋል፡፡

፪/ ማንኛውም ተቋም ማሕበረሰቡ የአካዳሚያዊ ነፃነቱን ሲያራምድ የማሕበራዊ ሃላፊነት ባሕልን እንዲያበለፅግ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፫/ ማንኛውም ተቋም በዚህ አዋጅና በዓለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት የአካዳሚያዊ ነፃነት አተገባበር በሥርዓት እንዲመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ፲፯. የመንግስት ተቋማት ነፃነት

፩/ ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ተልእኮውን ለማስፈፀም ይችል ዘንድ በዚህ አዋጅ ተቋማዊ ነፃነቱ ተረጋግጧል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት የቦርዱና የሚኒስቴሩ ሃላፊነት እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት ተቋማት ነፃነት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

## 14. Granting the Status of an Institute

An institution that maybe granted the name and status of an institute by the Ministry shall, in addition to the requirements stipulated under paragraphs (d) and (e) of sub-article (1) of Article 11 of this Proclamation:

1/ be able to give education and training at least in one field or discipline; and

2/ have a capacity in the discipline to offer education in a degree programme.

## 15. Establishment of New Public Institution

1/ Notwithstanding the provisions of Articles 11 and 12 of this Proclamation and without prejudice to other provisions of this Proclamation, a new public institution may be established as a university or a university college on the basis of decision by the Council of Ministers.

2/ The Ministry shall ensure that the new public institution meets all the requirements expected of its level.

## 16. Academic Freedom

1/ Academic freedom shall be guaranteed for every institution in pursuit of its mission and consistent with international good practice.

2/ Every institution shall cultivate the culture of social responsibility in its academic community in the exercise of academic freedom.

3/ Every institution shall regulate the exercise of academic freedom in accordance with this Proclamation and international good practice.

## 17. Autonomy of Public Institutions

1/ Every public institution is hereby granted the necessary autonomy in pursuit of its mission.

2/ Subject to the responsibilities of the Board and the Ministry as stipulated in this Proclamation, autonomy of public institutions shall also include to:

ሀ) አግባብነት ያላቸውን የሥርአተ ትምህርትና የምርምር ፕሮግራሞች ማዘጋጀትና ማካሄድ፤ አዳዲስ ፕሮግራሞችን መክፈት ወይም ነባሮችን መዝጋት፤ አደረጃጀቱን መወሰንና የውስጥ ደንብንና መመሪያዎችን ማውጣትና መተግበር፤

ለ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የአካዳሚክና ሌሎች ሰራተኞቹን መቅጠርና ስለሥራ አፈፃፀም ብቃት ባስቀመጣቸው መመዘኛዎችና በሚሻው ውጤት መሰረት ኃላፊነታቸውን መወሰን፤

ሐ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ተፈፃሚነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መርሆዎች መሰረት የሰው ሃይሉን ማስተዳደር፤

መ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ፕሬዚዳንቱን፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና የቦርድ አባላትን በእጩነት ማቅረብ፤ የትምህርት ክፍሎች መሪዎችን መምረጥና መሾም፤

ሠ) በዚህ አዋጅና ተፈፃሚነት ባላቸው ሌሎች ሕጎችና ደንቦች መሠረት የገንዘብ ሃብቱንና ንብረቱን ማስተዳደር፡፡

፫/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ነፃነቱን ሲያራምድ ሕጋዊነት፣ ውጤታማነት፣ ግልፅነት፣ ፍትህና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

## ፲፰. ስለመንግስታዊ ተቋም የአካዳሚክ ክፍሎች ነፃነት

፩/ ማንኛውም ተቋም አሳማኝ በሆነ የትምህርት ዓይነቶች ወይም የትምህርት ዓይነት ቅርንጫፎች መጣመር ላይ የተመሰረቱ አስፈላጊ አደረጃጀት ያላቸውና ተገቢው ስያሜ የተሰጣቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፪/ የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም አካዳሚክ ክፍሎች ተቋሙ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚያወጣቸው ድንጋጌዎች፣ መመዘኛዎችና ያፈፃፀም ስርዓት መሰረት በአስተዳደር፣ በፋይናንስና በአካዳሚክ ጉዳዮች ነፃነት ይኖራቸዋል፡፡

፫/ የተቋማት ፕሬዚዳንቶች የአካዳሚክ ክፍሎች ባላቸው ነፃነት ሃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ አስፈላጊው ተቋማዊ ድጋፍ፣ አመቺ ሁኔታዎችና በቂ ሀብት እንዲኖሯቸው ማስቻል ይኖርባቸዋል፡፡

a) develop and implement relevant curricula and research programmes; create new or close existing programmes; set up its organizational structure and enact and implement its internal rules and procedures;

b) consistent with other provisions of this Proclamation, select, through a transparent system of competition, academic and other staff to be employed by the institution and designate or determine their responsibilities based on institutional requirements and expectations concerning performance and quality of work;

c) administer its personnel based on the provisions of this Proclamation and the principles of other applicable laws;

d) nominate the president, vice presidents and members of the Board, and select and appoint leaders of academic units and departments as provided for by this Proclamation;

e) manage its funds and property on the basis of this Proclamation and other applicable laws and regulations.

3/ Every public institution shall exercise its autonomy in ways that, at the same time, ensure lawfulness, efficiency and effectiveness, transparency, fairness, and accountability.

## 18. Autonomy of Academic Units of Public Institutions

1/ Every institution shall have academic units with the minimum necessary hierarchical governance structures and with appropriate nomenclature that shall be based on reasonable and justifiably clustered disciplines or fields or branches of a discipline.

2/ Subject to rules, standards and procedures established by the institution, consistent with this Proclamation, academic units of a public institution shall have the necessary autonomy in administration and finance as well as in academic affairs.

3/ Presidents shall ensure that academic units are provided institutionally with the necessary support and enabling systems and resources to fulfill their responsibilities as autonomous units.

## ፲፱. ስለትምህርት ፕሮግራሞች

፩/ በተለየ ሁኔታ ካልተቋቋመ በስተቀር የማንኛውም ተቋሞ ቁልፍ ተግባር በመደበኛ ፕሮግራሞች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ ምርምር ማካሄድና ለማሕበ-ረሰብ አገልግሎት መስጠት ይሆናል፡፡

፪/ ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ማንኛ ውም ተቋም በተጨማሪ በሚከተሉት መንገዶች ትምህርትና ስልጠና መስጠት ይችላል፡-

ሀ) ተከታታይ ትምህርት፤

ለ) የርቀት ወይም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዝ ትምህርት፡፡

፫/ ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ማንኛ ውም ተቋም በተጨማሪ የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት ወይም በአንድ የተወሰነ የሙያ መስክ እውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት ተገቢውን ሰርተፊኬት መስጠት ይችላል፡፡

## ፳. የማስተማሪያ ቋንቋ

፩/ በሌሎች ቋንቋዎች ትምህርት መስጠት ወይም ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የማንኛውም ተቋም የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ለአጫጭር ስልጠና እና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መምህራን ማዘጋጃ የሚፈፀም ሙያዊ ሥልጠና በተፈላጊው ቋንቋ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

፫/ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት በምልክት ቋንቋ መሰጠት ወይም መደገፍ ይኖርበታል፡፡

## ፳፩. ሥርዓተ ትምህርት

፩/ በማንኛውም ተቋም የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ ትግበራና የምዘና ዓላማ ተማሪው ተገቢው ሳይንሳዊ ዕውቀት፣ በነፃነት የማሰ ላሰል ክህሎት፣ ሃሳቡን የመግለፅ ክህሎ-ቶችና ሙያዊ እሴቶችን እንዲጨብጥ በማስቻል ብቁ ባለሙያን ማዘጋጀት ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም ተቋም የትምህርት ክፍሎቹ የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃን በተገቢ የምሩቃን ብቃት መመዘኛዎች እንዲመራ ያደርጋል፡፡

## 19. Education Programmes

1/ Unless specifically established otherwise, the core business of any institution shall be to offer education and training through regular programmes, conduct research, and render community services.

2/ Subject to demonstrable competence, any institution may also offer education and training through the following programmes:

a) continuing education;

b) distance or virtual education.

3/ Subject to demonstrable competence, any institution may also give short-term trainings for capacity building, or for imparting knowledge and skills in specific fields, and award appropriate certificates.

## 20. Language of Instruction

1/ The medium of instruction in any institution, except possibly in language studies other than the English language, shall be English.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, short-term trainings and preparation of teachers for primary schools and grades may be given in any appropriate languages.

3/ Education for students with complete hearing impairment shall be given in or supplemented by appropriate sign language.

## 21. Curriculum

1/ Curricular design, delivery, and assessment of learning outcomes in any institution shall aim at enabling the learner to acquire pertinent scientific knowledge, independent thinking skills, communication skills and professional values that together prepare him to become a competent professional.

2/ Every institution shall guide curricular development by its academic units through appropriate learning outcomes.

፫/ ተቋማት ወቅታዊ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃን የሚያስጠብቅ ተቋማዊ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ስርዓት ይኖራቸዋል፤ የትምህርት ክፍሎቻቸው ስርዓቱን ስለመተግበራቸውም ያረጋግጣሉ::

፬/ ከአንድ ባላይ ብዛት ላላቸው ተቋማት የጋራ የሆነ ስርዓተ ትምህርት በነዚሁ ተቋማት ተሳትፎ በጋራ ሊቀረፅ ይችላል፤ ስርዓተ ትምህርቱም በሁሉም ፈፃሚ ተቋማት የሚተገበር አነስተኛው መመዘኛ ሆኖ ያገለግላል::

፭/ ሀገራዊ ጥቅሞችና አግባብነት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም በተቋማት የጋራ ተሳትፎ ሥርዓተ ትምህርቶች ሊዘጋጅላቸው የሚገቡ ፕሮግራሞችንም ጨምሮ ለሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ስርዓተ ትምህርቶችን የመቅረፅና የመተግበር ነፃነት ይኖረዋል::

፮/ የስርዓተ ትምህርት አተገባበር በምርምርና ጥናት ላይ የተመሠረተና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፤ የመማር ማስተማር ሂደቱም በዝግጅቱ፣ በአሰጣጡ እና በምዘና ስርዓቱ ሁሌም ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል::

፯/ የእያንዳንዱ ተቋም ሥልጣን እንደተተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ለመንግስታዊ ተቋማት የጋራ የሆኑ ስርዓተ ትምህርቶች ቀረፃን ሊያስተባብር ይችላል፤ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎችን ለማስፈፀምም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

፰/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሃገራዊ የሥርዓተ ትምህርት ቡድኖች ወይም ምክር ቤቶች ወይም የሥርዓተ ትምህርት ግምገማ፣ ቀረፃና ትግበራን የሚያስተባብርና የሚከታተል አካል ሊያቋቁም ይችላል::

## ፳፪. ስለተቋም ጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት

፩/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እና አግባብነት ያላቸው ደንቦችና መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም አስተማማኝ የሆነና በየጊዜው የሚሻሻል የጥራት ማጐልበቻ ሥርአት ይኖረዋል::

፪/ የማንኛውም ተቋም ውስጣዊ የጥራት ማጎ ልበቻ ሥርዓት የአካዳሚክ ሰራተኞች የሙያ ልማትን፣ የትምህርት ይዘትን፣ የመማር ማስተማሩ ሂደትን፣ የተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥን ያካተተ ግልፅና የተሟላ የጥራት መለኪያን የያዘ መሆን ይኖርበታል፤ በተጨማሪም ተማሪዎች የትምህርት ይዘትን፣ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን፣ የምዘና፣ የፈተናና የውጤት አሰጣጥ ሥርዓቱን የሚገመግሙበት ስርዓት ይኖረዋል::

3/ Institutions shall have suitable framework that provide for purposeful curricular development; and shall ensure its implementation by academic units.

4/ Curricula common to any number of public institutions may be developed jointly through the participation of the public institutions responsible for their implementation; and such curricula shall serve as the minimum requirements applicable to any of the institutions.

5/ Without prejudice to national interests and relevance, every institution shall enjoy the liberty of developing curricula for all of its academic programmes, including concerning programmes for which nationally applicable curricula may be developed through joint efforts of institutions.

6/ Curriculumm delivery shall be research and study-based and up-to-date and the teaching-learning process shall be continuously updated in its design, delivery methods, and instruments of assessment.

7/ The Ministry may, without prejudice to the legitimate authority of the individual institutions, coordinate curricula development common to public institutions and issue directives as may be necessary to bring the provisions of this Article into operation.

8/ The Ministry may establish, whenever necessary, national panels or councils or a body to coordinate and monitor curricula review, development and implementation.

## 22. Institutional Quality Enhancement

1/ Without prejudice to other provisions of this Proclamation and the relevant regulations and directives, every institution shall have a reliable internal system for quality enhancement that shall be continuously improved.

2/ The internal system of quality enhancement of every institution shall provide for clear and comprehensive measures of quality covering professional development of academic staff, course contents, teaching-learning processes, student evaluation, assessment and grading systems, which shall also include student evaluation of course contents together with the methods and systems of delivery, assessment, examinations and grading.

፫/ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓቱ በተቋሙ ለመማር መረጃ ለሚጠይቁ ታሳቢ ተማሪ ዎች ከሚሰጥ መረጃ አንስቶ ተማሪዎች ትምህርቱንና ቆይታቸውን ሲያጠናቅቁ እስከሚሰጡት ግምገማ ድረስ ባሉት በሁሉም የትምህርት አግባብነትና ጥራትን በሚመለከት ሂደት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬/ ማንኛውም ተቋም የጥራት ደረጃ መመዘኛ ዎችን ማዘጋጀት፣ በየጊዜው አካዳሚያዊ ኦዲት ማድረግና በኦዲት የተመለከቱ ድክመቶችን መከታተልና ማስተካከል እንዲሁም ግምገማውን፣ የተከናወኑ ተግባራትን እና የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ ተገቢ ሰነዶችን መያዝና ለኤጀንሲውም መላክ ይኖርበታል፡፡

፭/ ተቋማት ጥራት ማጎልበትን አስመልክቶ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በኤጀንሲው የሚሰጡ ተገቢነት ያላቸው አስተያየቶችን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡

፮/ የተቋም የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓትን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

፯/ ሚኒስቴሩ፣ ማዕከሉና ኤጀንሲው የተመራቂዎች ቁልፍ ባህሪያትን ወይም የምሩቃን የብቃት መመዘኛዎችን እንደየነገሩ ሁኔታ በሚወስን ወይም በሚያመላክት ሃገራዊ የምሩቃን ብቃት ማዕቀፍ አማካኝነት ጭምር የተቋማት ጥራትን የማጎልበት ጥረትን እና የሥርአተ ትምህርት ቀረፃን አቅጣጫ ያስይዛሉ፡፡

## ፳፫. ስለ አካዳሚክ ምክርና ድጋፍ

፩/ ማንኛውም ተቋም አግባብነት ባላቸው ክፍሎችና በአካዳሚክ ሰራተኞቹ አማካኝነት በተቋሙ ስለሚሰጡ የትምህርት አይነቶች እና ስለትምህርቱ ይዘት፣ አደረጃጀትና የተማሪዎች ምዘና ስርዓት በተገቢ ተቋማዊ ስርዓት ለተማሪዎቹና ለአመልካቾች መግለፅ ይኖርበታል፡፡

፪/ ማንኛውም ተቋም በየትምህርት አይነቱ በትምህርት ላይ ቆይታቸው ጊዜ በሙሉ ለተማሪዎች የአካዳሚክ የምክርና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡

፫/ የአካዳሚክ ምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ልዩ አካዳሚያዊ ድጋፍ የሚያሻቸው ተማሪዎች መኖራቸውን ከጠቆመ የተቋማት የትምህርት ክፍሎች ድክመቶቹን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

3/ The quality enhancement system shall be applied to all processes of importance to the quality of study programmes, beginning with the information provided to potential applicants and ending with student evaluation upon completion of the course.

4/ Institutions shall develop quality standards, undertake academic audit on a periodic basis, follow-up and rectify the deficiencies revealed by the audit, and maintain appropriate documentation of the audit, activities undertaken and of the ensuing results, and submit such documentations regularly to the Agency.

5/ Institutions shall be responsible to give practical effect to appropriate recommendations by the Agency on quality enhancement measures that have to be taken.

6/ Details on institutional systems of quality enhancement shall be included in the internal regulations of institutions.

7/ The Ministry, the Centre, and the Agency shall also guide institutional quality enhancement efforts as well as curricula development through a national qualifications' framework that shall, as the case may be, determine or indicate core learning outcomes or graduate competencies.

## 23. Academic Guidance and Counseling

1/ Every institution, through its relevant units and academic staff, shall officially and properly inform students and applicants of the courses of study available, the content, structure, and requirements of each course.

2/ Every institution shall assist students throughout the duration of their courses of study by providing them with specialized academic advice and counseling relating to their studies.

3/ Academic units shall take remedial actions where academic advice and counseling reveal the need for special academic support and follow up.

፬/ ተቋማት እንዳስፈላጊነቱ የትምህርት መስኮች ምርጫን አስመልክቶ ለተማሪዎች የቅድመ ቅበላ የማማከር አገልግሎት ሥርዓትን ለመመሥረት የሚያስችላቸው እርምጃን ይወስዳሉ::

## ፳፬. ምርምርና የምርምር አቅጣጫዎች

፩/ በማንኛውም ተቋም የሚካሄድ ምርምር የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማሳደግ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ባተኮሩ የአገሪቱ የልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ይሆናል::

፪/ ማንኛውም ተቋም ከቁልፍ የውስጥና የውጭ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በሀገር ፍላጎት፣ በተቋሙ ተነፃፃሪ ሙያዊ ዓቅም እና ባለው የገንዘብ ሀብት የተወዳዳሪነት ብልጫው ላይ ተመሥርቶ ምርምር የሚደረግባቸው ጉዳዮች ቅደም ተከተልን መለየት ይኖርበታል::

፫/ ማንኛውም ተቋም የሚያካሂደው ምርምር በተለይ፡-

ሀ) በአገሪቱ ቀዳሚ ፍላጎት ላይ በመመስረት በቴክኖሎጂ ሽግግር ችግር ፈቺ የሆነና የማስፈፀም ዓቅምን የሚገነባ፣

ለ) አግባብነት ያላቸው ቀጣይ ጥናቶችና ምርምሮችን ለማካሄድ እንዲችሉ ተማሪዎችን በመሠረታዊ የምርምር ዕውቀትና ክህሎት የሚያስታጥቅ፣

መሆን አለበት::

፬/ ማንኛውም ተቋም በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የራሱ ምርምርን ለማካሄድና የምርምር ፕሮጀክቶችን ከሌሎች ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት፣ የምርምር አካላት እና ኢንዱስትሪዎች በጋራ ለማካሄድ የሚያስችለው ተቋማዊ ስርዓት ይኖረዋል::

፭/ ምርምር ማካሄድን የሚመለከቱ የአደረጃጀ-ትና የማኔጅመንት ዝርዝር ጉዳዮች በተቋሙ የሚወሰኑ ይሆናሉ::

፮/ ማንኛውም ተቋም አከራካሪ ጉዳዮችን አብራርቶ በመደንገግ እና ዓቅምና ተፈፃሚነትን ግምት ውስጥ በማስገባት በምርምር አጀንዳውና ዕቅዱ መሰረት አካዳሚክ ሠራተኞቹን በዋናነት በመምህርነት ወይም በተመራማሪነት ወይም ሁለቱንም በማቀናጀት እንዲያካሂዱ አድርጎ የሚያሰማራበት ግልጽነት ያለው ሥርዓት ይኖረዋል::

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተቋም እያንዳንዱ የአካዳሚክ ሠራተኛውን በሥነ-ጽሑፍ ላይ በተመሰረተ ጥናት ወይም በልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ባተኮረ ምርምር ላይ መሠማራቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል::

4/ Institutions shall explore and establish as necessary a system of pre-admission counseling of students on study choice.

## 24. Research and Research Directions

1/ The focus of research in any institution shall be on promoting the relevance and quality of education and on the country's development issues focusing on transfer of technology.

2/ Every institution shall define its core research areas and themes on the basis of the priority needs of the country, the institution's comparative advantages, and in consultation with the key stakeholders.

3/ More specifically, every institution shall undertake research that shall:

a) take into account the priority needs of the country and enable the country to solve its challenges and build its capacity through technology transfer;

b) equip students with basic knowledge and skills that enable them to undertake further and relevant studies and research.

4/ Every institution shall have an institutionalized system that enables it to carry out planned research and conduct joint research projects with other national and international institutions, research centres, and industries.

5/ Particulars on the organization, management, responsibilities, and procedures required to conduct research shall be determined by each institution.

6/ Every institution shall have a transparent system of research that deploys purposefully its academic staff as primarily teachers, researchers, or combinations thereof on the basis of its research agenda and plan, demonstrable merit, and practicality, and with stipulations clarifying debated areas.

7/ Without prejudice to sub-article (6) of this Article, every institution shall ensure that all and everyone of its academic staff are engaged in study activities based on literature or research focusing on developmental issues.

፰/ ማንኛውም ተቋም ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፫፻ ቀናት ውስጥ ወይም አዲስ የሚቋቋም ተቋም ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የተቋሙንና የአካዳሚክ ሰራተኞቹን አፈፃፀምን የሚቃኙ የምርምርና የምክር አገልግሎት የብቃት መመዘኛዎች፣ ሙያዊ ስነምግባር እና ሃላፊነትን የደነገጉ መመሪያዎችና ያፈፃፀም ስርዓቶች ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ፳፭. የምርምርና ፈጠራ ፈንድ

፩/ ማንኛውም ተቋም የምርምርና ፈጠራ ፈንድ ይኖረዋል፡፡

፪/ ማንኛውም ተቋም በበጀት ምደባና ሌሎች ድጋፎች በተለይ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ማሻሻል ላይ ላተኮረ ምርምር ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተ ጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተቋም ቅድሚያ የሚሰጠውን የምርምር ሥራ መንግስታዊ ካልሆነ ምንጭ በሚያገኘው ገቢ ተጠቅሞ ማካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም ተቋሙ ከመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ካልሆነ ምንጭ በተለይ ለምርምር የተመደበለት ገንዘብ ባግባቡ እና በሙሉ ለምርምር ተግባር መዋሉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፬/ ማንኛውም ተቋም ግልፅነት ያለው የምርምር ፈንድ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

፭/ ማንኛውም ተቋም ወይም የተቋሙ አካዳሚክ ሠራተኛ ከሌሎች አካላትና ከውጭ አገር ምንጭ በሚገኝ ገንዘብ የጋራ የምርምር ሥራ ማካሄድ የሚችለው የምርምሩ ሥራ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፰) ሥር በተገለጸው መሰረት በተቋሙ የሥነ-ምግባር ስርዓት ክልል የሚከናወን ከሆነ ነው፡፡

## ፳፮. የምክር አገልግሎት እና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት

፩/ ተቋማት በብቃታቸው መሠረት የምክር አገልግሎትና ተጓዳኝ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

፪/ የመንግስት ተቋማት የአካዳሚክ ሠራተኞ- ቻቸው የሚካሄዱት የምክር አገልግሎትና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ተቋሙ እንዲያከናውን የተቋቋመባቸው ሥራዎች ጥራትና አፈፃፀምን ሳይነኩ መከናወናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

8/ Every institution shall issue rules and procedures on research and consultancy standards, code of professional ethics, norms, responsibilities that shall govern its operations and the activities of its academic staff within 300 days from the effective date of this Proclamation, and in case of a new institution, within a year from the date of its establishment.

## 25. Research and Innovation Fund

1/ Every institution shall establish research and innovation fund.

2/ Every institution shall allocate sufficient fund particularly for research focusing on technology transfer and innovation.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, any institution may conduct research in the priority areas using incomes from non-public sources; and it shall ensure that all such funds as well as public funds allocated specifically for research are utilized with efficiency and efficacy.

4/ Every institution shall have a transparent system of research fund management and utilization.

5/ Any institution or any of its academic staff may enter into joint research and receive research funds from external and foreign sources if the research falls within the research standard, code of professional ethics, and norms of the institution as shall be stipulated in accordance with sub-article (8) of Article 24 of this Proclamation.

## 26. Consultancy and other Supplementary Activities

1/ Institutions may perform consultancy or other supplementary activities in areas related to their competence.

2/ Public institutions shall ensure that undertaking of consultancy or other supplementary activities by academic staff shall not in any way compromise the quality, extent, and availability of activities for the implementation of which the public institutions are established.

፫/ የመንግስት ተቋማት በአካዳሚክም ሆነ በሌሎች ሠራተኞቻቸው የሚከናወኑ ተጓዳኝ ተግባራት ተልዕኳቸውን እና የተመሰረቱባቸው ሕጋዊና የስነምግባር መርሆዎችን የማይሸረሽሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸ ዋል::

፬/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ተቋሙ አዲስ የተቋቋመ ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በሠራተኞቹ የሚከናወኑት የምክር አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት የሚመሩበትን መመሪያ ማውጣት ይኖርበታል::

፭/ ማንኛውም ተቋም ከኢንዱስትሪዎች ጋር ግልፅነት ባለው ድርድርና ስምምነት መሠረት መርህን የጠበቀና የጋራ ጥቅምን የሚያራምድ ግንኙነት የመመስረት ሃላፊነት አለበት::

፮/ የግለሰቦች አእምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት መብቶችና ውል የተገባበት ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተቋም ለአካዳሚክ አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ ይደረጉ የነበሩትን ዕውቀትና ክህሎት ለሕብረተሰቡ ግልጋሎት እንዲውሉ የማድረግ ሃላፊነት አለበት::

፯/ ተቋማት በምክር አገልግሎቶች አማካይነት የሚያገኟቸውን ውጤቶች ለአካዳሚክ አገልግሎቱ ማዳበሪያና ለመማር ማስተ-መሩ ሂደት ማበልጸጊያ አንድ ምንጭ አድርገው መጠቀም ይኖርባቸዋል::

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከተውን መመሪያ ተላልፎ በመገኘቱ አግባ-ብነት ባለው ሃላፊ የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሚ የመተ-ላለፍ ሁኔታ የፈፀመ ሰው በተቋሙ የዲስፕሊን ደንብ መሠረት እርምጃ እንዲ-ወሰድበት ይደረጋል::

፱/ ማንኛውም የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ጥሰት መኖሩን የተገነዘበ የቅርብ ሃላፊ ወይም የተቋሙ ባለሥልጣን በሕጋዊ ሥርዓት መሠረት ጥሰቱን የማስቆም ሃላፊነት ይኖርበታል፤ ይህን ሃላፊነቱን ካልተወጣ ወይም ችላ ካለ የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል::

## ፳፯. <u>መረጃ ስለማግኘት</u>

፩/ ተቋማት ስታቲስቲካዊ መረጃ የሚሰበሰቡ-በትንና በመካከላቸው፣ በክፍሎቻቸው መካከልና ከሚኒስቴሩ ጋር መረጃዎችን የሚለዋወጡበት ቀልጣፋ ሥርአት መፍጠር ይኖርባ ቸዋል::

3/ Public institutions shall ensure that undertaking of supplementary activities by academic or other staff does not erode their mission, or their legal and ethical standards and foundations.

4/ Every public institution shall issue detail directives to regulate consultancy services or other supplementary activities rendered by its academic staff within one year from the effective date of this Proclamation, and in case of a new institution, within two years from the date of its establishment.

5/ Every institution shall have the responsibility to forge relations with industries for mutual benefits and on the basis of principled and transparent negotiations and agreements.

6/ Without prejudice to individual intellectual property rights and agreements on confidentiality, every institution shall have the responsibility to put at the service of the wider community the knowledge and skills that have hitherto been utilized only for academic purposes.

7/ Institutions shall use the results of the consultancy services as one source to deliver informed academic services and to enrich teaching and learning.

8/ Any non-compliance by any academic staff with the directives referred to in sub-article (4) of this Article shall constitute sufficient ground for disciplinary action against the violator in accordance with the institutions disciplinary rules, if the violator persists in his violations after the first instance official warning by an appropriate person of the institution.

9/ Any immediate supervisor or any other pertinent official who is aware of any violation of the provisions of this Article shall have the responsibility to stop it through due process; and shall be liable to appropriate disciplinary action if he neglects his responsibility.

## 27. <u>Access to Information</u>

1/ Institutions shall establish efficient systems for statistical data collection and information exchange among themselves, their units, and with the Ministry.

፪/ ተቋማት ትክክለኛ፣ ዝርዝርና የተሟላ አመታዊ የትምህርትና የገንዘብ ገቢና ወጪ ስታቲስቲካዊ መረጃ ማሳተም ይኖርባቸዋል፡፡ መረጃን የማሳተሙ ግዴታ ከአቅም በላይ የሆነ ክስተት ካላጋጠመ በስተቀር አንድ የትምህርት ዘመን እንደተጠናቀቀ በአንድ መቶ ሃያ ቀናት ጊዜ ውስጥ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

፫/ በሕግ የተደነገጉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምርምር ለሚያካሂዱ የአካዳሚክ ሰራተኞችና ተማሪዎች መረጃ የመስጠትና የመተባበር ሃላፊነት አለባቸው፡፡

**፳፰. <u>የአካዳሚክ ዘመን እና የበጀት ዓመት</u>**

፩/ የማንኛውም ተቋም የመደበኛ ፕሮግራም አንድ የትምህርት ዘመን እኩል በሆኑ ሴሚስተሮች የተከፈሉ ፫፻ ቀናት ይኖሩታል፡፡

፪/ የማንኛውም ተቋም ሴኔት የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የትምህርት ዘመንን ይወስናል፡፡

፫/ የመንግሥት ተቋማት የበጀት ዓመት የመንግሥት በጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የተቋማት ሠራተኞች

**፳፱. <u>የሠራተኞች ዓይነት</u>**

ማንኛውም ተቋም፡-

፩/ አካዳሚክ ሠራተኞች፣

፪/ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣

፫/ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣

፬/ እንደ አግባቡ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ ባለሙያዎች፣

ይኖሩታል፡፡

**፴. <u>አካዳሚክ ሠራተኞች</u>**

፩/ ማንኛውም ተቋም የሚከተሉት አካዳሚክ ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፡-

2/ Institutions shall publish accurate, detailed, and comprehensive annual educational and financial statistical data. The statistical data shall be published, except in circumstances of force majeure, within 120 days after the end of an academic year.

3/ Without prejudice to legal restrictions, governmental and non-governmental organizations shall have the responsibility, upon request, to cooperate in providing the necessary information to academic staff or students who undertake research.

**28. <u>Academic Calendar and Fiscal Year</u>**

1/ The minimum standard of an academic year of regular programmes in institutions shall be 300 calendar days, divided equally into appropriate semesters.

2/ The senate of every institution shall determine the actual academic year in accordance with the provisions of sub-article (1) of this Article.

3/ The fiscal year of every public institution shall be the fiscal year of the Government.

## SECTION TWO
## STAFF OF INSTITUTIONS

**29. <u>Category of Staff</u>**

Any institution shall have:

1/ academic staff;

2/ technical support staff;

3/ administrative support staff;

4/ professionals in teaching hospitals, as may be appropriate.

**30. <u>Academic Staff</u>**

1/ Any institution may have the following academic staff:

ሀ) ለማስተማርና/ወይም ለምርምር የተቀጠሩ ኘሮፌሰሮች፣ ተባባሪ ኘሮፌሰሮች፣ ረዳት ኘሮፌሰሮች፣ ሌክቸረሮች፣ ረዳት ሌክቸረሮች እና በሁኔታዎች አስገዳጅነትና ለመሸጋገሪያ ጊዜ የሚቀጠሩ ረዳት ምሩቆች፤

ለ) በዓለም ዓቀፍ መልካም ተሞክሮዎችና በተቋሙ ሴኔት ውሳኔና ደንብ መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛነት እውቅና የተሰጣቸው ሌሎች ሠራተኞች::

፪/ ማንኛውም ተቋም ለአካዳሚክ ሰራተኞች የማዕረግ ዕድገት የሚሰጥበትና አዲስ ቅጥርን የሚፈፅምበት ዓለም አቀፋዊ መልካም ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ የዕድገትና የቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ይኖረዋል።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የባችለር ዲግሪ ምሩቃን በመደበኛ አካዳሚክ ሠራተኛነት በመንግስታዊ ተቋም ሊቀጠሩ የሚችሉትና ማዕረጋቸው የሚወሰነው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል::

፬/ ማንኛውም ተቋም በጥራትና በቁጥር በቂ የአካዳሚክ ሠራተኞች እንዳሉት ማረጋገጥ ይኖርበታል:: የአካዳሚክ ሰራተኞች ብዛት በተቋሙ የሚወሰን ሆኖ በተማሪ መምህር ምጣኔና ለምርምር በሚያስፈልግ ተጨማሪ ቁጥር ላይ የተመሰረተ ይሆናል::

፭/ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ አገራዊ የማስተማርና የምርምር ሥራዎች ጫና መስፈርት ይኖራል:: መስፈርቱ በመንግሥት ተቋማት የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶና በቦርዱ ተደግፎ በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል:: ሚኒስቴሩ መስፈርቱን በግል ተቋማትም ተፈፃሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል::

፮/ ሚኒስቴሩ ማንኛውም ተቋም ማሟላት ያለበትን በትምህርት ደረጃና በማዕረግ አነስተኛው የአካዳሚክ ሰራተኞች ምጣኔን በየጊዜው ያወጣል::

፯/ በድህረምረቃ ፕሮግራሞች ዓቅሙ በተሻለ ዕድገት ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ተቋም እንደ አንድ ሀገራዊ ቀዳሚ ተግባሩ ያነሰ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው ልማት ያለ ትምህርት ክፊያ እገዛ ያደርጋል::

፰/ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ለአንድ አካዳሚክ ቅጥር ቦታ የሚያመለክት ሰው ሊቀጠር የሚችለው ከቅርብ ጊዜ አሰሪው የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል ብቻ ይሆናል::

a) professors, associate professors, assistant professors, lecturers, assistant lecturers and, under unique circumstances or conditions of transition, graduate assistants employed for teaching and/or research;

b) other employees of the institution considered academic staff by decision of the senate following international good practice and the provisions of the institution's internal regulations.

2/ Every institution shall institute rules and procedures on employment and promotion of its academic staff, consistent with international good practices.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, graduates with bachelor degrees may be employed as regular academic staff in government institutions only on the basis of directives to be issued by the Ministry.

4/ Every institution shall ensure adequate supply of academic staff in quality as well as in numbers. The size of academic staff in an institution shall be based on staff-to-student ratios and additional research requirements that shall be determined by the institution.

5/ There shall be national standards for teaching and research loads applicable in all public institutions. The standard loads shall be formulated by the forum of public universities and be implemented upon recommendation by the respective Boards and approval by the Ministry. The Ministry may decide to apply the standards on private institutions.

6/ The Ministry shall issue, from time to time, minimum academic staff ratios with regard to educational qualifications and professional ranks, which shall be complied with by every institution.

7/ Any public institution endowed with better postgraduate programme resources shall assist, free of tuition charges and as a matter of national priority, in the academic staff development of less so endowed public institutions.

8/ Without prejudice to other pertinent laws, any applicant to an academic position in an institution shall be considered for employment only if he produces a letter of release from his last employer.

፱/ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ ተቋም በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት የተባረረ አካዳሚክ ሠራተኛ በሌላ ተቋም መቀጠር የሚችለው የቀድሞ ታሪኩ፣ የተባረረበት ጥፋትና ከተባረረ በኋላ ያለበት ሁኔታ ታይቶና ተገምግሞ በሴኔት ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል።

፲/ ማንኛውም ተቋም እንደነገሩ ሁኔታ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።

## ፴፩. የአካዳሚክ ሠራተኛ መብት

፩/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም የአካዳሚክ ሠራተኛ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

ሀ) በተቋሙ ተልዕኮ መሠረት የአካዳሚክ ነፃነትን የመጠቀም፤

ለ) በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ምርምር የማካሄድና ሙያዊ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤ እንዲሁም በተቋሙ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የሳባቲካልና የምርምር ዕረፍቶችን በመውሰድ ለተቋሙና ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ምርምሮችና ጥናቶች የማካሄድ፤

ሐ) በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያ መሠረት ሙያውን የሚያዳብር ትምህርትና ሥልጠናን የማግኘት፤

መ) በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስቴሩ በሚወጣ ሀገራዊ መስፈርት መሠረት የሙያ ዕድገትን የማግኘት፤

ሠ) ግልፅና ፍትሃዊ አስተዳደር የማግኘትና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በሚፈቅደው መሠረት በመንግስት የሚወሰን ወይም በግል ተቋሙ ዓቅም ላይ የተመሠረተ ደሞዝና ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት፤

ረ) በተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ፣ ዕቅድና የውስጥ ደንብና መመሪያዎች ዝግጅትና የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ላይ እንደአመቺነቱ የመሳተፍና በመማር ማስተማር ሂደት አግባብነትና ጥራት ላይ አስተያየት የማቅረብ፤

ሰ) ስለ ስራ አፈፃፀሙ የተደረገ ግምገማ ውጤትንና ያለእርሱ ዕውቀት በግል ማህደሩ ውስጥ ስለተቀመጡ መረጃዎች የማወቅ፤ እንዲሁም በማህደሩ ውስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች ለተቋሙ አስተዳደራዊ ጉዳይ ወይም አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በሚስጢር እንዲያዙለት የማድረግ፤

9/ Without prejudice to other applicable laws, any academic staff who has been dismissed for disciplinary reasons may be employed in another institution only after a proper review and scrutiny of his prior history, the nature of the disciplinary offence that caused his dismissal and his situation after the dismissal, and upon the prior approval by the senate.

10/ Every institution shall have, as may be appropriate, the obligations to implement the provisions of this Article.

## 31. Rights of Academic Staff

1/ Without prejudice to other provisions of this Proclamation, every academic staff shall have the right to:

a) exercise academic freedom based on the institution's mission;

b) conduct research and render consultancy services in accordance with internal regulations of the institution; and take sabbatical and research leaves to conduct research and studies beneficial to the institution and the country, in accordance with internal regulations of the institution;

c) be entitled to further education and training for professional development, subject to internal rules and regulations of the institution;

d) be promoted and assume new academic rank on the basis of merit in accordance with the institution's rules and regulations and in accordance with national norms and standards the Ministry may issue as necessary;

e) enjoy transparent, fair, and equitable administration and system of remuneration and benefits that shall be instituted by Government as the economic condition of the country may permit or as the income of a private institution may permit;

f) participate, as feasible, in formulations of institutional direction, plans, regulations, and in curricula development and make comments on the quality and appropriateness of the teaching-learning process;

g) be informed on his performance results and of any records kept in his personal file without his prior knowledge as well as enjoy confidential maintenance of information in his personal file except for the official business of the institution or the provisions of pertinent laws require otherwise;

ሸ) በተቋሙ ግቢ ውስጥ የራሱና የግል ንብረቱ ደህንነት ተጠብቆ ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት፤

ቀ) ስለተቋሙ ዕቅድ፣ ዕድገት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ ሁኔታና የክንውን ውጤቶች መረጃ የማግኘት፤

በ) አካዳሚክ ሠራተኛን መምረጥ ተገቢ በሆነበት ሁሉ የመመረጥና የመምረጥ፤

ተ) በዲስፕሊን ጉዳይ የመሰማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳለት የመጠየቅና ፍትህን የማግኘት::

፪/ ማንኛውም ተቋም አካዳሚክ ሠራተኞቹን በሚመለከቱ የመብት ጉዳዮች ላይ በአሳታፊ ሂደት የውስጥ ደንብና ያፈፃፀም ስርዓትን የመቅረፅና ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለበት::

## ፴፪. የአካዳሚክ ሠራተኛ ግዴታ

፩/ የተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ የማስተማር፣ የአካዳሚክ ምክር አገልግሎትና የሕብረተሰብ አገልግሎት የመስጠት፤

ለ) በራሱ የሙያ መስክና ብቃት መሰረት ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ችግር ፈቺ ጥናትንና ምርምርን የማካሄድና ዕውቀትና ክህሎትን የማሸጋገር፣ ወይም ቢያንስ የሚያስተምረውን ትምህርት በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የማድረግና በየጊዜው የማሻሻል፤

ሐ) ሥርዓተ ትምህርትን በመገምገም፣ በመቅረፅና በማጎልበት ሂደት ላይ የመሳተፍና ተገቢውን ሚና የመጫወት እንዲሁም በሥርዓተ ትምህርቱ አተገባበር በተማሪዎች ምዘና፣ ውጤት አሠጣጥ፣ ማማከር፣ የተማሪዎችን ቅሬታዎችና አቤቱታዎችን በማስተናገድና ባጠቃላይ በሙያዊ ሥነ-ምግባር የሚጠበቅበትን ሙያዊ ብቃት የማረጋገጥ፤

መ) የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና ተቋሙ የሚመራባቸውን እሴቶች የማክበር፣ የመተግበርና አካዳሚክ ነፃነቱን በሙያዊ ስነምግባር እና አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የመጠቀም፤

ሠ) ተማሪዎች የተቋሙን ተልዕኮ፣ መሪ እሴቶችና የከፍተኛ ትምህርት ዓላማ ዎችን እንዲያውቁ የመምከር፣ የማገዝና የመርዳት፤

h) enjoy campus security for himself and for his personal property while rendering the proper services;

i) be informed on the plan, development, direction, condition and performance of the institution;

j) elect and be elected where election of academic staff is the norm;

k) receive due process in disciplinary matters and demand and receive redress in cases of inappropriate decisions.

2/ Every institution shall formulate rules and procedures on all matters of rights of its academic staff and adopt and implement the same after having them duly debated through participatory processes.

## 32. Responsibilities of Academic Staff

1/ Every academic staff member of an institution shall have the responsibilities to:

a) teach, including assisting students in need of special support, and render academic guidance or counseling and community services;

b) undertake problem-solving studies and researches and transfer knowledge and skills, in the specific area of self-competence and professional position, that are beneficial to the country; or at least ensure that own teaching is research and study-based and continuously updated;

c) participate in curriculum development, review, and enhancement; and the required professional standard in curriculum delivery, student assessment, grading, counseling, and management of student complaints and grievances, and in professional ethical standards in general;

d) uphold, respect and practice the objectives of higher education and the guiding values of the institution; and exercise academic freedom with professionalism and consistent with the applicable provisions of this Proclamation;

e) counsel, assist and support students in acquainting themselves with the mission and guiding values of the institution as well as with the objectives of higher education;

ረ) ሙሉ የሥራ ጊዜውን ለተቋሙ የማዋል፤

ሰ) በመማር-ማስተማር ሂደት የራስን ፖለቲካዊ አመለካከት ወይም ሃይማኖት በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ከመጫን የመቆጠብ፤

ሸ) ከተቋሙ ማሕበረሰብ አባላት በሚኖረው ግንኙት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ መብቶችን ከሚፃረሩ ድርጊቶችና አሰራሮች የመቆጠብ፤

ቀ) በተቋሙ የማቋቋሚያ ሕግ ወይም መመሥረቻ ሰነድ እና በተቋሙ የሴኔት ደንብ መሠረት የሚሰጡት ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፤

በ) ከሌላ ተቆም ጋር አስቀድሞ በሚደ-ረግ ስምምነት መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ ስለመቅጠር በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሙሉ ሃይሉን፣ የሥራ ጊዜ-ውንና ትኩረቱን ለተቋሙ የማዋል።

፪/ አካዳሚክ ሰራተኞች የሆኑ የጤና ባለሙያ ዎች በተቋሙ የማስተማሪያ ሆስፒታል ውስጥ በሙያቸው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታም ይኖርባቸዋል፡፡

፫/ ተቋማት በዚህ አንቀጽና አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረተና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ያሳተፈ የአካዳሚክ ሠራተኞች የዲስፕሊን ደንብ አውጥተው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፫) የተመለከተውን ደንብ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ወይም አዲስ ተቋም ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን አንስቶ ባሉት ፫፻ ቀናት ውስጥ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ፴፫. <u>ስለአካዳሚክ ሠራተኞች ቋሚነትና የጡረታ መውጫ ዕድሜን ስለማራዘም</u>

፩/ እንደ ልዩ ጥቅምና ለሙያ ልቀት ማበረ-ታቻ እንዲሆን አንድ አካዳሚክ ሠራተኛ ቋሚ ቅጥር ሊደረግ ይችላል። የአካዳሚክ ሠራተኛ ቋሚ ቅጥር የሚሆነው በሰጠው አገልግሎትና ባበረከተው የማስተማር እና/ወይም የምርምር ምሁራዊ አስተዋፅኦ ወይም ባስመዘገበው የተቋም መሪነት ብቃት ላይ ተመስርቶ ይሆናል።

f) devote his full working time to the institution;

g) refrain from imposing his political views and religious beliefs on his students during teaching-learning process;

h) treat and interact with members of the institution's community by refraining from acts that are contrary to rights enshrined in the Constitution;

i) perform other additional responsibilities that may be provided for by the senate statutes, establishing legislation, or memorandum of association of the institution;

j) without prejudice to the provisions of this Proclamation pertaining to joint appointment, devote his full energy, working time and attention to the institution.

2/ Academic staff who are medical and health professionals shall have also the responsibility to render health services in the institution's teaching hospital.

3/ Institutions shall draw up, through participation of the academic staff, and implement rules and procedures of discipline of academic staff which shall be consistent with the provisions of this Article and other relevant provisions of this Proclamation.

4/ Every institution shall formulate and implement the rules and procedures of discipline referred to in sub-article (3) of this Article within 300 days from the effective date of this Proclamation or, in case of a new institution, within 300 days from the date of its establishment.

## 33. <u>Employment Tenure and Extension of Retirement Age of Academic Staff</u>

1/ Tenured employment of academic staff shall constitute a privilege to be attained through meritorious continuous service and outstanding scholarly teaching and/or research or institutional leadership achievements as an incentive to encourage academics to continue to excel in their professions.

፪/ ቋሚ የሆነ የአካዳሚክ ሠራተኛ የሥራ ዋስትና ይኖረዋል፤ ቋሚ የሆነ የአካዳሚክ ሠራተኛ ከሥራው ሊባረር የሚችለው በመንግስት ተቋሙ የሴኔት ደንብ መሠረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የሚያሟላ ፕሮፌሰር ወይም ተባባሪ ፕሮፌሰር በጡረታ ከተገለለ በኋላም ማዕረጉን እንደያዘ እንዲቀጥል በተቋሙ የሴኔት ደንብ መሠረት ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በመንግሥታዊ ተቋም የሚያገለግል አካዳሚክ ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜን ለእያንዳንዱ ጊዜ በሶስት ዓመት የሚታሰብ ሆኖ ለሁለት ጊዜያት እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ) የአካዳሚክ ሠራተኛው የማስትሬት ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ኖሮት መልካም ጤንነት ያለውና ተከታታይና ውጤታማ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ፣

ለ) ተቋሙ በወቅቱና በወደፊት ፍላጎቱ ላይ ተመሥርቶ የጡረታ ዕድሜው መራዘሙ ተገቢ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ፣

ሐ) የአካዳሚክ ሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜው እንዲራዘምለት ፈቃደኛ ከሆነ፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ለማድረግ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፴፬. አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ ስለመቅጠር

፩/ አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ መቅጠር ተፈጻሚ የሚሆነው የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማረጋገጥ መልካም መፍትሄ ሆኖ ሲገኝ ወይም የአካዳሚክ ሠራተኛ እጥረትን ለመቅረፍ አስፈላጊ ሲሆን ነው፡፡ የጋራ ቅጥር ተግባራዊ ሲደረግ የማስተሬት ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለውን የአካዳሚክ ሠራተኛን የሚመለከት ሆኖ ከኢንዱስትሪ፣ ከንግድ፣ ከምርምር ማዕከሎች ወይም ከሌሎች ድርጅቶች በጋራ ቅጥር በተቋም ለመሰማራት የሚያበቃ ሙያዊ ዓቅም ያለው ባለሙያንም የሚመለከት ይሆናል፡፡

2/ A tenured academic staff shall have job security, and may not be dismissed from his position unless he has committed a serious breach of discipline as stipulated by the senate statutes of the public institution.

3/ Professors or associate professors who meet the requirements of sub-article (1) of this Article may, upon retirement, be given the rank and status of professor emeritus or associate professor emeritus in accordance with the provisions of the senate statutes of an institution.

4/ The retirement age of an academic staff of a public institution may be extended by the Ministry, for two consecutive sets of terms of three years each, where:

a) the staff holds a Master’s Degree or above, remains in good health and has a meritorious continuous service;

b) the institution reasonably justified, on the basis of actual and projected demand, the need to extend the retirement age;

c) the staff has freely consented to extension of the retirement age.

5/ The Ministry shall issue directives for the implementation of the provisions of this Article.

## 34. Joint Appointment

1/ Joint appointment of academic staff shall apply in circumstances when it shall prove an efficacious solution for an institution's challenge to ensure the relevance and quality of education as well as to meet demand of academic staff; and it shall be restricted in application to an institution's professionals with Master's degree and above and to professionals with high degree of relevant expertise from industry, business, research establishments and other organizations.

፪/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ አካዳሚክ ሠራተኛ ወይም የመንግሥት ሰራተኛ ዓቅሙ ካለው በራሱ ፈቃድና በተቋሙ ወይም በመሥሪያ ቤቱ ፈቃድ በጋራ ቅጥር ሊሰማራ ይችላል:: የሰው ሃይል እጥረት ባለባቸው አንዳንድ መስኮች፣ ተቋማትና መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች አካዳሚክ ሠራተኞችን ወይም የመንግሥት ሠራተኞችን በጋራ ለመቅጠር የመተባበር ግዴታ አለባቸው::

፫/ የቅጥሩ ሁኔታ፣ ቅጥሩ የሚቆይበት ጊዜ፣ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች፣ እንዲከናወኑ የሚፈለጉ ተግባራትና ጊዜን ማደላደል የመሳሰሉት ለተቀጣሪውና ለአሠሪዎቹ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች የሚመለከተው ሴኔት በሚያወጣው ደንብና ሥርዓት መሠረት በስምምነት ይወሰናሉ::

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የመንግስት ተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ ወይም ሌላ የመንግስት ሰራተኛ በግል ተቋም የጋራ ተቀጣሪ ሆኖ የመቀጠር መብት እንደሰጡ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም::

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መመሪያና የሥነ ሥርዓት ደንብ እንዲያወጡ የሚረዳ መመሪያን ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣል::

## ፴፭. <u>የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች</u>

፩/ የመንግሥት ተቋማት የቴክኒክና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑሰ አንቀፅ (፫) እና አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (በ) መሠረት ቦርድ በሚያወጣው ፖሊሲና መመሪያ መሠረት ይተዳደራሉ::

፪/ አካዳሚክ ባለሙያዎች ያልሆኑና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የተቀጠሩ የቴክኒክ ሠራተኞች የሚተዳደሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚወጡት ፖሊሲዎችና መመሪያ-ዎች ይሆናል፤ ሆኖም የደመወዝ ክፍያቸው በመንግስት የሕዝብ ጤና ጥበቃ ዘርፍ ለተመሳሳይ ባለሙያዎች ተፈጻሚ በሚሆነው መሠረት ይሆናል::

2/ Without prejudice to other provisions of this Proclamation and other applicable laws, an academic staff or a government employee, may be employed, with his consent and the consent of his institution or organization, on a joint appointment basis if he has the required capability to do so. Where there is scarcity of qualified experts in some fields, institutions and organizations shall co-operate with one another for the joint employment of an academic staff or a government employee.

3/ Issues of importance to the joint appointee and the concerned employers such as status, duration of appointment, remuneration and other benefits, the tasks to be achieved and the apportionment of working time shall be negotiated and agreed by the parties within the framework of rules and procedures enacted by the concerned senate.

4/ The provisions of this Article shall not be construed to entitle an academic staff of a public institution or a government employee to be jointly appointed in a private institution.

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (3) of this Article, the Ministry shall, within a year from the effective date of this Proclamation, issue a standard guideline to assist institutions develop their own rules and procedures.

## 35. <u>Administrative and Technical Support Staff</u>

1/ Administrative and technical support staff of public institutions shall be governed by policies and directives issued by the Board of the institution in accordance with sub-article (3) of Article 36 and sub-article (1)(j) of Article 44 of this Proclamation.

2/ Non-academic professionals and the technical staff employed in teaching hospitals shall also be governed by policies and directives issued under sub-article (1) of this Article; provided however, that their remuneration system shall be consistent with standards applicable to the public health sector.

፫/ መንግሥታዊ ተቋማት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸው ተፈላጊውን የብቃት ደረጃ ያላቸው መሆናቸውንና ቁጥራቸውም ከተፈላጊው ቁጥር ያልበለጠ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርባቸዋል::

፬/ መንግሥት በጀት ሲመድብ የመንግሥት ተቋማት ተፈላጊውን የአስተዳደና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቁጥር ብቻ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸውን መጠን መመደቡን ያረጋግጣል::

፭/ ማዕከሉ ከመንግስታዊ ተቋማት ጋር በመሆን የሚያስፈልገውን የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ትክክለኛ ቁጥር ለመወሰን የሚረዳ የምጣኔ መስፈርትን ይህ አዋጅ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣል::

፮/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎችን ተፈጻሚነት እንዲያግዝ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ተገቢ አደረጃጀትና ጥንቃቄ የተሞላው የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቅጥር አፈጻጸም እንዲኖረው የማድረግ ግዴታ አለበት::

፯/ የመንግስት ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተመለከተው የምጣኔ መስፈርት ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸው ምጣኔን ማስተካከል አለባቸው::

**፴፮. <u>የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መብትና ግዴታ</u>**

፩/ የመንግስት ተቋማት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች መሠረት መልካም አስተዳደርን የማግኘት መብት ይኖራቸዋል::

፪/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአስተዳደር ደንብና መመሪያን ከማውጣትና ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በአሳታፊ ሂደት ግንዛቤና መግባባት እንዲፈጠር የማድረግ ግዴታ አለበት::

፫/ የመንግሥት ተቋም ቦርድ አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች ላይ በመመስረትና የተቋሙን አቅም በማገናዘብ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አስተዳደር ዝርዝር መመሪያን ማውጣት ይችላል::

፬/ ማንኛውም የተቋም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ አግባብነት ላላቸው ሕጎችና የተቋሙ መመሪያዎች የመገዛትና በተግባርም የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች የማክበር ግዴታ አለበት::

3/ Public institutions shall ensure that their administrative and technical support staff meet the required level of competence and that they are not in excess of the optimum number.

4/ The government shall ensure that its budgetary appropriations to public institutions are made to meet only the optimum number of administrative and technical support staff.

5/ The Centre together with the public institutions shall, within one year from the effective date of this Proclamation, establish standard ratios that shall be applicable in determining the optimum number of administrative and technical support staff of a public institution.

6/ Every public institution shall ensure slim organization and frugal employment of support staff to conduce for the application of the provisions of sub-articles (3) and (4) of this Article.

7/ Public institutions shall adjust their staff ratios within one year from the effective date of the standard ratios to be established pursuant to sub-article (5) of this Article.

**36. <u>Rights and Responsibilities of Support Staff</u>**

1/ Support staff of public institutions shall be entitled to good governance in accordance with the applicable principles provided for by civil service law.

2/ Every institution shall formulate rules and procedures on all matters of importance to its support staff and have them validated through participatory processes before adoption.

3/ Based on the principles of the applicable civil service law, the Board of a public institution may issue detail rules regulating the administration of the institution's support staff.

4/ Any support staff of an institution shall have the responsibility to respect applicable laws and institutional directives as well as conform in his practice to the objectives of higher education and the guiding values of the institution as applicable.

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለተቋማት ተማሪዎች

### ፴፯. የተማሪዎች መብት

፩/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የማንኛውም ተቋም ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡-

ሀ) በመማርና በምርምር በነፃነት እውነትን የመፈለግና ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ፤

ለ) በመማሪያ ክፍል፣ በተቋም ግቢና በሕበረተሰብ ውስጥ ባጠቃላይ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፤

ሐ) በተቋም ግቢ ውስጥ ሕገ-መንግስታዊ ሰብአዊ መብታቸውና ደህንነታቸውን ተጠብቆ የመኖርና የግል ንብረታቸውን ደህንነትን የማስጠበቅ፤

መ) በተቋም ጉዳዮች ላይ በሕጋዊና ሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነፃነት የማራመድ፤

ሠ) ማንኛውም ዓይነት አድልዎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ሕጋዊ ከለላን የማግኘት፤

ረ) በማንኛውም የመምህርና ተማሪ ግንኙነት ገጽታዎች የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፤

ሰ) ስለ አካዳሚያዊ ብቃታቸው በዚህ አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በተቋሙ አከዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፤ ኢፍትሃዊ ምዘና ሲፈፀም ቅሬታን በተቋሙ ስርዓት መሰረት በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትህን የማግኘት፤

ሸ) ግልፅነት ባለው ስርዓት መሠረት በአከዳሚክ ሰራተኞች የስራ አፈፃፀምና በአካዳሚክ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ግምገማ ላይ የመሳተፍ፤

ቀ) በግል የትምህርት ማሕደር በቋሚነት የሚቀመጡ መረጃዎች በምስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለፁበት ሁኔታ የሚወስን የሚያስተማምን ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፤

## SECTION THREE
## STUDENTS OF INSTITUTIONS

### 37. Rights of Students

1/ Without prejudice to other provisions of this Proclamation and other applicable laws, students of any institution shall have the right to:

a) free inquiry of truth and freedom of expression of ideas and thoughts in the process of learning and conducting research;

b) enjoy the freedom to learn with appropriate opportunities and conditions in classrooms, campuses and in the larger community;

c) protection of their constitutional human rights, personal safety, and security of their personal property on campus;

d) be free to express orderly their views on issues of institutional policy;

e) receive protection from any form of discrimination or harassment;

f) be entitled to equitable and fair treatment in all respects of the teacher-student relationship and to an environment conducive to stimulate learning;

g) be evaluated solely on academic basis consistent with norms provided for by this Proclamation and the institution's academic standards, and receive redress against capricious evaluation;

h) participate in a transparent system of performance evaluation of academic staff and academic programmes;

i) enjoy the benefits of a carefully considered policy of confidentiality regarding the information that should be part of their permanent educational record and as to the conditions of its disclosure;

በ) የተማሪው የጋራ ጥቅሞችን በሕጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብ-ነት ባላቸው ሕጐች በተቋቋመና የተቋ-ሙን ተማሪዎች በአባልነት በሚያቅፍ የተቋሙ የተማሪዎች ማሕበር አባል የመሆን፤

ተ) በተቋሙ ደንብና ስርዓት መሠረት በማሕበራቸው አማካይነት በተቋሙ መገልገያዎች የመጠቀም፤

ቸ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና የተቋም ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በማሕበራቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካይነት ተቋሙን በሚያስተዳድሩት አካላት ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤

ኀ) የሚያስከትሏቸው ግዴታዎች እንደተ-ጠበቁ ሆነው በማሕበራቸው አመራር ስር ዜና፣ አስተያየትና ርእሰ አንቀፆ-ችን ጨምሮ ሃሳብን በነፃ ለማንሸራሸር በተቋም ውስጥ የመገናኛ ሚዲያን የመጠቀም፤

ነ) በዚህ አዋጅ መሰረት የወጪ መጋራት ስርዓት ተጠቃሚ የመሆንና የምክር አገልግሎትን የማግኘት።

፪/ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ የተመለ-ከተውን የተማሪዎች መብት ማስከበሪያ የሚሆን መመሪያን የመቅረፅና የመተግበር ግዴታ አለበት፤ መመሪያው በዚህ አዋጅ መሠረት የተቀረፀና የአካዳሚክ ማሕበረ ሰቡን ባሳተፈ ሂደት መግባባት የተደረሰበት መሆን ይኖርበታል።

## ፴፰. የተቋም ተማሪዎች ግዴታ

፩/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባ-ብነት ያላቸው ሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የተቋም ተማሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

ሀ) በክፍል የመገኘትና ትምህርቱን በሚገባ የመከታተል፤ የማንኛውም አካዳሚክ ሰራተኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣንን የማክበር፤

ለ) በተመዘገበበት ትምህርት የተቀመጡ የብቃት መመዘኛዎችን የማሟላት፤

ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የተ-ቋሙን መሪ እሴቶች የማወቅና የማራመድ፤

መ) በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋሙ ግቢ ውስጥ በሕግ የተጠበቀውን የሌሎች ሰዎችን መብት የማክበር፤

j) join the institution's student union, which shall be founded on the principle of universality of membership in accordance with the pertinent laws so as to promote and protect lawfully their common interests;

k) obtain access to facilities of the institution through their union in accordance with the rules and procedures of the institution;

l) participate, through their union or representatives, in the sessions of the institution's governing bodies in accordance with this Proclamation and directives issued by the Board;

m) use, under the leadership and guidance of the student union and with the attendant responsibilities, communications media on campus to provide a forum for the free exchange of ideas and to present news, opinion and editorial comments;

n) benefit from the cost-sharing system and receive guidance and counseling services in accordance with this Proclamation.

2/ Every institution shall have the responsibility to develop and implement rules and procedures that shall safeguard the rights of students stipulated under this Article. The rules and procedures shall be developed in accordance with this Proclamation and on the basis of consensus built through the participation of the academic community.

## 38. Responsibilities of Students

1/ Without prejudice to other provisions of this Proclamation and other applicable laws, any student of an institution shall have the responsibilities to:

a) attend classes properly and respect the indivisible authority of any academic staff in the leadership and management of the teaching-learning process;

b) maintain standards of academic performance established for each course in which he is enrolled;

c) know and uphold the objectives of higher education and the guiding values of the institution;

d) respect, in classroom or anywhere in the premises of the institution, the rights of other persons protected by law;

ሠ) አግባብነት ያላቸው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን እንደዚሁም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረቱትን የተቋሙ መመሪያዎችና ደንቦችን የማክበር፤

ረ) ከተቋሙ አካዳሚክና ሌሎች ሠራተኞች እንዲሁም ከማንኛውም የተቋሙ ተማሪ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ-መንግሥታዊ መብቶቻቸውን የማክበር፤

ሰ) ከማንኛውም ሕገወጥ ድርጊት እና ከማንኛውም ከሥነምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፤

ሸ) የግልም ሆነ የጋራ የተማሪ ጥቅሞች አደጋ ላይ በሚወድቁበት ጊዜ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ቅሬታን በማሰማት መፍትሔን የመሻት፤

ቀ) የተቋሙን ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም፤ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በተቋሙ ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂ የመሆን፤

በ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተቋሙ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም።

፪/ ማንኛውም ተቋም የተማሪዎችን የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ተገቢ ሥርዓት የማውጣት ግዴታ አለበት።

## ፴፱. የተማሪዎች ቅበላ

፩/ በማንኛውም ተቋም በቅድመ ምረቃ ትምህርት ለመመዝገብ የሚችሉ ተማሪዎች የመሰናዶ ትምህርትን ያጠናቀቁና የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናን ያለፉ መሆን ይኖርባቸዋል፤ በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በሚኒስቴሩ የአቻ ግምት የተሰጣቸው ተማሪዎችም የመመዝገብ ዕድሉን ሊያገኙ ይችላሉ።

፪/ የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናውን የሚያስተዳድረውና የቅበላ መስፈርቱን የሚወስነው ሚኒስቴሩ ይሆናል።

፫/ የዚህ አንቀጽና የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም የሚከተሉትን ተማሪዎች ይቀበላል፦

e) observe scrupulously the applicable provisions of this Proclamation and the rules of the institution which are consistent with this Proclamation;

f) interact with academic and other staff and any other student of the institution with due respect to their constitutional rights;

g) refrain from any unlawful act and from any unethical activities;

h) remonstrate and seek redress peacefully and through legal avenues in the event student interests, be it individual or collective, are at stake, and exhaust all institutional avenues of redress;

i) use and handle the properties of the institution with due care and be held accountable for any damage caused to the property of the institution due to intentional or negligent misuse or destruction;

j) effect payment of fees applicable in accordance with the provisions of this Proclamation for services that has been provided by the institution.

2/ Every institution shall have the duty to adopt a code of conduct governing students' behavior and appropriate disciplinary procedures.

## 39. Admissions of Students

1/ Admissions to undergraduate programmes of any institution shall be based on completion of the preparatory programme and obtaining the necessary pass marks in the university entrance examination. Admissions may also be granted to students completed their secondary school in foreign countries on the basis of equivalent academic achievements that shall be determined by the Ministry.

2/ The Ministry shall administer the university entrance examination and decide on eligibility for admissions to any institution.

3/ Without prejudice to other provisions of this Article, other provisions of this Proclamation and other applicable laws, every institution shall, with respect to student admissions, have the rights and responsibilities to admit:

ሀ) በቅድመ ምረቃ ፕሮግራሙ የመሰናዶ ትምህርትን አጠናቀው የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናን ያለፉና በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በሚኒስቴሩ የአቻ ግምት የተሰጣቸውን፤

ለ) ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት የቅደመ-ምረቃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና ተቋሙ ያስቀመጠውን መግቢያ የቅ-ድመ-ምረቃ ውጤት ያላቸውን፤ ወይም ለሶስተኛ ዲግሪ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁና ተቋሙ ያስቀመጠ ውን መግቢያ አካዳሚክ ውጤት ያላቸውን፣

ሐ) ብቃትን መሠረት አድርጎ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተቋሙ የሚያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተናን ያለፉ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ምሩቃንን::

፬/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና ንዑስ አንቀፅ (፫) ተራ ፊደል (ሀ) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ልዩ ድጋፍን ማግኘት ስለሚገባቸው ዜጎች እና የቅበላ ሥነ-ሥርዓቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ሆኖ ሚኒስቴሩ ደንቡን ለማስፈጸም በሚያወ ጣው መመሪያ መሰረት ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

፭) ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ የመቋቋሚያ ሕግ መሠረት በወጣ ልዩ የቅበላ ሥርዓትና የተቋሙ ሴኔት በሚወ ስነው አገባብ መሠረት ዓቅሙ ያላቸው ጎልማሶችን በቅድመ ምረቃ ተማሪነት ሊቀበል ይችላል፤ ሚኒስቴሩ ይህን የቅበላ ስርዓት በግል ተቋማትም ሁኔታው ሲፈቅድ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል።

፮/ የተማከለ የተማሪዎች ምደባ እስከቀጠለ ድረስ ሚኒስቴሩ ተማሪዎችን የሚመድበው የመንግሥት ተቋማትን በማማከር ይሆ-ናል፤ የመንግሥት ተቋማት ራሳቸው በቀጥታ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚች-ሉበት ጊዜ ሲደርስና ተግባራዊ መደረጉም ሲታመንበት ሚኒስቴሩ የመግቢያ ፈተና-ውን በማስተዳደር፣ የማለፊያ ነጥብንና መግቢያ ነጥብን በመወሰን፣ ስለ ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚዎች መመሪያን በማው-ጣት፣ የቅበላ ስርዓትን በመወሰን እና የቅበላው አፈፃፀምን በመከታ- ተልና በማስተካከል ላይ የተገደበ ይሆናል::

a) for undergraduate studies, graduates of preparatory schools who pass the university entrance examination and graduates of foreign country secondary school systems with equivalent level as determined by the Ministry;

b) for second degree-level graduate studies, candidates who have completed their undergraduate studies with the academic results required by the institution; or, for doctoral programmes, candidates who have second-level degrees and the academic results required by the institution;

c) technical and vocational education and training graduates with pertinent qualifications and who satisfy entrance qualifications assessment set by the institution, with the right to participate in the assessment being limited to those who qualify on the basis of merit-based directives to be issued by the Ministry.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-articles (1) and (3)(a) of this Article there shall be special admissions procedures for disadvantaged citizens to be determined by regulation of the Council of Ministers and to be implemented by directive of the Ministry issued hereunder.

5/ A public institution may admit adults under special admissions procedures to be issued pursuant to the establishment regulations of the institution and as the institution's senate may determine; and the Ministry may extend the applicability of this provision to private institutions as circumstances may permit.

6) The Ministry shall consult the public institutions concerning student placement so long as the current centralized placement of students in public institutions shall continue. As and when direct selection of students for admission by public institutions becomes feasible and desirable, the Ministry shall limit itself to administering the entrance exam, deciding on pass marks and eligibility for admission, including entitlement to affirmative action, monitoring the admission process and ensuring compliance by institutions to its directives.

## ፵. ስለ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች

፩/ ተቋማት አገልግሎት መስጫ አውታሮቻ- ቸውና ፕሮግራሞቻቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሆነው እንዲታነጹ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

፪/ ሁኔታና ዓቅም በፈቀደ መጠን ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎቻቸው ጥቅም ሲሉ የክፍሎ- ቻቸውን አጠቃቀምና አመዳደብ መለወጥ፣ አማራጭ የፈተና ሥርዓቶችን መቀየስና የትምህርት ሂደቱን የሚያመቻቹ ዜዴዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል::

፫/ የተቋሞች ሕንፃዎች ዲዛይን፣ የግቢዎቻቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ኮምፒውተሮቻቸውና ሌሎች የመገልገያ አውታሮቻቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጐት ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል::

፬/ አስፈላጊ ሲሆንና አቅም በፈቀደ መጠን ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎቻቸው የቱቶሪያል፣ የፈተና ጊዜያት መራዘምና የማስረከቢያ ጊዜያት መራዘምን ጨምሮ ልዩ አካዳሚክ ዕርዳታዎች ሊያደርጉላቸው ይገባል::

## ፵፩. የመማር-ማስተማር ጥራትና የተማሪዎች ምዘና

፩/ በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት የትምህርቱ አሰጣጥ በየትኛውም መልኩ ቢሆን አሳታፊ ሆኖ ተማሪን ያማከለና በንቃት መማርን የሚያራምድ መሆን ይኖርበታል::

፪/ በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታ በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋሙ ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረ- ታታ መልካም ድባብ ያለው መሆን ይኖርበታል::

፫/ የትምህርቱ አቀራረጽና አሰጣጥ የተማሪዎ ችን ዕውቀትና ክህሎት የሚያበለጽግ፣ መልካም እሴቶችን የሚያስታጥቅና በተማ- ሪዎች አመለካከት ላይ አውንታዊ ለውጥና እድገት የሚያመጣ መሆን ይኖርበታል::

፬/ ተማሪዎች የሚመዘኑት በመዛኝነቱ አግባ ብነት ባለው ስርዓትና በተማሩት ላይ ተመሥርቶ መሆን ይኖርበታል፤ የምዘና ውጤት አሰጣጥ ስርዓትም የተረጋገጠውን ዓቅም የሚገልፅ ይሆናል::

፭/ በተቋም ደረጃ ዕውቅና የተሰጠውና በእያን ዳንዱ የትምህርት ክፍል እንደአግባቡ በማጣጣም የሚሠራበት እና እያንዳንዱ የአካዳሚክ ሠራተኛ ሊያከብረው የሚገባ ተማሪዎችም አስቀድመው የሚያውቁት የተማሪዎች ምዘናና ፈተና ስርዓት ይኖራል::

## 40. Physically Challenged Students

1/ Institutions shall make, to the extent possible, their facilities and programmes amenable to use with relative ease by physically challenged students.

2/ Institutions shall, to the extent that situations and resources permit, relocate classes, develop alternative testing procedures, and provide different educational auxiliary aids in the interest of students with physical challenges.

3/ Building designs, campus physical landscape, computers and other infrastructures of institutions shall take into account the interests of physically challenged students.

4/ Institutions shall ensure that students with physical challenges get to the extent necessary and feasible academic assistance, including tutorial sessions, exam time extensions and deadline extensions.

## 41. Quality of Teaching-Learning and Assessment of Students

1/ The teaching and learning process in any institution shall be, whatever the methods of delivery employed, interactively student-centered that shall promote active learning.

2/ The teaching and learning conditions in any institution shall, as far as practicable, create in-class and on-campus enabling environment and encouraging atmosphere for students to learn.

3/ The designing of courses and their delivery shall be such that the courses shall add to the knowledge and skills students already have, cultivate constructive professional values, and bring about attitudinal changes and development in students at the end of the courses.

4/ Students shall be assessed properly and fairly on the basis of their learning experience; the marking system shall be reflective of the competences achieved by students.

5/ There shall be institutionally recognized and well-defined student assessment and examination methods and systems at academic unit levels to which any academic staff shall adhere, and have been made known to students.

፮/ በተማሪዎች ምዘናና የምዘና ውጤት ደረጃ አሰጣጥ ረገድ አመራር የሚሰጡ በተገቢ የትምህርት ክፍሎች ደረጃ ብቁ አካላት እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት ይኖራል።

፯/ ምዘናና የምዘና ውጤቶችን አስመልክተው ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች በተቋምና በአካዳሚክ ክፍሎች ደረጃ ተገቢው ትኩረት ተሠጥቷቸው በጥንቃቄና በአፋጣኝ መታየት ይኖርባቸዋል።

፰/ አካዳሚክ ሠራተኞች በተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥ የሥራ ላይ ሙያዊ የንድፈ-ሃሳብና የክህሎት ሥልጠና ይሰጣቸዋል፤ የማስተማር ብቃትና የምዘና ክህሎቶችን ጠንቅቆ ማወቅ በአካዳሚክ ሰራተኛነት ለመቀጠልና ዕድገትን ለማግኘት እንደ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ይወሰዳሉ።

፱/ በተማሪዎች በኩል ምንጭ ሳይጠቅሱ የሌላ ሰው ሥራና ሐሳብን እንደ የራስ ሥራና ሐሳብ ተጠቅሞ የቤት ወይም የምርምር ሥራ መሥራትም ሆነ በፈተናዎች ላይ ማጭበርበር፣ በአካዳሚክ ሠራተኞች በኩል ደግሞ በፈተናዎች አስተዳደር፣ በቤት ሥራዎችና በፈተናዎች እርማት እንዲሁም በውጤት አሠጣጥ ላይ በዝምድና ወይም ለማጥቃት ብሎ መሥራት ከባድ ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ የዲስፕሊን ጥፋቶች ተደርገው ይወሰዳሉ።

፲/ የማስተማር ዘዴዎች፣ የተማሪዎች ምዘና፣ የምዘና ውጤቶችና ደረጃ አሰጣጥን የሚመለከቱ ሥነ-ሥርዓቶች በተቋሙ የሴኔት ደንብ ውስጥ መካተትና በትምህርት ክፍሎች መመሪያዎች ተብራርተው መገለጽ ይኖርባቸዋል።

**<u>ክፍል ሶስት</u>**
**<u>የመንግስት ተቋማት</u>**

**<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>**
**<u>አስተዳደርና ውስጣዊ አደረጃጀት</u>**

**፵፪. <u>የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ተቋም፡-

ሀ) የአመራርና አማካሪ አካላት፣

ለ) የአካዳሚክ ክፍሎች፣

ሐ) እንደአግባቡ የመማሪያ ሆስፒታል አመራር፣

ሐ) የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች፣

6/ There shall be adequate structures, at the necessary levels of the pertinent academic units, which shall constitute leading authorities at any of the levels on student assessments, examinations and grading of results.

7/ Student complaints against assessment methods, examinations, grading systems or results thereof shall be handled, at institutional level, with due care and expeditiously.

8/ Academic staff shall receive on-job and tailor-made professional training on student assessment theories and skills; and mastery and successful application of assessment skills as well as teaching shall constitute critical prerequisites for continuity of employment and promotions.

9/ Plagiarism and cheating by students in assignments and examinations and nepotism or vengeance by academic staff in administration of examinations, correction of examinations and assignments, and in determining grades shall constitute breaches of discipline warranting severe penalties.

10/ Rules and procedures governing teaching methods and assessment, grading and academic status of students shall be provided in the senate statutes of each institution and shall be further elaborated in guidelines issued by the appropriate academic units.

**<u>PART THREE</u>**
**<u>PUBLIC INSTITUTIONS</u>**

**<u>SECTION ONE</u>**
**<u>GOVERNANCE AND INTERNAL STRUCTURES</u>**

**42. <u>Organization of Public Institutions</u>**

1/ Without prejudice to other provisions of this Proclamation, any public institution shall have:

a) governing and advisory bodies.

b) academic units;

c) governing body of teaching hospital, as may be relevant;

d) administrative and technical support units;

መ) ቢሮዎችና ተግባራቱን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችሉት ሌሎች መገልገያዎች፣

ይኖሩታል::

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የአካዳሚክ ክፍሎችን ለመመስረት ሲወሰን ከትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ ከተብብር አሰራላጊነትና ከውጤታማ የሀብት አጠቃቀም አኳያ እየታየ መሆን ይኖርበታል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተቋቋመ የትምህርት ክፍል በፕሬዚዳንቱ ተዘጋጅቶና በአስተዳደር ካውንስል፣ በዩኒቨርስቲ ካውንስልና በሴኔት የተመከረበትና በቦርዱ የፀደቀ የአስተዳደር ሥርአት ይኖረዋል:: የአስተዳደር ሥርዓቱም የአመራርና የአስፈፃሚ አካላትን የያዘና ኃላፊነታቸውን እንዲሁም የአመራርና የአስተዳደር ሥነ-ሥርአቶችን ያካተተ ይሆናል::

፬/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም በቦርዱ የማፀደቅና በሚኒስቴሩም የማስፈቀድ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ በአለም አቀፍ መልካም ልምድ ላይ ተመሥርቶ ተልእኮውን ለማሳካት የሚያስችል የተሻለ ውጤታማ ሥራ ለመስራት ብቻ በማሰብ አደረጃጀቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀየር እራሱን እንደገና ሊያደራጅ ይችላል::

፭/ ሚኒስቴሩ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም መመሪያ ካልሰጠ በስተቀር፣ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት እራሱን እንደገና ለማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተቋሙ ፕሬዚዳንት በአስተዳደር ካውንስል፣ በዩኒቨርሲቲ ካውንስል፣ በሴኔትና በተቋሙ የመምህራንና የተማሪዎች ማሕበራት የተመከረበት የተሟላ የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ ያቀርባል::

## ፵፫. የአመራርና አማካሪ አካላት

፩/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት የአመራርና አማካሪ አካላት ይኖሩታል:-

ሀ) ቦርድ፤

ለ) ፕሬዚዳንት፤

ሐ) ሴኔት፤

መ) የአስተዳደር ካውንስል፤

ሠ) የዩኒቨርሲቲ ካውንስል፤

ረ) የትምህርት ክፍል ካውንስል፤

e) office and other facilities necessary for undertaking properly its activities.

2/ The establishment of academic units in accordance with this Proclamation shall be determined on the basis of relevance and quality of education and research as well as on cooperative, efficient and effective use of resources.

3/ Any academic unit of an institution established pursuant to sub-article (2) of this Article shall have a system of governance that shall be devised by the president, debated by the managing council, the university council and the senate, and approved by the Board. Such system shall consist of governing and managing bodies, their responsibilities, and rules and procedures of leadership and management.

4/ Notwithstanding other provisions of this Proclamation, a public institution may reorganize itself, in part or in full, differently in accordance with international good practice, with the sole purpose of more effective performance in the fulfillment of its mission and subject to approval by the Board and endorsement by the Ministry.

5/ Except as may be directed otherwise by the Ministry, in the event any public institution finds it necessary to reorganize itself as provided in sub-article (4) of this Article, the president shall submit to the Board an exhaustive proposal discussed by the managing council, the university council, the senate, and by unions of students and teachers of the institution.

## 43. Governing and Advisory Bodies

1/ Governing and advisory bodies of a public institution shall consist of:

a) board;

b) president;

c) senate;

d) managing council;

e) university council;

f) academic unit council;

ሰ) የትምህርት ክፍል አስተዳደር ካውንስል፤

ሸ) የዲፓርትመንት ጉባኤ፤

ቀ) በቦርዱ ወይም በሴኔቱ ወይም በዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ የሚቋቋሙ አስፈላጊ ቋሚና ጊዜያዊ ... አማካሪ ወይም ልዩ ኮሚቴዎች ወይም ካውንስሎች::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት ተቋም የአመራርና የአማካሪ አካላት አደረጃጀትና ስያሜዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬) እና (፭) መሠረት ፕሬዚዳንቱ በሚሰጠው ምክር ላይ ተመሥርቶ ቦርዱ ሊለውጣቸው ይችላል::

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተራ ፊደል (ረ) እስከ (ሸ) የተመለከቱት የትምህርት ክፍሎች አመራር አካላት ይዘት፣ አመሰራረት፣ ሃላፊነትና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፵፪ (፫) መሰረት ይወሰናል::

## ፵፬. የቦርድ ኃላፊነት

፩/ የመንግሥታዊ ተቋም ቦርድ የተቋሙ የበላይ አመራር ሆኖ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ) ተቋሙ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች መተግበሩንና በተቋሙ ውስጥ መል ካም አስተዳደር መስፈኑን መከታተልና ማረጋገጥ፤

ለ) የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተቋሙ እቅድ፣ በጀት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ አደረጃ-ጀት፣ የአስተዳደርና አሰራር ሥርዓት፣ የውስጥ ደንብና የአካዳሚክ ፕሮግ-ራሞችን በሚመለከት የሚቀርቡለት ሃሳቦችን መርምሮ ማፅደቅና ተግባራ-ዊነታቸውን መከታተል፤

ሐ) በፕሬዚዳንቱ በሚቀርብ ሃሳብ ላይ በመመ-ሥረት ምክትል ፕሬዚዳንቶችና ሌሎች አካዳሚክ ሃላፊዎች እንዲሁም የሴኔት አባ- ላት እንዳግባቡ የሚታጩበት፣ የሚሾሙ- በት ወይም የሚመደቡበትና የሚመረጡ- በትን ሥርዓትና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣት እና በትክክል መተግበራቸውንም መከታተል፤

መ) ፕሬዚዳንታዊ እጩን ለሹመት እንደአ ግባብነቱ ለሚኒስትሩ ወይም ለክልሉ አካል ማቅረብ እና ፕሬዚዳንቱ በሚያቀ ርበው መሠረት ምክትል ፕሬዚዳን-ቶችን መሾም፤

g) academic unit managing council;

h) department assembly;

i) advisory or specialized committees or councils that may be established by the board, senate or university council.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the structures and nomenclature of governing and advisory bodies of a public institution may be modified by its board upon advice by the president in accordance with sub-articles (3), (4), and (5) of Article 42 of this Proclamation.

3/ The composition, constitution, responsibilities, and decision-making process of governing bodies of academic units under paragraphs (f) to (h) of sub-article (1) of this Article shall be determined in accordance with Article 42(3) of this Proclamation.

## 44. Responsibilities of the Board

1/ The board of a public institution shall be the supreme governing body of the institution and it shall have the responsibilities to:

a) supervise and ensure that the institution implements the provisions of this Proclamation and that good governance prevails in the institution;

b) without prejudice to other provisions of this Proclamation, examine, approve and follow up the implementation of proposals of institutional reorganization, organizational plans, policies, administration and academic programmes and internal regulations of the institution;

c) issue directives, upon the advice of the president, regarding qualification requirements and procedures of nomination and appointment procedures and terms of office of the vice presidents and other academic officers as well as members of the senate; and monitor the propriety of implementation of the same;

d) nominate the president for appointment as may be appropriateby the Ministry or the state body and appoint the vice presidents on the basis of nominations made by the president;

ሠ) አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ምክትል ፕሬዚዳንት ኃላፊነቱን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሳየ ከሃላፊነት ማሰናበትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ መውስድ፤ ፕሬዚዳንቱን የሚመለከት ሲሆን ደግሞ ሚኒስትሩን በማማከር እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤

ረ) የተቋሙን ኦዲተሮች መሾምና ክፍያቸ ውን መወሰን፤

ሰ) የተቋሙን የስትራቴጂክ እቅድ፣ አመ ታዊ እቅድና በጀት ማቅረብና ሲፀድ- ቁም ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፤ የተቋሙን የክንውን ሪፖርትና የፋይ ናንስ መግለጫን ማፅደቅና ማቅረብ፤

ሸ) ተቋሙ የዋና ዋናና የጥቃቅን ገቢዎቹን ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ መያዙንና ወጪዎቹ በበጀቱ መሠረት መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፤

ቀ) የተቋሙ ሌሎች የአመራር አካላት ከባድ የሕግ መጣስ ተግባር በሚፈፅሙበት ጊዜ ወይም ከባድ የሆነ የገንዘብ ብክነት ስለመከ ሰቱ ጥርጣሬ ካለ ወይም በርግጥ ተከስቶ ከሆነ በራሱ ስልጣን ክልል ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ መውሰድና ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ፤

በ) በፌደራል መንግስት የሰራተኞች አዋጅና ደንቦች መሠረታዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቅጥር፣ እድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን የሚመለከት ፖሊሲን እንዳስፈላጊነቱ እንዲዘጋጅ ማድረግና ማፅደቅ፤

ተ) ተቋሙን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት እና ለሚኒስቴሩ የሚያስፈልግ ከሆነም ሪፖርት ማድረግ፤

ቸ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤ ለከፍተኛ ትምህርት ዕድገት በሚጠቅሙ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ በአጠቃላይና የተቋም አስተዳደር ላይ በተለይ በተቋም መሪነቱ ከሚያስተውለው ወይም ከሚያውቀው በመነሳት ለሚኒስቴሩ ምክር መስጠት፤

ኀ) በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት፤

ነ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ኀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ ቅሬታዎችን በተፋጠነ መንገድ ተቀ- ብሎ የሚፈታበት የተሟላ ተቋማዊ ሥርአት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

e) take, without prejudice to the applicability of other relevant laws, any disciplinary action, including removal from office, against any vice president in the event of serious failure to discharge his responsibility; in the case of the president, consult with the Ministry for measures to be taken;

f) appoint auditors of the institution and determine their remunerations;

g) review and submit strategic plans, annual plans and budgets of the institution and supervise their implementation up on approval; approve and submit performance reports and financial statements of the institution;

h) monitor and ensure that the institution keeps proper books of accounts of all its mainstream and sundry incomes and that all expenditures are as budgeted;

i) take remedial measures within its own competence and report promptly to the Ministry in the event of serious breaches of the law by the institution's other governing bodies or in the event the danger of serious financial loss is suspected or has actually happened;

j) cause, as necessary, the formulation of and approve policies regarding employment, promotion, discipline, salary, allowances, and other benefits for the administrative and technical support staff of the public institution on the basis of the basic principles of the federal civil service laws;

k) request and obtain information on matters concerning the institution and report the same if particularly important to the Ministry;

l) submit proposal as may be necessary to the Ministry for the amendment of the law establishing the public institution as well as advise it on all matters of importance to higher education and research generally and for institution governance particularly as perceived from its position as board of an institution;

m) examine and give final decision on grievances against decision by the public institution;

n) monitor, without prejudice to the provisions of paragraph (m) of this sub-article, that the institution has an adequate institutional system to expeditiously receive and redress grievances;

ኘ) የተቋሙን፣ የተቋሙን አካዳሚክ ክፍሎች፣ የመሪዎቹንና የአስተዳደር አካላቱን የስራ አፈፃፀም በፕሬዚዳንቱ ሪፖርት መሰረት ከእቅድ አኳያ መገምገም፤

አ) የሴኔት ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው የአካዳሚክ ሕጎች መፈፀማቸውን መከታተል፤

ከ) በኘሬዚዳንቱ ወይም በሴኔት የተላለፉ ውሳኔዎች የተቋሙን ተልእኮ የሚጎዱ ወይም የመንግስትን ፖሊሲ፣ ይህንን አዋጅ ወይም ሕገ-መንግስቱን የሚቃረኑ ሆነው ሲገኙ ውሳኔዎቹን መሻር፤

ኸ) የራሱን የአሰራር ሥነሥርዓትና የውስጥ አስተዳደር ደንብና አባላቱን የሚመለከት የዲሲፕሊን ደንብን ማውጣት፤

ወ) የኘሮፌሰርነት የማዕረግ ዕድገትን ማፅደቅ፤

ዐ) ከኘሬዚዳንቱ በሚቀርብ ምክር ላይ ተመሥርቶ ተቋሙ ለትምህርት የሚያስከፍላቸውን የተለያዩ ክፍያዎች አይነትና መጠን እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት በወሰነው መሠረት የተቋሙን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተከፋይ አበሎችን፣ የትርፍ ስዓት ክፍያዎችንና የመሳሰሉትን መወሰን፤

ዘ) የሴኔቱን፣ የአስተዳደር ካውንስሉንና የዩኒቨርሲቲ ካውንስሉን በትክክል መደራጀትና መሥራት መከታተል፤ አስፈላጊነቱን ሲያምንበትና በኘሬዳንቱ ምክር ላይ በመመሥረት ተጠሪነቱ ለኘሬዚዳንቱ ወይም ለዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ የሆኑ ልዩ አማካሪ አካላትን ማቋቋም፤

ዠ) በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የተሰጠው ሌላ ኃላፊነትን መወጣትና ይህን አዋጅ ማክበርና ተቋሙም እንዲያከብረው ማድረግ::

፪/ የቦርዱ ተጠሪነት እንዳግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም ለተገቢው የክልል መንግስት አካል ይሆናል::

፫/ የፌደራል መንግስት ተቋም የቦርድ ሰብሳቢ በሚኒስትሩ የሚሾም ሆኖ ቦርዱ የተሰጠውን ሃላፊነት በትክክል መወጣቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት::

፬/ የፌደራል መንግስት ተቋም ቦርድ አባላት ጥቅማ ጥቅሞች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑና በተቋሙ የሚሸፈኑ ሆኖ የተቋሙን ዓቅም ግምት ውስጥ ያስገቡ ይሆናሉ::

o) conduct, on the basis of the president's report, performance evaluations of the institution, of its constituents, and of its leaders and governing bodies against plans;

p) monitor the implementation of senate legislations and decisions;

q) rescind decisions made by the president or the senate when the decisions compromise institutional mission or contravene government policy, this Proclamation, or the Constitution;

r) issue its own rules of procedure and internal regulations, as well as rules of discipline applicable to its members;

s) approve promotions to the rank of professorship;

t) determine upon advice by the president the type and amount of different payments relating to education charged by the public institution and, on the basis of decisions by the Council of Ministers, decide on payable allowances, overload rates and other similar sundry rates.

u) oversee the proper constitution and functioning of the senate, university council, and the managing council; and establish, as it may consider necessary and upon the advice of the president, any particular advisory council accountable to the president or to the university council;

v) carry out such other responsibilities as provided for by other provisions of this Proclamation and by the establishing law of the public institution and respect and cause the respection of this Proclamation by the institution..

2/ The board shall be accountable to the Ministry or, in case of an institution under a state, to the appropriate organ of the state government.

3/ The board's chairperson of a federal public institution shall be appointed by the Minister; and shall have the responsibility to ensure that the board discharges effectively its responsibilities.

4/ Benefits due to the members of board of a federal public institution shall be determined by the Ministry, with due regard to the ability of the institution, and covered by the institution.

## ፵፭. ስለቦርዱ አባላትና ምልአተ ጉባኤ

፩/ ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮና ዓቅምን መሰረት ያደረገ የሴቶች ተሳትፎ ያለበት ሰባት ድምፅ መስጠት የሚችሉ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪/ ሚኒስትሩ ከቦርዱ ሰበሳቢ በተጨማሪ ሶስት ድምፅ መስጠት የሚችሉ የቦርድ አባላትን መርጦ ይሾማል፡፡

፫/ ፕሬዚዳንቱ ከአስተዳደር ካውንስሉና ከሴኔቱ ጋር በመመካከር ሌሎች ሶስት እጩዎችን በሚኒስትሩ እንዲሾሙ ያቀርባል፡፡

፬/ የተቋሙ ፕሬዚዳንት ድምፅ የማይሰጥ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የሚሾሙት የቦርድ አባላት በኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉ ወይም ያገለገሉና በተለይ በማስተማር ወይም በምርምርና በግል ስብዕናቸው የታወቁ ግለሰቦች፣ ወይም እውቀታቸው፣ ልምዳቸውና አትኩሮታቸው ለከፍተኛ ትምህርት አላማዎች በአጠቃላይና ለተቋሙ ተልእኮዎች መሳካት በተለይ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችላቸው የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ተወካዮች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፮/ ቦርዱ በራሱ ውሳኔ ማንኛውንም ሰው በአስረጂነት በስብሰባዎቹ ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

፯/ አምስት ድምፅ የሚሰጡ የቦርዱ አባላት ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ ሆኖም አምስት የቦርድ አባላት መሳተፍ የማይችሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ከተፈጠረ ቦርዱ በአራት አባላት ምልአተ ጉባኤ ስብሰባዎቹን ያካሄዳል፡፡ ቦርዱ ይህንን ሁኔታ በተመለከተ በአሰራር ሥነ-ሥርዓት ደንቡ ላይ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

፰/ የቦርዱ ሰብሳቢ ጊዜ በተቆረጠለት ስብሰባ ላይ መሳተፍ የማይችል ከሆነ በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላት ያንን ስብሰባ የሚመራ ሰብሳቢ ከመካከላቸው በመምረጥ የስብሰ ባውን አጀንዳ ይፈጽማሉ፡፡

፱/ ቦርዱ በጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚያሳልፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡

## ፵፮. ስለቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ በአመት ከሦስት እስከ አራት የሚሆኑ መደበኛ ስብሰባዎችን ያደርጋል፤ ቦርዱ ባጠቃላይ ሃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችልና በተለይ የእቅድና የበጀት ዝግጅቶች እንዲሁም አፈጻጸም ላይ አስተዋፅኦ ለማድረግ እንዲችል መደበኛ ስብሰባዎቹ አመቺ በሆኑ ወቅቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡

## 45. Composition and Quorum of the Board

1/ The board shall be composed of seven voting members, including the chairperson; and selection of members shall give due regard to merit-based gender balance.

2/ The Minister shall select and appoint the board chairperson and three additional voting members to the board.

3/ The president, in consultation with the university council and the senate, shall nominate three other voting members of the board and submit their list for appointment to the Minister.

4/ The president of the institution shall be a non-voting member and secretary of the board.

5/ The members to be nominated pursuant to sub-article (2) and (3) of this Article shall be past or present holders of responsible positions and notable personalities especially in teaching or research and in integrity, or be representatives of the customers of the products and services of the institution and whose exceptional knowledge, experience and commitment are such as to enable them to contribute to the attainment of the mission of the institution and the objectives of higher education generally.

6/ The board at its discretion may invite any resource persons to any of its sessions.

7/ The board shall have a quorum when five of the voting members attend; provided however, that in the event that it proves difficult for five members to attend under certain circumstances, the board shall conduct its sessions with a quorum of four voting members. The board shall specify in its rules of procedures the circumstances under which this provision may apply.

8/ In the event the chairperson may not attend a scheduled session, the attending members shall choose a chairperson from among the attending members for that particular session and execute the session's agenda.

9/ The board shall resolve matters by simple majority votes.

## 46. Regular Sessions of the Board

1/ The board shall conduct three to four regular sessions in a year. The sessions shall be spread in such a manner as to enable it to give strategic leadership and influence preparations of plans and budgets as well as plan implementation by the institution.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አባላቱ አንድ ሶስተኛው በሚጠይቁበት ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ማድረግ ይችላል፡፡

፫/ ኘሬዚዳንቱ የቦርዱ ሰብሳቢ ስምምነትን በማግኘት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማድረግ ይችላል፤ ሁሉም የቦርዱ ስብሰባዎች በቂ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ በሰነድ መያዛቸውን፣ ሰነዶቹ በጥንቃቄ መጠበቃቸውን እና ቦርዱ በሚያዘው መሠረት ውሳኔዎቹ በትክክል ለሚመለከታቸው መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ፵፯. የቦርድ አባልነት መቋረጥ

የቦርድ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

፩/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፤

፪/ በፈቃደኝነት ከአባልነት በመልቀቅ፤

፫/ በሞት፣ በሕመም ወይም በከባድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘት፤

፬/ በከባድ ጥፋት፣ በችሎታ ማጣት ወይም ስብሰባዎች ላይ ለመገኘት ከባድ የሆነ ድክመት በማሳየት ወይም ባለመቻል፤

፭/ ሚኒስቴሩ ቦርዱን ሙሉ በሙሉ ለመቀየር ወይም በከፊል ለመለወጥ ውሳኔ ላይ ሲደርስ፡፡

## ፵፰. ስለቦርድ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ

፩/ ቦርዱ አመራሩን በቀጣይነት ለማሻሻል የሚረዱ ትምህርቶችን ለማግኘት የራሱን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፪/ የቦርዱ የአፈፃፀም ግምገማ ኘሬዚዳንቱ ተሳትፎ በሚያደርግበት ድምፅ የመስጠት መብት ባላቸው አባላት በዝግ ስብሰባ ይካሄዳል፡፡

፫/ የቦርዱ ሰብሳቢ የግምገማውን ውጤቶች በየወቅቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያደርጋል፤ የቦርድ ሰብሳቢዎችና የትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ የጋራ መድረክም በዓመት ሁለት ጊዜ ይኖራል፡፡

፬/ ቦርዱ ግምገማውን መቼና እንዴት እንደሚያካሂድ ይወስናል፤ ሆኖም በአመት ቢያንስ አንድ የክትትል ግምገማና አንድ የማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the board may hold extra-ordinary sessions at the request of its chairperson or one-third of its voting members.

3/ The president may cause through the chairperson extraordinary sessions to be held and shall generally ensure that all board sessions are well-prepared for, regularly held, properly documented, and that the documentation is kept in order, and the results are effectively communicated as directed by the board.

## 47. Termination of Board Membership

Membership of the board may be terminated by:

1/ expiry of the term of office, as may be determined in the directive to be issued by the Ministry;

2/ resignation;

3/ illness, death or conviction of serious criminal offence;

4/ severe misconduct, incompetence, or serious failure or inability to attend board sessions;

5/ decision by the Ministry to reform the board in whole or in part.

## 48. Performance Self-Evaluation of the Board

1/ The board shall conduct its own performance evaluation with the purpose of drawing lessons to improve continuously its leadership.

2/ Performance evaluation of the board shall be conducted in a closed meeting of the voting members, with the president of the institution attending and contributing to the evaluations.

3/ The board chairperson shall submit regularly the results of the evaluation to the Ministry. The Ministry and board chairpersons shall also hold biannual joint forums.

4/ The board shall determine when and how to conduct its performance evaluations; provided however, that it shall have annually at least one monitoring evaluation and one summative evaluation.

## ፵፱. ስለሴኔት

የቦርዱ ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሴኔት የአካዳሚክ ጉዳዮችን በሚመለከት መሪ አካል በመሆን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩/ የተቋሙን የትምህርት ዘመን መወሰን፤

፪/ የተቋሙን አካዳሚክ ፕሮግራሞችንና ስርዓተ ትምህርቶቻቸውን መወሰን፤ የትምህርት ክፍሎች የሚሰጡትን ትምህርት እና የሚያካሂዱትን ምርምር ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ መምራትና አቅጣጫን ማስያዝ፤

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የትምህርትና ምርምር ፕሮግራሞችን በሚመለከትና የአካዳሚክ ማሕበረሰቡ የሚተዳደርበትን ደንብ ማውጣትና ስለ መከበሩም መከታተል፤

፬/ ዲግሪ የሚሰጥበትን ወይም የሚሰረዝበትን ሁኔታዎችን መወሰን፤

፭/ ተቋም አቀፍ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻና የተማሪዎች ምዘና ስርዓትን ማውጣት፤

፮/ በአካዳሚክ ሃላፊነት ስለሚሹሙት ጥያቄ ሲቀርብለት ለፕሬዚዳንቱ ምክር መስጠት፤

፯/ የፕሮፌሰር ማዕረግ ዕድገት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ደግፎ ለቦርዱ ማቅረብና በተባባሪ ፕሮፌሰር ዕድገት ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ መስጠት፤

፰/ በትምህርት ክፍሎች በሚቀርብ በፕሮፌሰር ደረጃ የሚፈፀም የአዲስ ቅጥር ጥያቄ ላይ መወሰን፤

፱/ የሴኔት ኮሚቴዎች ብዛት፣ አባልነት፣ ሃላፊነትና አሰራርን መወሰን፤

፲/ በፕሬዝዳንቱ በሚቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በተቋሙ እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባ ልዩ አስተዋፅኦ ላስመዘገቡ ሰዎች የክብር ዲግሪ ወይም ሌሎች ሽልማቶችን መስጠት፤

፲፩/ በተቋሙ ሥር ስላሉት የትምህርት ክፍሎች መከፈት፣ መዝጋት ወይም መዋሃድ በኘሬዝዳንቱ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት መርምሮ ማፅደቅ፤

፲፪/ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የሚሰጠውን ሌላ ሃላፊነት ወይም በፕሬዚዳንቱ የሚመራለትን ጉዳይ ማከናወን፡፡

## 49. The Senate

The senate, being the leading body of the institution for academic matters and without prejudice to the responsibilities of the board, shall have the responsibilities to:

1/ determine the academic calendar of the institution;

2/ accredit academic programmes and their curricula and supervise academic units to ensure the relevance and quality of education and research;

3/ legislate and ensure proper implementation of the institution's statutes related to all academic and research matters in accordance with this Proclamation;

4/ determine conditions on which degrees are awarded or revoked;

5/ determine an institution-wide framework for quality enhancement and student assessment;

6/ advise the president, upon request, on appointments of academic office holders;

7/ recommend to the board promotions of academic staff to the rank of professor and promote to the rank of associate professor;

8/ approve nominations by academic units for employment of academic staff with the rank of professor;

9/ decide on the type, number, membership, and responsibilities of its specialized committees;

10/ award honorary degrees and other academic prizes to persons with outstanding achievements meriting recognition by the institution, upon request by the president;

11/ examine and approve recommendations by the president in respect of opening, closure or merger of academic units under the public institution;

12/ perform other responsibilities which may be given to it in the establishing law of the institution or may be referred to it by the president.

## ፶. የሴኔት አባላት

፩/ የሴኔት የአባልነት ሁኔታ፣ የአገልግሎት ዘመን እና የአባላት ቁጥር በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከሴኔቱ አባላት ቢያንስ አብላጫው በፕሬዝዳንቱ የሚመረጡ ሆነው ለሃላፊነቱ የሚመጥኑና በተቋሙ ውስጥ በተነፃፃሪ ረጅም አገልግሎት ያላቸው የአካዳሚክ ሠራተኞች ይሆናሉ፡፡

፫/ ኘሬዝዳንቱ የተቋሙ የአካዳሚክ ማሕበረ-ሰብ በተገቢ ሁኔታ በሴኔቱ ውስጥ መወ-ከሉን ያረጋግጣል፤ የሴኔቱ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

፬/ ለአፈፃፀም ውጤታማነት ሲባል በሴኔቱ አባልነትና የአባላት ብዛትን እዲሁም የስራ ዘመን ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፕሬዚዳንቱ ምክር መሰረት ቦርዱ ማሻሻያ ማድረግ ይችላል፡፡

## ፶፩. የሴኔት ስብሰባዎች

፩/ ሴኔት የአባላቱን ዲስፕሊን ጨምሮ የራሱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሚያወ ጣው የውስጥ ደንብ ይወስናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ፕሬዝዳንቱ ሲጠይቅ ሴኔቱ ቀጣይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፫/ ሴኔቱ ፕሬዚዳንቱ ወይም ቦርዱ ሲጠይቅ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛው ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፬/ ፕሬዚዳንቱ የሴኔት ስብሰባዎች በበቂ ሁኔታ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ መዘገባቸውንና ቃለ ጉባኤዎቹ መጠበቃቸውን፣ በጉዳዮች ላይ የሚደረገው ውይይት ሁሉንም የዳሰሰ መሆኑን እና የሴኔት ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው በትክክል መተላለፋቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፡፡

፭/ ከሴኔት አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤ የሴኔት ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፤ ደምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለም ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፮/ ሴኔት በሃላፊነቱ መሰረት የትምህርት ክፍሎችን፣ የኮሚቴዎቹን እና እንደ አካል የራሱን የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፤ የግምገማው ውጤት በኘሬዚዳንቱ አማካኝነት ለቦርዱ ይቀርባል፡፡

፯/ ሴኔቱ በማንኛውም ስብሰባው ለስራ አስፈላጊ ናቸው ያላቸው የስራ ክፍሎችን ወይም ግለሰቦችን በአስረጂነት ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

## 50. Members of the Senate

1/ Membership and the number of members of the senate and their terms of office shall be determined by the establishing law of the public institution.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, at least the majority of the members of the senate shall be meritorious and senior members of the academic staff appointed by the president.

3/ The president shall chair the senate and ensure that the institution's academic community is appropriately represented in its membership.

4/ The Board of a public institution may, upon advice by the president, change or modify senate membership and terms of office, as necessary and consistent with good practice, but solely to ensure that it shall be fit for purpose

## 51. Sessions of the Senate

1/ The senate shall determine its regular and extraordinary sessions in its own rules of procedure and internal regulations, which shall also include disciplinary rules of its members.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the senate may hold continuous sessions upon request by the president.

3/ The senate may hold extraordinary sessions upon the request of the president, the board or one-third of its members.

4/ The president shall ensure that senate sessions are well-facilitated and prepared for, properly documented and the documentation kept in order, and are exhaustive in the discussion of issues; and that senate decisions are properly communicated and implemented.

5/ The senate shall have a quorum when more than half of its members attend and shall make decisions by simple majority votes, and in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

6/ The senate, consistent with its mandate, shall devote some of its sessions to evaluations of the academic performance of the academic units, of its committees, and its own performance; and the results of the evaluations shall be duly communicated by the president to the board.

7/ The senate at its discretion may invite resource persons it deems necessary to any of its sessions.

## ፶፪. ስለመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመትና የስራ አፈፃፀም ግምገማ

፩/ የተቋም ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (መ) መሠረት ቦርዱ አወዳድሮ ከሚያቀርባቸው እጩዎች መካከል እንደአግባቡ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ይሾማል፡፡

፪/ የፕሬዚዳንትነት የሃላፊነት ቦታ በቦርዱ በሚሰየም አካል በይፋ ለተወዳዳሪዎች ይገለጻል፡፡

፫/ የመንግሥት ተቋም ምክትል ፕሬዚዳንቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሐ) እና (መ) መሠረት በይፋ ተወዳዳሪዎች ተጋብዘው የተሻለ ብቃትና ዝግጁነት ያለው ተመርጦ በቦርድ ይሾማል፡፡

፬/ የመንግሥታዊ ተቋም እጩ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች የአካዳሚክ መሪነት እና የአስተዳደር ክህሎት ያላቸው እንዲሁም ለተቋማዊ ለውጥና እድገት ዝግጁ የሆኑና ሕገ መንግሥቱንና የመንግሥት ፖሊሲዎችን የተቀበሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውድድርና የምርጫ ሥነ ሥርዓት ዝርዝር መመሪያ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግና በቦርዱ ይወጣል፡፡

፮/ የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የሥራ ዘመን ስድስት አመት ሲሆን የምክትል ፕሬዚዳንት አራት አመት ይሆናል፤ ሆኖም የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተደጋጋሚ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

፯/ ቦርዱ የፕሬዚዳንቱንና የምክትል ፕሬዚ-ዳንቶቹን የሥራ አፈፃፀም የክትትል ግምገማ በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲሁም ጥልቀት ያለው ግምገማ ደግሞ በየሶስት አመቱ ፕሬዚዳንቱና ምክትል ፕሬዚዳንቶቹ በተገኙበትና ያለድምፅ በሚሳተፉበት ሁኔታ ያካሂዳል፡፡

፰/ ማንኛውም ሰው ከ፩፻፹ ቀናት በላይ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ወይም ተጠባባቂ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ መቆየት የለበትም፡፡

## ፶፫. የመንግስት ተቋም ፕሬዚዳንት ኃላፊነት

፩/ የቦርዱ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት ተቋም ፕሬዚዳንት የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የሚከተሉት ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

## 52. Appointment and Performance Evaluation of President and Vice Presidents of a Public Institution

1/ The president shall be appointed by the Minister or by the head of the appropriate state organ, as the case may be, from a short list of nominees provided by the board in accordance with sub-article (1)(d) of Article 44 of this Proclamation.

2/ The position of the president shall be publicly advertised by a body designated by the board.

3/ The vice presidents of a public institution shall be appointed based on merit and through competition by the board in accordance with sub-article (1)(c) and (d) of Article 44 of this Proclamation.

4/ The candidate president and vice president of a public institution shall have, among others, commendable academic leadership and managerial ability as well as demonstrable commitment to institutional change and development and to the Constitution and government policies.

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (4) of this Article, further particulars of requirements and procedures of competition and selection shall be determined by the law establishing the institution and by the board.

6/ The terms of office of the president of a public institution shall be six years and of the vice president four years; provided however, that and without prejudice to other provisions of this Proclamation, they may be repeatedly reappointed.

7/ The board shall make monitoring reviews on the performance of the president and vice presidents bi-annually and comprehensive in-depth reviews every three years in the presence and with the participation of the president and the vice presidents.

8/ No person shall hold the position of acting president or acting vice- president for a period of more than 180 days.

## 53. Responsibilities of the President of a Public Institution

1/ The president of a public institution shall be the chief executive officer of the institution and, without prejudice to the responsibilities of the board, shall have the responsibilities to:

ሀ) ተቋሙ የሥራ ድርሻውንና ተልዕኮውን ለማሳካት ይችል ዘንድ ተቋሙን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

ለ) የተቋሙ አካላትና ማሕበረሰብ የከፍተኛ ትምህርት አላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች ማክበራቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) የዚህ አዋጅና የሌሎች በተቋሙ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ አግባብነት ያላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

መ) ተቋሙ አገሪቱ በምትፈልገው መጠንና አይነት ከፍተኛ ጥራት ወይም ብቃት ያላቸው ምሩቃንን ማፍራቱን ያረጋግጣል፤

ሠ) መማር ማስተማርንና ምርምርን የሚያበረታታ አመቺ ተቋማዊ ሁኔታን ይፈጥራል፤ በቀጣይነት ይገነባል፤

ረ) የተቋሙ የምርምርና የማማከር ተግባራት ሁሉ ቅድሚያ በሚሰጣቸው አገራዊ ጉዳዮች ላይ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) ተቋሙ ተልእኮውን ለማሳካት ከአለም አቀፍ እንዲሁም ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት፣ አግባብነት ካላቸው ኤጀንሲዎች እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ድርጅቶችና ማሕበራት ጋር በዘላቂነት ግንኙነት እንዲፈጥር ያደርጋል፤

ሸ) ተቋሙ ሁልጊዜም ከሃገራዊና አለም አቀፋዊ እድገቶች ጋር እኩል የሚራመድና በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምርምር፣ በማማከር እና በማሕበረሰብ አገልግሎቶች የአገሪቱን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችለው ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ቀ) ተቋሙ በሰው ሃይሉ፣ በአደረጃጀቱና አሰራሩ ለተቋሙ ተልዕኮ የሚመጥን ብቃት ያለው የውስጥ አመራርና አስተዳደር ሥርአት እንዲኖረው ያደርጋል፤

በ) የአካዳሚክ ሃላፊዎችና የሴኔት አባላትን የአሰያየምና የሹመት ስርአትን በማዘጋጀትና በቦርዱ በማፀደቅ በተግባር ላይ ያውላል፤

ተ) በትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ በተቋማዊ ነፃነትና ተጠያቂነት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትና በወጪ ቆጣቢነት መርሆች ላይ በመመሥረት የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትን ለሴኔቱና ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፤

a) direct and administer the public institution with the aim of ensuring the achievement of its mission;

b) ensure that organs of the institution and its community uphold the objectives of higher education and guiding values of the institution;

c) ensure that the provisions of this Proclamation and of other laws applicable to the institution are respected;

d) ensure that the institution prepares high quality graduates in as many numbers and fields consistent with the needs of the country;

e) create and continuously build a conducive institutional environment stimulating learning and research;

f) ensure that the institution's research and consultancy activities focus on national priorities;

g) ensure that the institution in the pursuit of its mission is perpetually connected internationally as well as with federal and state institutions, relevant agencies and business and industry, and associations;

h) ensure that the institution always keeps abreast national and international developments and positions itself to respond effectively to the country's needs in education, training, research, consultancy and community services;

i) ensure that the institution has a capable system of internal leadership and management in its human resource, organization and performance;

j) design and implement, upon ultimate approval by the board, nomination and appointment systems of academic heads and senate members;

k) determine and implement, upon approval by the senate and the board, academic unit-and-department level governing bodies and structures guided by the principles of relevance and quality of education and research, autonomy, efficacy and efficiency of service delivery;

ቸ) የቅጥርና ሃላፊነት ቦታዎች በውድድር የሚያዙ መሆኑንና ከሃላፊነት መነሳትም በስራ አፈፃፀም ግምገማ፣ በዲስፕሊን ጉዳይ እና በአገልግሎት ዘመን ማብቃት ብቻ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ኀ) የተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ፣ ደንብና መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርአት አግባብነት ባለው የመንግስት ፖሊሲ፣ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሰረት መቀረጻቸውን ያረጋግጣል፤

ነ) ተቋማዊ የደረጃ መለኪያዎችን ያዘጋጃል፤ የተቋሙ የአካዳሚክና የአስተዳደር ሥራዎች በወጡት መለኪያዎች መሠረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ኘ) የተቋሙን ገቢና ወጪ በትክክል የሚያሳዩ የሂሳብ መዛግብት መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

አ) የቦርድ፣ የሴኔት፣ የአስተዳደር ካውንስል እና የዩኒቨርሲቲ ካውንስል ሰብሰባዎች በበቂ ዝግጅትና ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ከ) በተቋሙ ውስጥ ወይም በተቋሙና በሶስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን የተቋሙን ተልዕኮና ጥቅሞች ከማሳካት አኳያ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፤

ኸ) የተቋሙ እንቅስቃሴና መሠረታዊ ግንኙነቶች በተገቢው የመረጃ ስርዓት መመዝገባቸውን፣ መረጃው በአግባቡ መጠበቁንና አግባብነት ላላቸውም ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ወ) የተቋሙን እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፀድቁም ያስፈፅማል፤

ዐ) ቦርዱ፣ የተቋሙ ማሕበረሰብ፣ መንግስትና ሕዝብ ስለተቋሙ ሁኔታ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ዘ) በተቋሙ ምድረ ግቢ ህይወትና ንብረትን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ የአደጋ መከላከያና የጥበቃ ሥርአት እንዲገነባ ያደርጋል፤

ዠ) ተቋሙ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸውም ግንኙነት ተቋሙን ይወክላል፤

l) ensure that employment and official positions are achieved through competition and that removal from office is based on performance evaluation, disciplinary matters and end of tenure of office alone;

m) ensure that policies, directives and procedures of the institution are designed in conformity with the provisions of this Proclamation, pertinent laws and government policies;

n) develop and implement institutional standard measures and ensure that the academic and administrative operations of the institution are on the basis of the standards;

o) ensure that the institution maintains a healthy balance of income and expenditure and proper books of accounts of all incomes and expenditures;

p) ensure that board and senate sessions as well as of those other leadership bodies such as the managing council and the university council are well-prepared for and held regularly;

q) resolve by peaceful and legal means all intra-institutional disputes and disputes with third parties, in pursuit of the institution's mission and best interests;

r) ensure that all fundamental operations and substantive transactions of the institution are appropriately documented in text and data form as appropriate and that the information is, without prejudice to institutional interests, appropriately and readily accessible to end-users;

s) prepare institutional plans and budget, and ensure their implementation upon approval;

t) inform periodically the board, government and the public about the state of the institution;

u) build and maintain a reliable safety and security system that protects life and property in the premises of the institution;

v) represent the institution in all its dealings with third parties;

የ) በተቋሙ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ደ) እንዳስፈላጊነቱ ለምክትል ፕሬዚዳንቶች እና አግባብነት ላላቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ሃላፊዎች ሃላፊነቱን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ጀ) የውጪ ጉዞዎቹን በታቀዱና ለተቋሙ ባላቸው ፋይዳ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ጠ) በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ እና በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፪/ ኘሬዚዳንቱ ሙሉ ጊዜውን ለቢሮው ስራዎች ያውላል፤ ለአገልግሎቱ ተገቢውን ደሞዝና ጥቅማጥቅሞች ያገኛል::

፫/ ኘሬዚዳንቱ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራው ላይ በማይገኝበት ጊዜ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ እሱን ተክቶ እንዲሠራ ይወክላል፤ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱም የማይገኝ ቢሆን ግን ሌላ ምክትል ፕሬዚዳንትን ሊወክል ይችላል::

## ፶፬. የመንግስት ተቋም ምክትል ኘሬዚዳንት ሃላፊነት

፩/ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የሚሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግስት ተቋም ምክትል ኘሬዚዳንት የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ) ፕሬዚዳንቱን ሃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ ማማከርና ማገዝ፤

ለ) በኘሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን::

፪/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ቦርዱ እንደሁኔታው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር በመመካከር አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚወስነውን ያክል ምክትል ኘሬዚዳንቶች ይኖሩታል::

፫/ ምክትል ኘሬዚዳንቶች አብዛኛው የሥራ ጊዜያቸውን ለቢሮው ስራዎች ያውላሉ፤ ለአገልግሎታቸውም ተገቢውን ደሞዝና ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ::

፬/ በማንኛውም የመንግስት ተቋም ውስጥ ተባባሪ ምክትል ኘሬዚዳንት የሚባል አይኖርም::

w) open and operate bank accounts in the name of the institution;

x) delegate, as may be necessary, his powers and responsibilities to the vice presidents and appropriate heads of academic units;

y) ensure that his foreign travels are of value to the institution and planned;

z) discharge such other responsibilities as may be given to him by the establishing law of the institution and by the board.

2/ The president shall devote full time to the requirements of his office; and shall be remunerated appropriately for his services in the form of basic salary and other benefits.

3/ In the case of absence from duty, the president shall delegate, as a standard practice, the academic vice president on his behalf and, in the case of simultaneous absence of the said vice president, any of the other vice presidents.

## 54. Responsibilities of Vice President of a Public Institution

1/ The vice-president of a public institution, without prejudice to those responsibilities given to him under the establishing law of the institution, shall have the responsibilities to:

a) advise, assist and support the president in the exercise of his responsibilities;

b) exercise the responsibilities the president may entrust to him.

2/ Any public institution may have as many vice presidents as the board determines in consultation with, as the case may be, the Ministry or the state organ.

3/ Vice presidents shall devote most of the time to the requirements of their offices and shall be remunerated appropriately for their services in the form of basic salary and other benefits.

4/ There shall not be associate vice presidents in any public institution.

## ፶፭. ስለኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንት አገልግሎት መቋረጥ

፩/ የመንግሥት ተቋም ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ኘሬዚዳንት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ከሃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፡-

ሀ) በፈቃዱ ሥራ በመልቀቅ፤

ለ) በችሎታ ማጣት፣ በከባድ ጥፋት፣ በሕመም ወይም በሞት ምክንያት የተሰናበተ ከሆነ፤

ሐ) በፈቃድ ከ፩፻፹ ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ከተለየ፤

መ) ያለፈቃድ ከ፵፭ ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ከተለየ፤ ወይም

ሠ) የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ከቦርድ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ወይም የቦርዱ ሃሳብ ባይቀርብም ተገቢ እርምጃ ነው ብሎ ካመነ እንደአግባቡ ሚኒስትሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ኃላፊ ፕሬዝዳንቱን ከሥራ ማሰናበት ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ቦርዱ ምክትል ፕሬዚዳንትን ከሃላፊነት ሊያሰናብት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሶስት ተከታታይ የክትትል ወይም በአንድ ጥልቅ የስራ አፈፃፀም ግምገማው የፕሬዚዳንቱ ወይም የምክትል ፕሬዚዳንቱ በሃላፊነት መቀጠል ተቋሙን ይጎዳል ብሎ ቦርዱ ካመነ እንዳግባብነቱ ከሃላፊነቱ እንዲሰናበት እርምጃን ሊያስወስድ ወይም ሊወስድ ይችላል፡፡

## ፶፮. የአስተዳደር ካውንስል

፩/ ኘሬዚዳንቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሃላፊዎች ለመጨመር ያለው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ኘሬዚዳንቱ፣ ምክትል ኘሬዚዳንቶቹ እና የተቋሙ አጠቃላይ ተማሪዎች ጉዳይ ሃላፊ የአስተዳደር ካውንስሉ ዋናዎቹ አባላት ይሆናሉ፤ የአስተዳደር ካውንስሉ ሰብሳቢ ፕሬዚዳንቱ ይሆናል፡፡

፪/ የአስተዳደር ካውንስሉ በስትራቴጂክ ጉዳዮችና ኘሬዚዳንቱ በጋራ መታየት አለባቸው ብሎ በሚያምንባቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ኘሬዝዳንቱን ያማክራል፤ እንዲሁም የተቋሙን እንቅስቃሴዎች የመከታተያ፣ የማስተባበሪያና የመገምገሚያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 55. Termination of Service of the President and Vice President

1/ The president or vice president of a public institution may be relieved of his responsibilities by:

a) resignation;

b) release on grounds of incompetence, severe misconduct, illness or upon death;

c) absence from duty for more than 180 consecutive days with official acquiescence;

d) absence from duty for more than 45 consecutive days without official acquiescence;

e) expiry of terms of office.

2/ The Minister or the head of the concerned state organ, as the case may be, may relieve the president of his post pursuant to the provisions of sub-article (1) of this Article and upon advice by the board, or without such advice if the Minister or the head of the concerned state organ is convinced that it is the right action to take.

3/ The board may relieve any vice president of his post, pursuant to the provisions of sub-article (1) of this Article.

4/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the board may, as the case may be, cause the removal or remove the president or any vice president if it determines, through three consecutive monitoring reviews or one in-depth review, his continuity in office would be injurious to the institution.

## 56. Managing Council

1/ Without prejudice to the power of the president to include other pertinent officers, the president, the vice presidents, and the officer in charge of institution-wide student affairs shall constitute the core members of the managing council; and the president shall chair the managing council.

2/ The managing council shall advise the president on strategic issues and on other cases that the president believes require collective examination as well as serve as a forum for monitoring, coordination, and evaluation of institutional operations.

፫/ የአስተዳደር ካውንስሉ ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ በመደበኛነት በታወቀ ቀንና ሰዓት መሠረት መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።

፬/ የአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባዎቹን የሚያ-ካሂደው ከመደበኛ አባላቱ መካከል አብዛኛ ዎቹ በተገኙበት መሆን ይኖርበታል።

፭/ የአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ኘሬዚዳንቱ በሚመድበው ፀሐፊ መያዝ ይኖርበታል።

፮/ ኘሬዚዳንቱ በአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባ-ዎች ሃሳብ በግልፅና በነፃ መንሸራሸሩን ያረጋግጣል፤ የሃሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የተፎካካሪ ሃሳቦቹን የተቀባይነት ክብደት ለማየት ሲባል ብቻ ኘሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

፯/ በኘሬዚዳንቱ ወይም በሱ በተወከለ ሌላ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሌላ አባል ልዩነቶች ሲኖሩ የአስተዳደር ካውንስሉን ውይይትና ውጤት ለሶስተኛ ወገን መግለጽ አይችልም።

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በግል ተቋማት ላይም እንዳግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ፶፯. የዩኒቨርሲቲ ካውንስል

፩/ የዩኒቨርሲቲ ካውንስል በኘሬዚዳንቱ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ፣ አባላቱ የአስተዳደር ካውንስሉ ዋናዎቹ አባላት፣ የአካዳሚክ ክፍሎች ሃላፊዎች፣ የሴኔት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የቤተመጻሕፍት ዋና ሃላፊ፣ ሬጅስትራር፣ ሌሎች ቁልፍ የአካዳሚክ መኮንኖች፣ የአገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ሃላፊዎች እና በኘሬዚዳንቱ ምክር ላይ ተመሥርቶ ቦርዱ በሚወስነው መሠረት የጾታ ተዋጽኦው የጠበቀ የአካዳሚክ ሠራተኞችና የተማሪዎች ተወካዮች ይሆናሉ።

፪/ የዩኒቨርሲቲ ካውንስል በተቋሙ ረቂቅ እቅድ፣ በጀት፣ አደረጃጀትና መመሪያዎች፣ የትምህርት ፕሮግራሞች፣ የትብብርና የግንኙነት ስምምነቶች፣ በትምህርት ክፍሎች መከፈል፣ ውህደትና መዘጋት እና በተቋሙ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ሃሳብ በመስጠት ኘሬዚዳንቱን ያማክራል።

፫/ የዩኒቨርሲቲ ካውንስል መደበኛ የስብሰባ ቀንና ሰዓት ኖሮት ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል።

፬/ በዩኒቨርሲቲ ካውንስል ስብሰባ ላይ የአባላቱ መገኘት ግዴታ ነው፤ በኘሬዚዳንቱ ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር አባልነት በውክልና ሊሰጥ አይቻልም፤ ስብሰባዎች ያለምልዓተ ጉባኤ ሊካሄዱ ይችላሉ።

3/ The managing council shall meet regularly at least twice a month on a regular day and time.

4/ The managing council shall hold and conduct its sessions with a majority of its core members present.

5/ Minutes of sessions of the managing council shall be taken by a secretary designated by the president.

6/ The president shall ensure free and open expression of views in managing council sessions. The president may order votes in case substantially competing opinions emerge to ascertain the weight of the competing opinions.

7/ No member other than the president or a person instructed by the president shall communicate to third parties the council's deliberations on controversial issues and the results thereof.

8/ The provisions of this Article shall also be applicable, as appropriate, with respect to private institutions.

## 57. University Council

1/ The president shall chair the university council, and its members shall consist of the core members of the managing council, all deans, directors, members of the senate standing committee, the chief librarian, the registrar, other key academic officers, service department heads, and, as it shall be determined by the board upon the advice of the president, an appropriate number of academic staff and student representatives with appropriate gender mix.

2/ The university council shall advise the president by expressing its views on institutional proposals regarding plans, budget, organizational structures, academic programmes, agreements of cooperation, and on division, merger and closure of academic units as well as on performance.

3/ The university council shall meet at least once every six months on the day and time that shall be fixed.

4/ Attendance of university council sessions by members shall be mandatory. Membership shall not be delegated except in accordance with the permission of the president. Sessions may be held without a requirement for quorum.

፭/ ፕሬዚዳንቱ በዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ ስብሰባ ሂደት ሃሳብን በነፃ ለመግለፅ የሚያበረታታ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤ በካውንስሉ ውይይት ሰፊ የሃሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የሃሳቦቹ ክብደትን ለማወቅ ሲባል ፕሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል::

፮/ የአስተዳደር ካውንስሉ ፀሃፊ ድምፅ የማይሰጥና በውይይቱ ላይ የማይሳተፍ ፀሃፊ ሆኖ ለዩኒቨርሲቲ ካውንስሉም ያገለግላል::

፯/ ፕሬዚዳንቱ ወይም ፕሬዚዳንቱ ከሰየመው ሰው ውጪ ማንኛውም አባል የዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ ቃል አቀባይ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም::

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዩኒቨርሲቲ ካውንስል የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

፱/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንዳግባቡ በግል ተቋማትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ::

## ፶፰. የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ

፩/ የመንግሥት ተቋማት ጥረቶቻቸውን ለማስተባበር፣ የትምህርት መለኪያዎችንና አሰራሮችን ለማመሳሰል፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እና ሚኒስቴሩን በከፍተኛ ትምህርት ሃገራዊና አለምአቀፋዊ የስትራቴጂ ጉዳዮች፣ ዕድገትና ሁኔታዎች ላይ ለማማከር በዚህ አዋጅ ዕውቅና የተሰጠው የምክክር መድረክ ሊያቋቁሙ ይችላሉ::

፪/ የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ በዚህ አዋጅ መሰረት መመስረቱን በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ይፋ እንቅስቃሴ ያደርጋል::

፫/ የመንግስት ተቋማት ፕሬዚዳንቶች ተቋሞ-ቻቸውን በመወከል የምክክር መድረኩ አባላት ይሆናሉ:: የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምክክር መድረኩ ስያሜ፣ ዓላማ፣ ተግባርና ሃላፊነት፣ አመራር፣ አሰራርና የስነስርዓት ደንብ በፕሬዚዳንቶቹ ጉባኤ ሊወሰን ይችላል::

፬/ የምክክር መድረኩ በፕሬዚዳንቶቹ ጉባኤ ውሳኔ የሚቋቋም ፅሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል::

፭/ የምክክር መድረኩ ቃል አቀባይ በፕሬዚ-ዳንቶች ጉባኤ ደንብ መሰረት በሰብሳቢነት የተመረጠው የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ይሆናል::

5/ The president shall ensure a democratic atmosphere stimulating free expression of opinions and ideas in sessions of the university council. The president may order votes in case substantially competing opinions emerge to ascertain the weight of the competing opinions.

6/ The secretary of the managing council shall also serve as the non-voting and non-consultative secretary of the university council.

7/ No member of the university council other than the president or a person nominated by the president shall serve as its official spokesperson.

8/ Without prejudice to the provisions of this Article, the university council may adopt its own rules of procedures.

9/ The provisions of this Article shall also be applicable, as may be appropriate, with respect to private institutions.

## 58. Forum of Public Institutions

1/ Public institutions may establish a forum, in accordance with this Proclamation and with an appropriate name, to coordinate efforts, harmonize academic standards and approaches, share experience, and to advise the Ministry on national and international strategic issues, trends and conditions of higher education.

2/ The establishment of the forum shall be effective as of the date of its registration by the Ministry upon ascertaining the consistency of its statutes with the provisions of this Proclamation.

3/ The presidents, representing their respective institutions, shall be members of the forum. Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the council of presidents may decide on nomenclature, aims, responsibilities, leadership architecture, procedures, and rules of the forum.

4/ The forum may establish its own office in accordance with the decision made by the council of presidents.

5/ The spokesperson of the forum shall be the incumbent leader of the forum, who shall be elected in accordance with its rules.

፮/ የምክክር መድረኩ ስራውን የሚያከናው-ነው በአባል ተቋማት አመታዊ የአባልነት መዋጮ፣ ስጦታዎችና ከሌሎች በሕግ ከተፈቀዱ ምንጮች በሚያገኘው ገንዘብ ይሆናል፡፡

፯/ የምክክር መድረኩ በአሰራሩ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጐች ድንጋጌዎችንም ማክበር ይኖርበታል፡፡

፰/ ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ በከፍተኛ ትምህ-ርት ጉዳዮች ላይ ከምምክር መድረኩ ጋር ለመምከር ይችላል፡፡

፱/ በመንግስት ተቋማት የምክክር መድረክና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሰረት በተቋቋመ የግል ተቋማት ማህበር መካከል እንዳስፈላጊነቱ የምክክር ግንኙነት ሊኖር ይችላል፡፡

፲/ የመንግስት ተቋማት የምክክር መድረክ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ወይም የሌሎች ሕጎችን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ ግድፈቶቹን እስኪያስተካክል ድረስ በሚኒስቴሩ ትዕዛዝ ሊታገድ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለመንግሥት ተቋማት መከፈል፣ መዋሃድ፣ የስም ለውጥና መዘጋት

### ፶፱. የመንግሥት ተቋም መከፈል፣ መዋሃድ ወይም የስም ለውጥ

፩/ አንድ የመንግስት ተቋም እንደአግባብነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ወይም በሚመለከተው ክልል በሚወጣ ሕግ መሠረት ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የመንግስት ተቋማት ሊከፈል ወይም ከሌላ የመንግስት ተቋም ጋር ሊዋሃድ ወይም ስሙ ሊለወጥ ይችላል፡፡

፪/ የመንግሥት ተቋማት መከፈል፣ መዋሃድ ወይም ስም መለወጥ የሚከናወነው የዚህ አዋጅና የሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይሆናል፡፡

### ፷. የመንግሥት ተቋም መዘጋት

፩/ እንደአግባብነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ውሳኔ የመንግሥት ተቋም እንዲዘጋ ማድረግ ይቻላል፡፡

፪/ የመንግሥት ተቋም መዘጋት በተገቢው ሚዲያ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

6/ The financial source of the forum shall be annual contributions by the member public institutions and grants and funds the forum may obtain from other legally permitted sources.

7/ The forum shall respect provisions of other applicable laws in its operations.

8/ The Ministry may, as may be necessary, consult the forum on issues of higher education.

9/ There may be, as may be necessary, consultative partnerships between the forum of public institutions and any legally established association of private institutions.

10/ Where the forum of public institutions contravenes the provisions of this Proclamation or any other applicable laws, it may be suspended by the order of the Ministry until it rectifies the irregularities.

## SECTION TWO

## DIVISION, MERGER, CHANGE OF NAME AND CLOSURE OF PUBLIC INSTITUTIONS

### 59. Division, Merger or Change of Name of Public Institution

1/ A public institution may be divided into two or more public institutions or merged with another public institution or its name be changed by regulation of the Council of Ministers or in accordance with a state's law, as the case may be.

2/ Division, merger or change of names of public institutions shall take place without prejudice to the provisions of this Proclamation and other applicable laws.

### 60. Closure of Public Institutions

1/ A public institution may be closed down by decision of the Council of Ministers or the appropriate organ of a state, as the case may be.

2/ The closure of a public institution shall be made public through the appropriate media.

**፷፩. ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ**

፩/ የመንግስት ተቋም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የመንግስት ተቋማት የተከፈለ ከሆነ መብቶቹና ግዴታዎቹ ለአዲሶቹ ተቋማት ይተላለፋሉ:: እያንዳንዱ አዲስ ተቋም ከነባሩ ተቋም የሚተላለፍለት መብትና ግዴታ መጠን መከፈሉ በተወሰነበት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ወይም የክልሉ ሕግ ይወሰናል::

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተዋሃዱ ተቋማት መብትና ግዴታ ለአዲሱ ተቋም ይተላለፋሉ::

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተከፈለው ወይም የተዋሃዱት የመንግስት ተቋማት ሕጋዊ ሰውነታቸውን አዲሶቹ ተቋማት በሕግ ከተቋቋሙበት ቀን ጀምሮ ያጣሉ::

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ የስም ለውጥ ያደረገ ተቋምን በሚመለከትም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

**61. Transfer of Rights and Obligations**

1/ Where a pubic institution is divided into two or more institutions pursuant to the provisions of this Proclamation, its rights and obligations shall be transferred to the newly formed institutions. The extent of rights and obligations to be transferred to each of the newly formed institutions shall be as prescribed by the Council of Ministers regulation or the state's law effecting the division.

2/ The rights and obligations of institutions merged in accordance with the provisions of this Proclamation shall be transferred to the new institution.

3/ The divided or merged public institution shall lose its former juridical personality from the date of the division or merger.

4/ The provisions of this Article shall, mutatis mutandis, apply with respect to an institution whose name has been changed.

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለመንግሥት ተቋም በጀትና የገንዘብ አስተዳዳር

## SECTION THREE

## BUDGET AND FINANCIAL MANAGEMENT OF PUBLIC INSTITUTIONS

**፷፪. በ ጀ ት**

፩/ የፌዴራል መንግስት ወይም ክልሎች ለመንግስት ተቋማት በጀት የሚመድቡት በስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነት ላይ በተመሠረተ የጥቅል በጀት ሥርዓት መሠረት ይሆናል::

፪/ የመንግሥት ተቋም አስቀድሞ ስምምነት የተደረሰበትን የአምስት ዓመት ጠቋሚ ጥቅል በጀት ይመደብለታል፤ ሆኖም ጥቅል በጀቱ በየዓመቱ እየተገመገመ የሚስተካከል ይሆናል::

፫/ የመንግስት ተቋም የገንዘብ ፍላጐቱን ለማሟላት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፮ እና ፷፯ በተገለጸው መሠረትና በሕግ ከተፈቀዱ ሌሎች ምንጮች ገቢዎችን ማሰባሰብ ይችላል::

፬/ እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም በተቋሙ ቦርድ የጸደቀውን የሥራ ዕቅድ፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነትን እንዲሁም የተቋሙን ዝግጁነት እየታየ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ በጥቅል በጀት ሥርዓት መሥራት ይጀምራል::

**62. Budget**

1/ Public institutions shall be funded by the federal government or states through block-grant system based on strategic plan agreements.

2/ Every public institution shall receive a block grant-budget, agreed upon in advance as indicative budget for a five-year period; provided however, that such block-grant budget shall be revised annually.

3/ Every public institution shall mobilize other income as provided for by Articles 66 and 67 of this Proclamation and other legally permitted sources.

4/ Depending on the state of its preparedness, every public institution may start operating under a block-grant system, depending on plans adopted by the board and the strategic plan agreement as well as on its general preparedness, after one year from the effective date of this Proclamation.

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የጥቅል በጀት አሠራር ተጠቃሚ ለመሆንና አስተዳደሩንም በአግባቡ ለመምራት ይችሉ ዘንድ የመንግስት ተቋማት የትምህርትና የገንዘብ መረጃዎችን የሚያስተዳድሩበትን አቅም መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

፮/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ተቋማት የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፡፡

፯/ የመንግስት ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ስጦታዎችን መቀበል ይችላል፤ ሆኖም የሚያገኘው ስጦታ በተቋሙ አቋም፣ ተልዕኮና ዓላማ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማይኖረው መሆን ይኖርበታል፡፡

፰/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ስለሚያገኘው ገንዘብና ከኢንቨስትመንት ስለሚያገኘው ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## ፷፫. የድጎማ በጀት

፩/ በማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም በአገልግሎት ላይ ያልዋለ የቀዳሚው ዓመት ጥቅል በጀት የተቋሙ ድጎማ በጀት ሆኖ ወደሚቀጥለው የበጀት ዓመት እንዲተላለፍና ለተቋሙ አገልግሎት እንዲውል ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ ተቋሙ የድጎማ በጀትን በካፒታል በጀት መልክ ብቻ ይጠቀምበታል፡፡

፫/ የድጎማ በጀት ከዓመቱ ጥቅል በጀትና ከተቋሙ ገቢ ከሚገኘው ገንዘብ ጋር እንደተቋሙ አጠቃላይ ዓመታዊ በጀት በቦርዱ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

## ፷፬. የገንዘብ አስተዳደር

፩/ የመንግሥት ተቋም ኘሬዚዳንት የተቋሙን የገንዘብ ጉዳይ በሕግ፣ በቅልጥፍና፣ በውጤታማነት፣ በቁጠባና በግልፅነት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነትና ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

፪/ ሕግ በሌላ ሁኔታ ያስቀመጣቸውን ሁኔታዎችና በጀትን አስቀድሞ በቦርድ የማፀደቅ አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ተቋም በጸደቀለት የሥራ ዕቅድ መሠረት ገቢውን በነፃነት የመጠቀም መብት ይኖረዋል፡፡

5/ Public institutions shall build their capacities in financial and educational data management to implement properly and efficiently block-grant funding within the period specified in sub-article (4) of this Article.

6/ The Ministry of Finance and Economic Development shall assist public institutions in implementing the provisions of this Article.

7/ Any public institution may accept donations from third parties; provided however, that no such donation or subsidy may negatively influence the standing, mission and objectives of the institution.

8/ Any public institution shall report to the Ministry of Finance and Economic Development and the Ministry or the appropriate state organ receipt of funds from third-parties and its investment incomes.

## 63. Budget Subsidy

1/ Any unutilized portion of allocated block-grant of any public institution may remain at the disposal of the institution as budget subsidy.

2/ The institution shall use the budget subsidy only as capital budget.

3/ The budget subsidy shall be budgeted together with the year's block grant and other institutional income for the year and approved by the board as the institution's total budget.

## 64. Financial Management

1/ The president of a public institution shall conduct the financial affairs of the institution in accordance with the law and with the principles of efficiency, efficacy, frugality and transparency.

2/ Without prejudice to other conditions provided by law and to the procedure of prior approval of the budget by the board, a public institution shall be free to use its income as it sees fit, in accordance with its approved business plan.

፫/ በጀት ባልፀደቀበት ወቅት ቦርዱ በጀቱን እስኪያፀድቀው ድረስ የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የተቋሙ መደበኛ ስራ እንዳይስተጓጎል በቀዳሚው የበጀት ዘመን አሰራርና መጠን መሰረት ወጪ እንዲያደርግ በቦርዱ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል::

## ፷፭. የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነት

፩/ የመንግሥት ተቋም ለአምስት ዓመት የሚቆይ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነት እንዳግባብነቱ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር ያደርጋል::

፪/ የስትራተጂክ ዕቅዱ ስምምነት በተለይ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) ስትራተጂክ ዓላማዎችን፣ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ የመማር-ማስተማር ውጤቶችንና ተቋማዊና የሰው ሃይል ልማትን፤

ለ) የታቀዱ የምርምር ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን፤

ሐ) የትምህርት ፕሮግራሞችን እና በተከታታይና በርቀት የሚሰጡ ፕሮግራሞችን፤

መ) የተማሪዎችን ብዛትና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ብዛትና የሙያ ብቃት ደረጃን፤

ሠ) የአካዳሚክ ሠራተኞቹን የብሔር ብሔረሰብ ተዋፅኦ ማመጣጠንን እና በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ ማሳደግን፣ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች የሚደረገውን እገዛ ማጠናከርን የሚመለከቱ እርምጃዎችን፤

ረ) ከመንግሥት የሚጠበቀውን ጠቋሚ የጥቅል በጀትና ሊከሠት የሚችለውን የገንዘብ ክፍተት ከሌሎች ምንጮች ለማሟላት በተቋሙ የተገባውን ግዴታ፤

ሰ) ጠቋሚ ጥቅል በጀቱና ተቋሙ ራሱ አሟላለሁ ያለውን ገንዘብ ለእያንዳንዱ የስትራተጂክ ዕቅዱ ዘመን መመደቡን የሚያሳይ ጠቋሚ ክፍፍል፤

ሸ) የስትራተጂክ ዕቅዱ በጀት በቂ ሳይሆን ቢቀር የተቀመጠውን መፍትሄ፣

ቀ) ተገቢ የሒሳብ፣ የክትትል፣ የግምገማና ሪፖርትን የማቅረብ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን::

፫/ ስትራቴጂክ ዕቅዱ የተመሠረተባቸው ታሳቢዎች ከተለወጡ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነቱ ሊሻሻል ይችላል::

3/ The board may authorize the president of a public institution to make necessary expenditures on the basis of the previous budget where the board may not be able to approve timely the budget for the current fiscal year.

## 65. Strategic Plan Agreement

1/ Every public institution shall conclude with the Ministry or the concerned state organ a strategic plan agreement for a period of five years.

2/ A strategic plan agreement shall, in particular, contain:

a) strategic objectives, academic priorities, learning outputs, and institutional and human resources development;

b) planned research projects and programmes;

c) study and diversity of programmes and continuing, distance and virtual education;

d) the number of students and the number and qualification of academic staff;

e) social goals such as measures to enhance the nation and nationality composition of its academic staff, increase the proportion of senior positions held by women, and assistance to disadvantaged sections of its students;

f) indicative block-grant budget commitments made by the government and the institution's commitment to make up, through other sources of income, the financing gap that may occur;

g) the indicative allocations of the block-grant budget and the funds to be mobilized by the institution for each year of the strategic plan period;

h) contingency plan in the event of non-fulfillment of the anticipated strategic-plan budget;

i) appropriate mechanisms of accounting, monitoring, evaluation and reporting.

3/ A strategic plan agreement may be amended in the event of significant changes in the circumstances or assumptions on which it has been based.

፬/ የመንግሥት ተቋማት ቀጣዩን ረቂቅ የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነታቸውን በወቅቱ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን ውስጥ እንደአግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ያፀድቃሉ፡፡

## ፷፮. ገቢን ስለማስገኘት

፩/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ ፕሬዚዳንት ጥያቄና በቦርዱ ውሳኔ የገቢ ማስገኛ ድርጅትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፪/ ድርጅቱ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ሕጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የሚሠራ ይሆናል፡፡

፫/ ድርጅቱን ለማቋቋም የሚያስፈልገው የመነሻ ገንዘብ በመንግስት የሚመደብ በጀት ሊሆን ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ሊኖሩት ይችላል፡-

ሀ) ድርጅቱ ከሚሠጠው አገልግሎት ወይም ከሚያከናውነው ሥራ የሚገኝ ገቢ፤

ለ) የተቋሙ ሠራተኞች በፈቃደኝነት ከሚያደርጉት መዋጮ፤

ሐ) ለድርጅቱ ከሚሰጡ ሥጦታዎች፤

መ) ከሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች፡፡

፭/ ተቋሙ የድርጅቱን የተጣራ ትርፍ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተልዕኮው መሣካት ሊጠቀምበት ይገባል፡፡

፮/ የድርጅቱ የፋይናንስ መግለጫዎች የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ለቦርዱ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## ፷፯. የገቢ ፈንድ

፩/ በመንግሥት ተቋም ውስጥ በቦርድ ተወስኖ እንደ አግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ሲፀድቅ የገቢ ፈንድ ሊቋቋም ይችላል፡፡

፪/ የፈንዱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) በተቋሙ የገቢ ማስገኛ ድርጅት የሚደረግለት መዋጮ፤

4/ Public institutions shall conclude the next strategic plan agreements, as the case may be, with the Ministry or the appropriate state organ within the current plan period.

## 66. Income Generation

1/ Without prejudice to the provisions of this Proclamation and other applicable laws, an income generating enterprise may be established by any public institution upon the request of the president and approval by the board.

2/ The enterprise shall have its own legal personality and operate, like any business organization, in compliance with all legal requirements.

3/ The initial capital required for the establishment of the enterprise may be a budget allocated by government.

4/ Without prejudice to sub-article (3) of this Article, the enterprise may have the following sources of income:

a) income generated from the services it renders and the activities it carries out;

b) voluntary contributions made by the staff of the institution;

c) donations;

d) other lawful sources of income.

5/ The institution shall use the net profits of the enterprise in the pursuit of its mission and objectives in accordance with the provisions of this Proclamation.

6/ The financial statements of the enterprise shall be submitted to the board within six months from the end of the fiscal year.

## 67. Income Fund

1/ An income fund may be set up in a public institution by decision of the board and, as the case may be, approval by the Ministry or the appropriate state organ.

2/ Sources of income of the fund shall be:

a) contributions made by the income generating enterprise of the institution;

ለ) በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያልዋለ የፈንዱ ገንዘብ፤

ሐ) ሥጦታዎች፤

መ) ሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች፡፡

፫/ ፈንዱ ቦርዱ በሚያጸድቀው መሰረት ለተቋሙ ልዩ ልዩ የዓቅም ግንባታ ተግባራት፣ ለሽልማትና ሌሎች ተግባራት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

፬/ የፈንዱ አጠቃቀም የበጀት ስርዓትን የተከተለ ይሆናል፡፡

## ፷፰. ሪፖርት ስለማቅረብና ስለቁጥጥር

፩/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም፡-

ሀ) በስትራተጂክ ዕቅዱ ላይ የተመሠረተውንና በአግባቡ ተመዝኖ የፀደቀውን ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና በኦዲ- ተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትን እንደአግባብነቱ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል ማቅረ- ብና የበጀት ዓመቱ ትምህርታዊና ሌሎች መረጃዎችን በዚህ አዋጅ አን- ቀጽ ፳፯ በተደነገገው መሠረት ማሳተም፣

ለ) በማናቸውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል የሚጠየቀውን መረጃ መስጠት፣

ይኖርበታል፡፡

፪/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም እንደአግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ሕግንና የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነቱን ማክበሩን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ሊደረግበት ይችላል፡፡

፫/ እንደአግባብነቱ ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ከሕግ፣ ከመንግስት ፖሊሲ፣ ከተቋሙ ተልዕኮ ወይም ደንቦች ጋር የሚጋጩ የቦርድ፣ የፕሬዚዳንት ወይም የሴኔት ውሳኔዎችን ሊሽር ይችላል፡፡

## ፷፱. የሂሳብ መዛግብት

፩/ የመንግሥት ተቋም በፕሬዚዳንቱ ኃላፊነትና አስተዳደር ሥር የሚመራ የተቋሙ ግዴታዎችንም ታሳቢ ያደረገ የገቢና የወጪ ሒሳብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓትን መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

፪/ የመንግስት ተቋም የደብል ኤንትሪ ሂሳብ አያያዝን የመከተል፣ ተቀጽላ የሆኑ ተግባራት ገቢና ወጪዎችን ከሌሎች ገቢዎችና ወጪዎች ለይቶ የመያዝ እና ለሁሉም የገቢና ወጪ ጉዳዮች የሒሳብ አያያዝ አጠቃላይ ሥርዓትን የመከተል ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

b) unutilized finance of the fund during the fiscal year;

c) donations;

d) other legally permitted sources of income.

3/ The fund may be used for different capacity building activities of the institution, prizes and other activities as shall be approved by the board.

4/ Disbursement of the fund shall comply with its budgetary appropriations.

## 68. Reporting and Supervision

1/ Any public institution shall:

a) submit to, as the case may be, the Ministry or the appropriate state organ duly evaluated and approved annual performance and audited financial reports based on the strategic plan agreement; and publish the educational and expenditure data for the fiscal year as provided for under Article 27 of this Proclamation;

b) furnish information to the Ministry or the concerned state organ whenever it is required to do so.

2/ Any public institution may be subject to supervision by the Ministry or the appropriate state organ to ensure its compliance with the law and strategic plan agreements.

3/ The Ministry or the appropriate state organ may annul decisions of the board, the president or the senate which are contrary to the law, government policy or to the institution's mission and statute.

## 69. Books of Accounts

1/ Every public institution shall install an accounting system, including income and expenditure accounting, and a reporting system, appropriate to its responsibilities, which shall fall under the responsibility and management of the president.

2/ Every public institution shall follow double-entry bookkeeping, keep costs and revenues related to supplementary activities separate from other costs and revenues, and shall observe general regulations on accounting in all other areas.

፫/ ሚኒስቴሩ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመማከር የአንድ የመንግስት ተቋም ሀብትንና ዕዳን ለመለካት ቀለል ያለ የመመዘኛና የኦዲት ሥርዓት ለመጠቀም የሚያስችል የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**፸. ኦዲት**

፩/ በማንኛውም የመንግሥት ተቋም ውስጥ ራሱን የቻለና ለፕሬዚዳንቱ ተጠሪ የሆነ የውስጥ ኦዲት ይቋቋማል፡፡

፪/ የመንግሥት ተቋም የውስጥ ኦዲት ክፍል ኃላፊ በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በቦርድ ይሾማል፡፡

፫/ የውስጥ ኦዲት የተቋሙን የአፈፃፀም፣ የፋይናንስና ንብረት ኦዲት አከናውኖ ውጤቱን ለፕሬዚዳንቱና ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፬/ እንደአግባብነቱ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም የክልሉ ዋና ኦዲተር ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ተቋም ሂሳብ በቦርዱ በተሰየመ የውጭ ኦዲተር በየአመቱ ተመርምሮ ውጤቱ ለፕሬዚዳንቱ፣ ለቦርዱና እንደአግባብነቱ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለግል ተቋማት

**፸፩. ተጠያቂነት**

፩/ የግል ተቋም በሚቋቋምበት የመመሥረቻ ሰነድ እና በመተዳደሪያ ደንቡ በተደነገገው መሠረት አግባብነት ላለው አካል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የግል ተቋም በትምህርት አሰጣጥና ምርምር ረገድ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ትክክለኛነት ተጠያቂነቱ ለሚኒስቴሩ ጭምር ይሆናል፡፡

**፸፪. ስለግል ተቋማት ሃላፊነት**

፩/ ማንኛውም የግል ተቋም የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

3/ The Ministry may, in consultation with the Ministry of Finance and Economic Development, issue directives on accounting and reporting system enabling the use of simplified valuation methods and auditing of statements for measurement of an institution's assets and liabilities.

**70. Audit**

1/ An autonomous internal audit unit accountable to the president shall be established in any public institution.

2/ The head of the internal audit unit of a public institution shall be appointed by the board upon recommendation by the president.

3/ The internal audit unit shall conduct performance, financial, and property audit of the institution and report the findings to the president and the board.

4/ Without prejudice to the powers of the federal or state Auditor General, as the case may be, the accounts of a public institution shall be audited annually by an external auditor appointed by the board; and the audit findings shall be reported to the board and the Ministry or the appropriate state organ.

## PART FOUR
## PRIVATE INSTITUTIONS

**71. Accountability**

1/ A private institution shall be accountable to the appropriate body as provided for in its memorandum of association and its by-laws.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, a private institution shall also be accountable to the Ministry in respect of the propriety of its operations in the provision of education and conducting research.

**72. Responsibilities of Private Institutions**

1/ Every private institution shall have the responsibilities to:

ሀ) በሚኒስቴሩ የሚወጡ የተማሪዎች ቅበላን የሚመለከቱ መመሪያዎችን በጥብቅ የመከተል፤

ለ) ትምህርታዊ ይዘትን፣ የማስተማር ዘዴን፣ የተማሪዎች መመዘኛና የፈተና-ዎች ሥርአትን እና የውጤት ሥርአትን ጨምሮ ቢያንስ ለደረጃው የሚጠበ-ቅበትን አነስተኛው የስርዓተ ትምህርት የጥራት ደረጃዎች የማረጋገጥ፤

ሐ) የአካዳሚክና የምርምር ክንውኖቹን አስመልክቶ ዓመታዊ ግለ-ግምገማና የተማሪዎችና የአካዳሚክ ሰራተኞች ግምገማ የማካሄድና ውጤቱን ለተቋሙ ማሕበረሰብ የማሳወቅና ለኤጀንሲውም ሪፖርት የማድረግ፤

መ) ከትምህርት ፕሮግራሞቹ መካከል በዲግሪ ለማስተማር ፈቃድ ባገኘባቸው የትምህርት መስኮች የሚከተለው ስርዓተ ትምህርትን፣ የቅበላ ዓቅምንና ትምህርቱን ለማጠናቀቅ የሚወስደውን መደበኛ ጊዜ በማካተት እውቅና የተሰጣቸው የትምህርት ፕሮግራሞችን ዝርዝር እና የአካዳሚክ ሰራተኞቹን ደረጃና የቅጥር ሁኔታቸውን የሚመ-ለከቱ መረጃዎችን በቀላሉ ተደራሽ በሆነ መልኩ የመያዝና እነዚሁኑ አስመልክቶ ለተማሪዎቹና ለኅብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፤

ሠ) በአመራርና በአስተዳደር አደረጃጀቱ፣ አሰራሩ፣ በአመራሩና በአስተዳደሩ ሃላፊዎች ብቃት፣ ተቋሙ የሚገኝበት አካባቢ፣ የትምህርት መገልገያዎችን ጨምሮ የካምፓሱ አጠቃላይ አካባቢያዊ ሁኔታ ተቋሙ ለተሰጠው ደረጃና ለሚያካሄዳቸው ሥልጠናዎች፣ ላለው የተማሪዎችና የሰራተኞች ብዛትና ለተሰማራበት የትምህርት መስክ የሚመጥን መሆኑን የማረጋገጥ፤

ረ) የአምስት ዓመት ዝርዝር የትምህ-ርት፣ የምርምርና የሥልጠና እቅ ድን እንዲሁም በእቅዱ ላይ በየዓ መቱ የተደረጉ ማስተካከያዎችን ለኤ ጀንሲው የማቅረብና እቅዱን ይፋ የማድረግ፤

ሰ) የትምህርት፣ የምርምርና የሥልጠና ተግባራቱን በተመለከተ ዝርዝር አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት በትም-ህርት ዓመቱ ማለቂያ ላይ ለኤጀን-ሲው ማቅረብና የትምህርት ግብአቶ-ቹንና ውጤቶችን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የማሳተም፤

ሸ) ሚኒስቴሩ የሚጠይቃቸውን መረጃ-ዎች ያለ ምንም ክፍያ ሚኒስቴሩ በሚፈልግበት አይነትና በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማቅረብ፤

a) ensure strict compliance with directives issued by the Ministry on admissions of students;

b) ensure the minimum curricula quality standards, including educational content, pedagogy, student assessment and examination system, and system of grading;

c) perform regular annual self-evaluation and evaluations by students and academic staff on its academic and research performance and make the results of the evaluations public to its community as well as report to the Agency;

d) maintain a readily accessible list of accredited study programmes offered, including the specific fields within the programmes in which the institution is authorized to offer degrees, and form of their delivery, enrollment capacity and the standard length of study, and the profiles of its academic staff and the modes of their employment; and give accurate information to its students and the public about the same;

e) ensure that its leadership and management structures, modus operandi of the structures, the leadership and management capabilities of the position occupants, its location, premises and facilities, and the campus environment generally are fit for the purposes of a higher education institution of its status, levels of studies, student and staff numbers, and the nature of the programmes and fields in which it is engaged;

f) submit to the Agency its detailed plans on education, research and training on a five-yearly basis, and annual up-dates of the plans; and make the plans public;

g) submit detailed annual reports to the Agency on its activities in education, research, and training at the end of each academic year and publish its educational input and output data as required by this Proclamation;

h) supply information required by the Ministry free of charge and in the form and within the time the Ministry may specify;

ቀ) የመክሰር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጥያቄ ከቀረበበት ይህንኑ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

በ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተግባሩን የማከናወን፡፡

፪/ የግል ተቋም አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን፤

ለ) የተቋሙን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ውጤት፤

ሐ) በትምህርት ዘመኑ በተቋሙ ውስጥ የተከሰቱ ሁኔታዎችን፤

መ) የትምህርቱን ዘመን ማብቃት ተከትሎ በተቋሙ የበላይ የአስተዳደር አካል የተፈረመበት ተቋሙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋምነቱ ያለበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ የግምገማ መግለጫ፡፡

፫/ ዓመታዊ የትግበራ ሪፖርት፣ የተቋሙ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እና የትግበራው የግምገማ ውጤት ይፋ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ሌሎች ድንጋጌዎችና በመደበኛ የአካዳሚክ ኦዲት አፈፃፀም ሳይገደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም የግል ተቋም ላይ ድንገተኛ የአካዳሚክ ኦዲት ወይም ማጣራት በማድረግ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## ፸፫. <u>የግል ተቋም የውስጥ ደንብ</u>

፩/ የግል ተቋም የውስጥ ደንብ ስለተቋሙ የአስተዳደር አካላት፣ የተቋሙ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ አሰጣጥ ሥነሥርአት፣ የአካዳሚክና ምርምር ጉዳዮች፣ የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን መብትና ግዴታ እና ስለቅሬታ አፈታት ሥርአት መደንገግ ይኖርበታል፡፡

፪/ የግል ተቋም የውስጥ ደንብ የዚህን አዋጅ ወይም የማንኛውንም አግባብነት ያለው ሌላ ሕግ ድንጋጌዎች የማይቃረን መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ ኤጀንሲው የግል ተቋማት ተገቢው የውስጥ ደንብ ያላቸው ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡

i) notify the Ministry immediately in case a bankruptcy proceeding is instituted against it;

j) conduct its operations in accordance with the provision of this Proclamation and other applicable laws.

2/ The annual report on the activities of a private institution shall include, among others:

a) activities and results thereof performed within the particular academic year;

b) results of performance evaluation of the institution;

c) internal developments that may have taken place in the institution in the course of the academic year;

d) a signed diagnostic statement of its state of general condition as an institution of higher education by its supreme governing body, following the end of the academic year.

3/ The annual report on activities, the long-term plans of the institution, and the results of evaluation of its activities shall be made public.

4/ Notwithstanding the other provisions of this Article and specifically provisions for academic audit, the Agency may conduct, as may be necessary, unscheduled reviews and investigations of any private institution and take corrective measures.

## 73. <u>Internal Regulations of Private Institutions</u>

1/ Internal regulations of a private institution shall stipulate the governing bodies of the institution, decision-making procedures of academic bodies, academic programmes, rights and obligations of the academic community, and grievance handling procedures.

2/ Internal regulations of a private institution and their amendments shall not contravene the provisions of this Proclamation and provisions of any other applicable law.

3/ The Agency shall ensure that any private institution has an appropriate and functional internal regulations.

## ፸፬. የእውቅና ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ

፩/ የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚኒስቴሩ እውቅናን ማግኘት ይኖርበታል።

፪/ ማንኛውም የግል ተቋም ዲግሪ ለመስጠት የሚችለው በሚኒስቴሩ እውቅና ሲሰጠውና እውቅና ባገኘበት የትምህርት ፕሮግራ-ሞች፣ የትምህርት ዓይነትና በተፈቀደለት የተማሪዎች ብዛት ብቻ ይሆናል።

## ፸፭. የእውቅና ፈቃድ ለማግኘት ስለሚ ቀርብ ማመልከቻ

፩/ የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማ-ሳደግ ወይም ለመለወጥ የሚፈልግ ማንኛ ውም ሰው የእውቅና ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻን ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) የተቋሙን ስምና ዋና አድራሻ፣

ለ) የተቋሙን የፋይናንስ አቅም፤

ሐ) ስለተቋሙ ተጠያቂ የሆነ አካልን ስምና አድራሻ፤

መ) የተቋሙን ባለቤቶች ስምና አድራሻ፤

ሠ) የተቋሙን ራዕይ፣ ተልእኮና ዓላማ፤

ረ) የትምህርት ፕሮግራሞችንና የትምህ-ርት ደረጃዎችን፤

ሰ) ደረጃውን የጠበቀ ስርዓተ ትምህርት፣ የተቀጠሩና የሚቀጠሩበትን ጊዜ በመለየት በቅርቡ የሚቀጠሩ የአካዳሚክ ሠራተኞች በሙያ ዓይነትና በትምህርትና በማዕረግ ደረጃ እና የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቁጥርና የትምህርት ደረጃ፤

ሸ) ተቋሙ ያለውና በቅርቡ የሚኖረው ለትምህርትና ለስልጠና የሚያስፈልጉ እንደ መፃህፍት፣ ቤተመፃሕፍት፣ ቤተሙከራ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የትምህርትና የምርምር መገልገያዎች ዝርዝር፤

## 74. Requirement for Accreditation

1/ Any person who desires to establish, upgrade or modify a private institution shall be required to secure an accreditation from the Ministry in accordance with this Proclamation.

2/ Any institution which has received accreditation and offers accredited study programmes shall have the right to issue valid qualifications of higher education to its graduates consistent with accredited study programmes, specific disciplines in the programmes, and its enrollment capacity.

## 75. Application for Accreditation

1/ Any person who desires to establish, upgrade or modify a private institution shall submit an application for accreditation to the Agency.

2/ An application submitted pursuant to sub-article (1) of this Article shall contain:

a) name and main address of the institution;

b) financial capacity of the institution;

c) the name and address of the body to which the institution is accountable;

d) the names and addresses of the owners of the institution;

e) vision, mission and objectives of the institution;

f) programmes of study and levels of education and training;

g) appropriate curriculum, the number and level of qualifications of academic staff and technical and administrative support staff recruited by the institution and soon to be recruited with recruitment plan;

h) details of the available and soon to be made available facilities and services required for conducting education or training such as libraries, laboratories, classrooms, educational and research facilities, and the manner in which they are maintained;

ቀ) የአዲስ ተማሪዎች ቅበላ መመዘኛ፤

በ) የተቋሙን ደረጃ፣ የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን መብትና ግዴታ እና የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርአትን የያዘ የውስጥ ደንብ፤

ተ) የተቋሙ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ስራዎች የሚከናወኑበት የአመራርና የአስተዳደር ሥርአት፤

ቸ) የተቋሙን የአምስት አመት እቅድ፤

ኀ) አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት የተሰጡ የኢንቨስትመንትና ሌሎች አስፈላጊ ፈቃዶችን፡፡

፫/ ኤጀንሲው የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ፦

ሀ) በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች ተቋሙ ማሟላቱን ሲያረጋግጥ የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል፤

ለ) ተቋሙ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች የማያሟላ ሆኖ ሲያገኘው የእውቅና ፈቃድ ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፡፡

፬/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ ጥያቄን ውድቅ ሲያደረግ ጥያቄው ተቀባይነት ያሰገኘባቸውን ምክንያቶች ለአመልካቹ በፅሁፍ መግለፅ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ የተከለከለ አመልካች የፈቃድ ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ በ፺ ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት እንደገና ለማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የእውቅና ፈቃድ በድጋሚ የተከለከለ አመልካች ዳግም ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ሊያመለክት ይችላል፡፡

፮/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ክልከላ ውሳኔውን እንደ ክልከላው ሁኔታ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## ፸፮. የእውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ኤጀንሲው የቀረበለትን የእውቅና ፈቃድ ማመልከቻ መርምሮ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱት መመዘኛዎችን ተቋሙ ማሟላቱን አረጋግጦ በተገቢ ጊዜ ውስጥ የእውቅና ፈቃዱን ይሰጣል፡፡

i) admission requirement for new students;

j) internal regulations of the institution providing for the status, rights and responsibilities of the academic community and grievance handling procedures;

k) system of governance and management by which the academic and administrative affairs of the institution shall be conducted;

l) a five-year plan of the institution;

m) investment and other necessary permits issued by the appropriate government organs.

3/ The Agency shall, upon examining the application submitted to it:

a) issue accreditation where it ascertains that the institution satisfies the requirements under this Proclamation and regulations and directives issued for the implementation of this Proclamation;

b) reject the application for accreditation where it finds that the institution does not meet the requirements under this Proclamation and regulations and directives issued for the implementation of this Proclamation.

4/ Where the Agency rejects an application for accreditation pursuant to sub-article (3)(b) of this Article, it shall notify the applicant in writing about the grounds for the rejection of the application.

5/ An applicant that is denied accreditation pursuant to sub-article (3)(b) of this Article, may reapply after fulfilling the requirements for accreditation within 90 days from the date of notification of the denial; provided however, that an applicant whose application is rejected twice may not reapply until after one year.

6/ The Agency shall make the decision on the rejection of accreditation public through appropriate media depending on the character of the decision.

## 76. Issuance of Accreditation

1/ Where the Agency, upon examining the application for accreditation submitted to it and ascertaining that the institution satisfies the requirements under this Proclamation and regulations and directives issued for the implementation of this Proclamation, issue the accreditation within a reasonable time period.

፪/ በኤጀንሲው የሚሰጠው የእውቀና ፈቃድ፡-

ሀ) የተቋሙን ስምና አድራሻን፣

ለ) የተቋሙን ደረጃ፣ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን፣

ሐ) የመምህራኑ ብዛትና የትምህርት ደረጃ ስብጥርን፣

መ) የ ተማሪዎች ብዛትና ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታን፣

ሠ) የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠበትን ቀንና የሚያገለግልበትን የጊዜ ገደብን፣

ረ) የእውቅና ፈቃዱን የሰጠውን ሃላፊ ስምና ፊርማ እና የኤጀንሲውን ማህተም፣

መያዝ ይኖርበታል፡፡

፫/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ መስጠቱን አስመልክቶ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

**፸፯. <u>የእውቅና ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፮ መሠረት ለግል ተቋም የተሰጠ የመጀመሪያው የእውቅና ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለ፫ ዓመታት ያገለግላል፡፡

፪/ ለግል ተቋም የተሰጠ የእውቅና ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃና በቀጣይም በየአምስት ዓመቱ አዲስ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት መታደስ ይኖርበታል፡፡

**፸፰. <u>የእውቅና ፈቃድን ለማሳደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እንዲታደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

፩/ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጥ ወይም ቀደም ሲል እንዲታደስ ሲጠየቅ ለኤጀንሲው ከቀረበው ማመልከቻ ጋር ቀርበው የነበሩትን መረጃዎችና የትምህርት ግብአቶችና መገልገያዎች አሁን ያሉበትን ደረጃ የሚገልፅ ሪፖርትን፤

፪/ በተቋሙ የጥራት ማጎልበት ስርዓት የተካሄደ የግለ-ግምገማ ውጤት ሪፖርትን፤

፫/ የተቋሙ የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የድጋፍ ሰጪ ቋሚ ሠራተኞች ዝርዝርን፤

2/ The accreditation issued by the Agency shall indicate:

a) the name and address of the institution;

b) the status, programmes and curriculum of the institution;

c) the number and qualification mix of the academic staff;

d) enrollment capacity and location of the campus;

e) the date of issuance of the accreditation and its duration of validity;

f) the name and signature of the official issuing the accreditation with the seal of the Agency affixed.

3/ The Agency shall make public the issuance of the accreditation through appropriate media.

**77. <u>Validity of Accreditation</u>**

1/ An accreditation issued to a private institution pursuant to Article 76 of this Proclamation shall be valid for three years from the date of its issuance.

2/ An accreditation issued to a private institution shall be renewed upon the expiry of the period of its validity prescribed under sub-article (1) of this Article and, subsequently, every five years before the beginning of a new academic year.

**78. <u>Application for Renewal of Accreditation</u>**

An application submitted for renewal of accreditation pursuant to sub-article (2) of Article 77 of this Proclamation shall include the following:

1/ a report on the state of fact of the information and provisions submitted to the Agency during the application for accreditation or for a previous renewal;

2/ a self-assessment document prepared by the quality enhancement system of the institution;

3/ the list of permanent academic staff and technical and administrative support staff of the institution;

፬/ በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝርን፤

፭/ ለትምህርትና ለምርምር እንዲሁም ከትምህርት ጋር ተዛማጅነት ላላቸው ሌሎች ተግባራት ማከናወኛ የተዘጋጁ መግልገያዎችንና የትምህርት መረጃዎች ዝርዝርን፤

፮/ በኦዲተር የተመረመሩ የመጨረሻዎቹን ሦስት ዓመታት የተቋሙ የሂሳብ ሪፖርቶችን፤

፯/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በኤጀንሲው የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን።

## ፸፱. <u>የእውቅና ፈቃድ ለማደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ ውሳኔ አሰጣጥ</u>

፩/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፰ መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲቀርብለት በገምጋሚ ኮሚቴው አማካይነት፦

ሀ) በተቋሙ የቀረበውን ግለ-ግምገማ፣ ሰነድና ሌሎች ሪፖርቶችን ይመረምራል፤ በነዚሁ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችንና ስታትስቲካዊ መግለጫዎችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤

ለ) በተቋሙ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን ባገናዘበ መልክ፦

(፩) የተቋሙን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ መሠረተ ልማቶች፣

(፪) ሥርአተ ትምህርትን፣ የመማር ማስተማር ጥራትን፣ የተማሪዎች መረጃዎችን፣ የትምህርት መገልገያዎችን፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና የመምህራኑ ብቃትን ጨምሮ የተማሪዎች የትምህርቱ ጥራት ግምገማን፣

(፫) የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ዝርዝርና የትምህርት ደረጃን፣

(፬) የምርምር ስራዎቹን መጠንና አግባብነት፣

በጥልቀት ይገመግማል፤

፪/ ኤጀንሲው በገምጋሚ ኮሚቴው ሪፖርት መሠረት፦

ሀ) በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች በተቋሙ መሟላታቸውን ካረጋገጠ የእውቅና ፈቃዱ እንዲታደስለት ያደርጋል፤ ወይም

4/ the list of students that have been enrolled each year in each field of study offered by the institution;

5/ the list of facilities and teaching aids made available for educational and research activities as well as other related activities of the institution;

6/ audited financial reports of the institution for the last three years;

7/ other information required by the Agency in accordance with the directive to be issued by the Ministry.

## 79. <u>Decision on Application for Renewal of Accreditation</u>

1/ Upon receiving an application for the renewal of accreditation pursuant to Article 78 of this Proclamation, the Agency shall, through its assessment committee:

a) evaluate the self-assessment document and other reports and ascertain the veracity of the information and statistics contained therein;

b) taking into account the nature of the institution's programmes, closely scrutinize:

(1) the academic and administrative infrastructure made available at the institution;

(2) the processes of teaching and learning which shall include the curricula, quality of teaching and learning, student support services, student involvement in the teaching-learning processes, and student evaluation on the quality of education, including on the quality of the academic staff;

(3) list and qualifications of support staff;

(4) scale and relevance of research activities.

2/ The Agency, based on the report of the assessment committee, shall:

a) issue renewal of the accreditation where it ascertains that the institution satisfies the requirements under this Proclamation and regulations and directives issued for the implementation of this Procllamation; or

ለ) በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈ-ሩትን መመዘኛዎች በተቋሙ አለመ-ሟላታቸውን ካረጋገጠ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል::

፫/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን ከወሰነ ተቋሙ ያለበትን ደረጃ መሆን ከሚገባው ደረጃ ጋር በማነፃፀር ከሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ ጋር በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች አመልካቹን በጽሑፍ ያሳውቀዋል::

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም በኤጀንሲው የተገለጹትን የማስተካከያ እርምጃዎች በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ውሰጥ በመውሰድ ተፈላጊ መመዘኛዎችን አሟልቶ እንደገና ማመልከት ይችላል::

፭/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄውን ውድቅ ያደረገበትን የመጨረሻ ውሳኔ በተገቢው ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል::

፮/ የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ተማሪዎችና ሰልጣኞች ቢኖሩ አግባብ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ተዛውረው ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል::

## ፹. <u>የእውቅና ፈቃድ እድሳት</u>

፩/ የታደሰው እውቅና ፈቃድ፣

ሀ) የተቋሙን ስምና አድራሻን፣

ለ) የተቋሙን ደረጃ፣ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን፣

ሐ) የ መምህራኑ ብዛትና የትምህርት ደረጃ ስብጥርን፣

መ) የተማሪዎች ብዛትና ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታን፣

ሠ) የእውቅና ፈቃዱ የታደሰበት ቀንና የሚያገለግልበት የጊዜ ገደብን፣

ረ) የእውቅና ፈቃዱን ያደሰውን ሃላፊ ስምና ፊርማ እና የኤጀንሲው ማህተም፣

መያዝ አለበት::

b) reject the application for the renewal of accreditation where it finds that the institution does not meet the requirements under this Proclamation and the regulations and directives issued for the implementation of this Proclamation.

3/ Where the Agency rejects an application for renewal of accreditation pursuant to sub-article (2)(b) of this Article, it shall notify the applicant in writing, together with a detailed statement explaining about the institution's standing vis-à-vis the requirements and recommending the corrective measures to be taken by the institution within a definite period of time.

4/ An applicant that is denied renewal of accreditation under sub-article (2)(b) of this Article, may reapply after fulfilling the requirements for accreditation by taking the corrective measures suggested by the Agency within the specified time limit.

5/ The Agency shall make public, through appropriate media, its final decision on rejection of renewal of accreditation.

6/ Any institution denied of renewal of accreditation shall take appropriate measures in order that the students and trainees it has admitted shall be transferred to other appropriate institutions and complete their studies.

## 80. <u>Renewal of Accreditation</u>

1/ The renewed accreditation shall indicate:

a) name and address of the institution;

b) status of the institution and its programmes and curricula;

c) number and qualifications of the academic staff;

d) enrollment capacity and location of the campus;

e) date of renewal of the accreditation and its duration of validity;

f) name and signature of the official renewing the accreditation with the seal of the Agency affixed.

፪/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ መታደሱን አስመልክቶ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

2/ The Agency shall make public the renewal of the accreditation through appropriate media.

## ፹፩. የእውቅና ፈቃድን ስለመሰረዝ

፩/ ኤጀንሲው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የግል ተቋም የእውቅና ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ሲረጋገጥ፤

ለ) ተቋሙ የሚፈለግበትን ደረጃ ባለመጠበቁ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም የሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጐች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ጥሶ በመገኘቱ በኤጀንሲው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በማስጠንቀቂያው በተገለፀው የጊዜ ገደብ ጉድለቶችን ሳያስተካክል ሲቀር፤

ሐ) ተቋሙ ሲፈርስ ወይም ሥራውን ሲያቆም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የሚወሰነው የእውቅና ፈቃድ ስረዛ አዲስ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫/ የዕውቅና ፈቃዱ የተሠረዘ የግል ተቋም ተማሪዎቹና ሰልጣኞቹ ትምህርታቸውን አግባብነት ባላቸው ሌሎች ተቋማት እንዲፈፅሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 81. Revocation of Accreditation

1/ The Agency may revoke the accreditation of a private institution on any one of the following grounds:

a) where it is found that the accreditation has been given on the basis of false information;

b) where the institution fails to rectify defects within the time fixed in the warning given by the Agency for failure to satisfy the required standards or for contravening the provisions of this Proclamation, any other relevant law or regulations or directives issued for the implementation of this Proclamation.

c) where the institution is dissolved or ceases its operations.

2/ A revocation of accreditation pursuant to sub-article (1)(a) or (b) of this Article shall be made effective before the beginning of a new academic year.

3/ Any institution the accreditation of which has been revoked shall take appropriate measures that the students and the trainees continue their studies in other appropriate institutions.

## ፹፪. አቤቱታ ስለማቅረብ

፩/ በኤጀንሲው ውሳኔ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም የእውቅና ፈቃድ እንዲታደስለት ያቀረበው ማመልከቻን ውድቅ የተደረገበት ወይም የዕውቅና ፈቃዱ የተሠረዘበት ማንኛውም ተቋም ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ለሚኒስቴሩ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ አቤቱታውን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የይግባኝ መርማሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አመልካቹ ቀርቦ እንዲሰማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 82. Appeal

1/ Any institution may appeal to the Ministry for a review of the Agency's decision on rejection of an application for accreditation or renewal of accreditation or on the revocation of accreditation, within 30 days of the receipt of the decision.

2/ The Ministry shall establish an appeal committee to review the decision of the Agency and to make recommendations.

3/ The Ministry shall grant the applicant the right to be heard before the final decision is given on the appeal.

## ፹፫. ምትክ የእውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ የእውቅና ፈቃድ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ማንኛውም የግል ተቋም ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ለኤጀንሲው ለማመልከት ይችላል፡፡

፪/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት፡-

ሀ) አመልካቹ የተበላሸውን የዕውቅና ፈቃድ እንዲመልስ፣

ለ) የዕውቅና ፈቃዱ የጠፋ ከሆነ ስለመጥፋቱ ሕጋዊ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ፣ ካደረገ በኋላ ምትክ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## ፹፬. የእውቅና ፈቃድ ስለመመለስ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የእውቅና ፈቃድ የተሰረዘበት ተቋም ፈቃዱ በተሰረዘ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለኤጀንሲው መመለስ አለበት፡፡

፪/ አንድ ተቋም ደረጃውን የለወጠ፣ ከሌላ ጋር የተዋሃደ፣ የተከፈለ ወይም ስሙን የለወጠ ከሆነ በዚሁ መሠረት ተገቢውን አዲስ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው የቀድሞውን ፈቃድ ለኤጀንሲው መመለስ ይኖርበታል፡፡

## ፹፭. ስለ እውቅና ፈቃድ ክፍያ

የእውቅና ፈቃድ ክፍያ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፹፮. ስለ መንግሥት ድጎማ

፩/ መንግስት ብቁ የሰው ሃይልን በማፍራት የአገሪቱ የልማት ፍላጎት የሚጠይቀው የማስፈፀም ዓቅም ግንባታን ለማጠናከር የሚሰሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማትን ለማበረታታት የበጀት ድጎማ ወይም የዓቅም ግንባታ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት፡-

ሀ) በቅደመ-ምረቃና ድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች በተቋማቱ ውስጥ ተመዝግበው የሚማ-ሩትን መደበኛ ተማሪዎችና ከእነርሱም መካከል በነፃ የሚማሩትን ተማሪዎች ብዛት፣

ለ) ተቋማቱ የቋሚ ቅጥር ዕድል ያስገኙ-ላቸውን የአካዳሚክ ሠራተኞች ብዛት፣

## 83. Issuance of Substitute Accreditation Certificate

1/ Any private institution may apply to the Agency for a substitute accreditation certificate where its accreditation certificate is damaged or lost.

2/ The Agency shall issue a substitute accreditation certificate:

a) in case of damage, upon the return of the damaged certificate by the applicant;

b) in case of loss, having received legally acceptable evidence.

## 84. Returning Accreditation Certificate

1/ An institution whose accreditation is revoked in accordance with this Proclamation shall return the accreditation certificate to the Agency within 15 days.

2/ An institution shall return the previous certificate to the Agency in order to get a new appropriate accreditation due to change of its grade, merger, division or change of its name.

## 85. Accreditation Fee

Fees to be paid for accreditation shall be prescribed by directives to be issued inaccordance with this Proclamation.

## 86. Government Subsidy

1/ The government may give budget subsidy or capacity building support to non-profit making private institutions that strive to strengthen the developmental efforts of the country by preparing particularly good quality professionals.

2/ The Ministry shall specify, by directives, the procedure for non-profit making private institutions to apply for budgetary subsidy or capacity building from government and the method of monitoring their use, taking into account:

a) the number of full-time undergraduate and graduate students enrolled at the institution, and the number of students who do not pay tuition fees;

b) the number of academic staff for whom the institution is the place of primary employment;

ሐ) የተቋማቱን የትምህርት ጥራት፣

መ) ተቋማቱ በትምህርትና ምርምር ረገድ ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች፣ እና

ሠ) ተቋማቱ ራሳቸው አገልግሎቶቻቸውን ለማስፋፋት ያፈሰሱትን ሀብት፣

በማገናዘብ ከመንግስት የበጀት ድጎማ ወይም የዓቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ሊያመለክቱ ስለሚችሉበትና አጠቃቀሙን ስለሚከታተልበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል።

፫/ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት፡-

ሀ) በተወሰነ መስክ ወይም ተወራራሽ በሆኑ መስኮች ለሚሰጧቸው የዲግሪ ፕሮግራሞችና ጥናቶች ድጋፍ እንዲሆን፣ ወይም

ለ) የሚያካሂዷቸው የዲግሪ ፕሮግራሞች የላቀ ጥራት ያሏቸው ስለመሆናቸው በኤጀንሲው ተረጋግጦ እንዲበረታቱ ለማድረግ፣

አስቀድሞ ለዚሁ ዓላማ ከተያዘው የመን ግስት ገንዘብ ላይ ተጨማሪ ድጎማ ሊደረግላቸው ይችላል።

## ፹፯. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለመንግሥት ተቋማት ስለሚሰጥ የዕውቅና ፈቃድም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ክፍል አምስት

## ስለአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

## ፹፰. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የከፍተኛ ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ዝግጅትና አተገባበር ከአለም አቀፍ እድገት እና ከአገራዊ ፍላጐትና መመዘኛዎች ጋር የሚመጣጠን መሆኑን ያረጋግጣል፤

፪/ በባችለር፣ በማስትሬት፣ በህክምና ስፔሻሊቲ እና በዶክትሬት ፕሮግራሞች ትምህርት ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ መመዘኛዎችን ይወስናል፤

፫/ የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

፬/ በዚህ አዋጅ፣ በመንግስት ፖሊሲና እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚያወጣቸው መሥፈርቶች መሠረት በመንግስታዊ ተቋማት ደረጃና በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚደረጉት የተማሪዎች ምደባ እና የተማሪዎች ቅበላ ስርዓቱ ባጠቃላይ ፍትሃዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

c) quality of education in the institution;

d) past achievements of the institution in the area of teaching-learning and research; and

e) institution's own funds invested in the development of its facilities.

3/ Non-profit making private institutions may receive earmarked additional subsidy funds:

a) to support degree programmes offered in specific fields of study or interdisciplinary studies; or

b) as incentive if the degree programmes are of a particularly high quality as confirmed by an assessment of the Agency.

## 87. Applicability of the Provisions of this Part

The provisions of this Part shall, mutatis mutandis, be applicable with respect to the accreditation of public institutions.

## PART FIVE

## POWERS AND DUTIES OF EXECUTIVE ORGANS

## 88. Powers and Duties of the Ministry

Without prejudice to other responsibilities provided for by this Proclamation, the Ministry shall have the powers and duties to:

1/ ensure that preparation and delivery of curricula of higher education are in accordance with international developments and national demands and requirements;

2/ determine the requirements for Bachelor, Master, Medical Specialty, and Doctoral programmes;

3/ ensure the implementation of the national policy and strategy on higher education;

4/ ensure that student placement to and within any public institution and procedures of admissions in general are consistently fair and just in accordance with this Proclamation, government policy, and with requirements it may stipulate from time to time as necessary;

፭/ ሃገራዊ አነስተኛ የትምህርት ብቃት መመ- ዘኛዎችን፣ የሙያ ስነምግባር ደንቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሰራር ሥነሥርአትን ያወጣል፤

፮/ መንግስት ለመንግስት ተቋማት ጥቅል በጀት የሚመድብበትን መሥፈርትና ሥር- አት ይወስናል፤

፯/ በተቋማት መካከል ትብብርና የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰/ ለተቋማት የውስጥ የጥራት ማጎልበቻ ሥርአት ድጋፍ ይሰጣል፤

፱/ የመንግስት ተቋም ስትራቴጂክ እቅድን ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

፲/ የአገሪቱ የከፍተኛ ባለሙያ የሰው ሃይል ፍላጐትን ለመለየትና ይህንኑ ለማሟላት ጥናት ያካሂዳል፤

፲፩/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርት መስክ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፤

፲፪/ የመንግስት አካላት፣ የሙያ ማሕበራት፣ የንግድ ማሕበራት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰዎች በትምህርት፣ በስልጠና፣ በተግባር ልምምድ፣ በምርምር እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳዮች ላይ ከተቋማት ጋር በጋራ ወይም በትብብር እንዲሰሩ ያበረታታል፤

፲፫/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ያረጋግጣል።

## ፹፱. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ በግልጽ የሠፈሩ የግምገማና የእውቅና አሰጣጥ መመዘኛዎችንና ሥርአትን በማዘጋጀት በስራ ላይ ያውላል፤

፪/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተቋምን ወይም የተቋምን ክፍሎች ለመክፈት ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ ፕሮጀክትን በመገምገም ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፫/ የእውቅና ፈቃድ ወይም እድሳት ለመስጠት የሚያስችል የተቋም ብቃትና የትምህርትና የስልጠና አግባብነትና ጥራት ግምገማን ያካሂዳል፤

5/ issue minimum national educational quality standards, professional code of conduct and necessary standard guidelines to be followed by institutions;

6/ determine criteria and standard procedures for government funding of institutions;

7/ facilitate cooperation and information exchange among institutions;

8/ provide technical support for internal quality assurance and enhancement systems of institutions;

9/ approve and ensure the implementation of strategic plans of public institutions;

10/ conduct studies to identify as well as to meet the professional and intellectual manpower needs of the country;

11/ in co-operation with concerned organs, promote investments to be made in the higher-education sector;

12/ encourage government organs, professional associations, business organizations, and other appropriate persons to work jointly on matters concerning education, training, research, practicum or apprenticeship and research and technology transfer;

13/ ensure proper implementation of the provisions of this Proclamation.

## 89. Powers and Duties of the Agency

Without prejudice to other responsibilities provided for by this Proclamation, the Agency shall have the powers and duties to:

1/ develop and implement clearly designed evaluation and accreditation criteria and procedures;

2/ evaluate projects for the opening or transforming of any institution or its units in accordance with this Proclamation and regulations and directives to be issued for the implementation of this Proclamation, and submit its recommendation to the Ministry;

3/ evaluate the activities, relevance and quality of education and training of any institution on the basis of which accreditation and renewal of accreditation shall be given;

፬/ የተቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ስለመቻሉ ግምገማ ያካሂዳል፤

፭/ በማንኛውም ተቋም የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል፤

፮/ የግምገማ ኮሚቴዎችን ያደራጃል፤ ሃላፊነታቸውና አሰራራቸውን ይወስናል፤ ስራቸውን ሲያከናውኑ የሚከተሉትን የስነ ምግባር መመሪያም ያወጣል፤

፯/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለእውቅና ፈቃድና ለእውቅና ፈቃድ እድሳት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይመረምራል፤ይወስናል፤

፰/ የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለመገምገም ወይም የእውቅና ፈቃድ ወይም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄዎችን ለመርመር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አግባብነት ካላቸው አካላት መረጃና አስተያየት ይጠይቃል፤

፱/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡትን የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎች መከተላቸውን ለማረጋገጥ ተቋማትን በመገምገም የሚደረሰባቸውን የግምገማ ግኝቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፲/ የተቋማትን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችሉ መመዘኛዎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፲፩/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተቋማትን መዋሃድ፣ መከፈል፣ መዘጋት ወይም የስም ለውጥ አስመልክቶ ለሚኒስቴሩ ምክር ይሰጣል፤

፲፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተቋማት ወይም የነሱ ቅርንጫፎች በተቋቋሙባቸው አገሮች እውቅና ያገኙ መሆናቸውንና በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫/ በውጭ ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችና የነዚህኑ ተቋማት ደረጃና አቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤

4/ evaluate whether the relevance and quality enhancement system of institutions are capable of ensuring quality in higher education;

5/ ensure that higher education and training offered at any institution are in line with economic, social and other relevant policies of the country;

6/ organize assessment committees, and determine their operational procedures and code of conduct for their assessment activities;

7/ examine and decide on applications submitted to it for accreditation and renewal of accreditation in accordance with the provisions of this Proclamation, and regulations and directives to be issued for the implementation of this Proclamation;

8/ request, when necessary, for information and opinions from appropriate organs to assess the relevance and quality of education or to examine accreditation or renewal of accreditation applications;

9/ evaluate institutions to ensure their compliance with the standards of relevance and quality of education set forth in this Proclamation and regulations and directives to be issued for the implementation of this Proclamation, and present to the Ministry conclusions resulting from the assessment;

10/ prepare and submit to the Ministry requirements and directives for the determination of status of institutions;

11/ advise the Ministry in respect of merger, division, closure or change of name of institutions in accordance with the provisions of this Proclamation;

12/ ensure that foreign institutions or their branches operating in Ethiopia are accredited in their country of origin and comply with the relevance and quality standards set by this Proclamation and regulations and directives to be issued for the implementation of this Proclamation;

13/ collect and disseminate information about the status, standards, and programmes of study offered by foreign institutions;

፲፬/ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃዎች የአቻነት መወሰኛ ሥርአት ያዘጋጃል፣ በውጭ አገር ተቋማት የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎ-ችን የአቻ ግምት ይሰጣል፤

፲፭/ እውቅና ያገኙ ተቋማትንና ደረጃቸውን፣ ዋና ዋና ክፍሎቻቸውንና የትኩረት መስኮቻቸውን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ይይዛል፣ አግባብነት ባላቸው የመገናኛ ዘዴዎች መረጃዎቹን በየጊዜው ለሕዝብ ያሰራጫል::

## ፺. የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የከፍተኛ ትምህርትንና የተቋማትን እድገት አስመልክቶ አገር አቀፍ ስትራቴጂ ያዘጋጃል፤

፪/ በከፍተኛ ትምህርት ሥርአት ውስጥ ትም-ህርትና ምርምር ስለሚያድጉበት ሁኔታ የረጅም ጊዜ አገር አቀፍ እቅድ ያዘጋጃል፤

፫/ የተቋማትን የትምህርትና ምርምር ጥራ-ትን፣ የአካዳሚክ ሰራተኞችን ብቃት እንዲ-ሁም የትምህርት ፕሮግራሞችን ለማሳደግ የሚያግዙ አገር አቀፍ የመነሻ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

፬/ በተቋም ደረጃ የሚወጣ እቅድና ስትራቴጂ በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚወጣ አጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት እቅድና ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለዚህም ከተቋማት ጋር በቅርበት ይሠራል፤ የስትራቴጂክ እቅድ ስምምነትን ይመረምራል፤ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፭/ ለእያንዳንዱ የመንግስት ተቋም ስለሚሰጥ የጥቅል በጀት ምደባ ሃሳብን ያመነጫል፤ የጥቅል በጀት ምደባ አፈፃፀምን ይከታተላል፤

፮/ የተቋማትን ዓመታዊ የትምህርት፣ የምርምር፣ የፋይናንስና ሌሎች ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፤ እንደተገቢነቱም አትሞ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፤

፯/ ተቋማት የተለያየ መጠን ባለው የልማት በጀት መልክ የማበረታቻ ሽልማት ስለሚያገኙበት መመዘኛና አሰራር ለሚኒስቴሩ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በስራ ላይ ያውላል፤

፰/ የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑንና በአካሄዱ ከአለም አቀፉ እውነታ ጋር እኩል የሚራመድ መሆኑን ያረጋግጣል፤

14/ develop guidelines on equivalence of higher education qualifications, and determine the equivalence of qualifications issued by foreign institutions;

15/ maintain up-to-date information on the accredited institutions and their status, main units and specialties, and periodically disseminate the same to the public through appropriate means of communication.

## 90. Powers and Duties of the Centre

Without prejudice to other responsibilities provided for by this Proclamation the Centre shall have the powers and duties to:

1/ prepare national strategy for the development of higher education and institutions;

2/ prepare long-term national plans for the development of education and research within the system of higher education;

3/ prepare national proposals to raise the quality of research activities of institutions, the qualifications of the academic staff, and the study programmes of institutions;

4/ ensure that institution level planning and strategy are in line with the national higher education macro plan and strategy; and for this purpose, work closely with institutions; examine strategic plan agreements and, upon approval, follow up their implementation;

5/ develop proposals on block grant budget allocations to individual public institutions, and monitor the implementation of the same;

6/ collect, analyze and as appropriate publish and disseminate annual educational, research, financial and other statistical data of institutions;

7/ submit proposal to the Ministry on criteria and scheme of rewarding institutions through grant of differentiated developmental budget, and implement the same upon approval;

8/ ensure that higher education is in line with the overall socio-economic development needs of the country and abreast global trends in orientation and approaches;

፱/ ቀልጣፋ የከፍተኛ ትምህርት አስተዳደር፣ አመራርና ማኔጅመንት እንዲኖር ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤

፲/ በወቅታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች፣ አሰራርና ውጤቶች ላይ ምርምርና ጥናት በማድረግ ትክክለኛ የአሠራር አቅጣጫዎችን ይጠቁማል፤ ለማሻሻያ፣ ለለውጥና ለልማት የእውቀት ግብአት ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

፲፩/ በአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ማሻሻያና ልማት ስትራቴጂና እቅድ ላይ ሃሳብ ይሰጣል፤

፲፪/ በሃላፊነቱ ማዕከልነት በአገራዊ ተቋማት መካከል ትብብርን ያጎለብታል፤ የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮችን ከሚያከናውኑ ተመሳሳይ የውጭ አገር አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፤

፲፫) በማቋቋሚያ ሕጉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፺፩. የአገልግሎት ክፍያዎች

፩/ የመንግስት ተቋም ለትምህርት አገልግሎቶች ክፍያ መጠየቅ ይችላል፤ የሚጠይቀው ክፍያ ዓይነት፣ መጠንና የክፍያ አፈፃፀም አግባብ የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖው ቦርዱ በሚወጣው መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል።

፪/ የግል ተቋም ክፍያ የሚያስከፍልበት የውስጥ ደንብ የሚወሰነው በተቋሙ የመመስረቻ ሰነድ ውስጥ ሥልጣን በተሠጠው አካል ይሆናል።

### ፺፪. ወጪ ስለመጋራት

፩/ የማንኛውም በመንግሥት ተቋም ተማሪ የሆነና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፩ መሠረት ለትምህርቱ የማይከፍል ኢትዮጵያዊ የትምህርቱን ወጪ በገንዘብ ወይም በአገልግሎት እንዲሸፍን ይደረጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ሥርዓት እና ሥርዓቱ በየጊዜው የሚከለስበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይፈጸማል።

9/ advise the Ministry on ways of ensuring efficient higher education governance, leadership and management;

10/ conduct research and studies on current policies, practices and results, and propose appropriate course of action, and serve as a resource centre for reform, change and development;

11/ give opinion on higher education reform and development strategy and plan of the country;

12/ foster cooperation among national institutions in its areas of activity, and maintain contacts with institutions of other countries which are in charge of issues of higher education;

13/ discharge other responsibilities that may be entrusted to it by the establishing law.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 91. Fees

1/ A public institution may charge tuition fees; however provided that the kind, amount and the manner of payment of the charge, without prejudice other provisions of this Proclamation, shall be determined by the directive to be issued by the board.

2/ The rules for charging and the amount of fees in a private institution shall be determined by the body authorized by the statutes of its formation.

### 92. Cost-Sharing

1/ Any Ethiopian student studying in a public institution and who is not required to pay tuition fee pursuant to Article 91 of this Proclamation shall contribute, in cash or in service, to cover the cost of his education.

2/ The cost-sharing of higher education scheme referred to in sub-article (1) of this Article and the periodical review of the scheme shall be as prescribed by regulation of the Council of Ministers.

## ፺፫. <u>አገልግሎት በሌሎች ወገኖች እንዲሰጥ ስለማድረግ</u>

፩/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ተገቢና ተግባራዊ ሲደረግ የሚችል ሆኖ ሲያገኘው የድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሰጥ ሊያደረግ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም አገልግሎት በሌሎች አቅራቢዎች እንዲሰጥ ሲያደረግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ለዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 93. <u>Outsourcing of Services</u>

1/ Any public institution may outsource support services to other providers as appropriate and whenever feasible.

2/ In outsourcing services, any public institution shall ensure that beneficiaries get appropriate and effective services and that the costs of the services are fair and acceptable.

## ፺፬. <u>የመሬት አቅርቦት</u>

መንግስት አግባብነት ባላቸው ሕጐችና ፖሊሲዎች መሠረት ተቋማት ለትምህርት፣ ለምርምርና ለሕብረተሰብ አገልግሎት ተግባራት ማከናወኛ የሚያስፈልጋቸውን መሬት ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 94. <u>Access to Land</u>

Government may make the necessary land available for use by institutions for the purposes of their education, research and community-services operations in accordance with applicable laws and policies.

## ፺፭. <u>ኃላፊነት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎችን ተላልፎ ከተገኘ በሕግ መሠረት የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡

፪/ እውቅና ያለው የትምህርት ማስረጃ ሳይሰጠው እንደተሰጠው አስመስሎ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ወይም ዕውቅና ላልተሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ማስረጃ የሰጠ ወይም የሃሰት የትምህርት ማስረጃ የሰጠ ማንኛውም ሰው በሕግ መሠረት የፍትሐብሔርና የወንጀል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 95. <u>Liability</u>

1/ Any person who fails to comply with the provisions of this Proclamation or regulations or directives to be issued for the implementation of this Proclamation shall, in accordance with the law, be civilly and criminally liable.

2/ Any person who, without having acquired accredited diploma, presents forged diplomas or any institution which issues diplomas for a programme that is not accredited shall, in accordance with the law, be civilly and criminally liable.

## ፺፮. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

፩/ በአዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ መሠረት የተሰጡ የቅድመ እውቅናና የእውቅና ፈቃዶች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጡ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ የግል ተቋማት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ ለማሟላት የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፡፡

፫/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት መታየት የጀመሩና ያላለቁ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናሉ፡፡

## 96. <u>Transitory Provisions</u>

1/ Pre-accreditation and accreditation certificates issued under Proclamation No. 351/2003 shall be deemed to have been issued in accordance with this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, private institutions shall take adjustment measures to fully meet the requirements of this Proclamation within one year from its effective date.

3/ Cases pending prior to the coming into force of this Proclamation shall be decided in accordance with the provisions of this Proclamation.

## ፺፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

## ፺፰. የተሻሩ ሕጎች

፩/ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤ ሆኖም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪዎች ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ እስከሆነ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል::

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም የአሰራር ልምዶች በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

## ፺፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም ፯ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 97. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

## 98. Repeal

1/ The Higher Education Proclamation No. 351/2003 is hereby repealed; provided however, that regulations and directives issued pursuant to it shall, in so far as they are consistent with the provisions of this Proclamation, remain in force until replaced by regulations and directives to be issued in accordance with this Proclamation.

2/ No law, regulations, directives or practices shall, in so far as they are inconsistent with the provisions of this Proclamation, have effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 99. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of September, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**